# ዜና ጳጳሳት ኢትዮጵያውያን

«ዜና ሕይወቶሙ ወዕረፍቶሙ ለብፁዓን ወቅዱሳን
አበው ኢትዮጵያውያን»

ዲያቆን መርሻ አለኸኝ

አዲስ አበባ፣ 1996 ዓ.ም

© መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

ALL RIGHTS RESERVED

ይህ መጽሐፍ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሊቃውንት ጉባኤ ታርሞና ተስተካክሎ የተፈቀደ ነው።

የአዘጋጁ አድራሻ

ፖስታ ሣጥን ቁጥር – 12418

Email:– mershing@yahoo.com

# መታሰቢያነቱ

1ኛ. ሚያዝያ 27 ቀን 1994 ዓ.ም ከምንወደውና ከሚወደን ቤተ ሰዎቹ ከዚህ ዓለም በሞት ለተለየው ለአባቴ አቶ አለኸኝ መንግሥቴ፤

2ኛ. ትምህርታቸውን፣ ምክራቸውንና ጸሎታቸውን ስንፈልግ ሳለ በድንገት ጥቅምት 30 ቀን 1996 ዓ.ም ከሞት ለተለዩን ደግ አባታችን ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ ይሁንልኝ።





«መልካም ስም ከብዙ ባለጠግነት ይበልጣል» /ምሳሌ 22÷1/፡
«መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ በሰው ፊት ይብራ» /ማቴ.5÷16/።

በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ «ስምና ሥራ» የሚሉት ቃላት «መልካም» በሚል ቅጽል ወይም አጎላማሽ ቃል በመገለፃቸው ትርጉማቸው ጎልቶ ይታያል። የሰው ልጅ «አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ» እንደ ተባለው /ዘፍ. 3÷19/ ከተወሰነ ዕድሜ በኋላ ከሥጋዊ ዓለም ይለያል። ለዘሩ፣ ለትውልዱ በዓለም ላይ የሚቀረው ስሙና ሥራው ነው። ስም የሚያስጠራ ሥራ ከሌለ ግን ስሙዬው ሲያልፍ ወዲያው ይረሳል፤ አስታዋሽ አይኖረውም። ፈጣሪውንም አያስመሰግንም፤ አያስከብርም። ቤተ ሰቡንም አያኮራም።

በመንፈሳዊውም ሆነ በሥጋዊው ዓለም መልካም ሥራ ማለትም እግዚአብሔርን የሚያስከብር፣ አገርን ወገንን በአጠቃላይ የሰውን ልጅ



«መልካም ስም ከብዙ ባለጠግነት ይበልጣል» /ምሳሌ 22፥1/፡
«መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ በሰው ፊት ይብራ» /ማቴ.5÷16/።

በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ «ስምና ሥራ» የሚሉት ቃላት «መልካም» በሚል ቅጽል ወይም አጎላማሽ ቃል በመገለፃቸው ትርጉማቸው ጎልቶ ይታያል። የሰው ልጅ «አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ» እንደ ተባለው /ዘፍ. 3÷19/ ከተወሰነ ዕድሜ በኋላ ከሥጋዊ ዓለም ይለያል። ለዘሩ፣ ለትውልዱ በዓለም ላይ የሚቀረው ስሙና ሥራው ነው። ስም የሚያስጠራ ሥራ ካልሠራ ግን ሰውዬው ሲያልፍ ወዲያው ይረሳል፡ አስታዋሽ አይኖረውም። ፈጣሪውንም አያስመሰግንም፡ አያስከብርም። ቤተ ሰቡንም አያኮራም።

በመንፈሳዊውም ሆነ በሥጋዊው ዓለም መልካም ሥራ ማለትም እግዚአብሔርን የሚያስከብር፣ አገርን ወገንን በአጠቃላይ የሰውን ልጅ

የሚጠቅም መልካም ዓላማን፣ እምነትን፣ ፍቅርን፣ ሰላምን ወዘተ. የሚያራምድ ሥራ የሠሩ ሰዎች ታሪካቸው፣ ገድላቸው፣ ዜናቸውና ትምህርታቸው ይጻፋል። በልዩ ልዩ መንገድ ይገለፃል።

መነሻችን «የአበው ስምና ሥራ ሲዘከር» የሚል ነውና በመንፈሳዊው ዓለም የሆነውንና የተደረገውን ስንመለከት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጀምሮ በቤተ ክርስቲያን ታሪክና በሌሎች ድርሳናት የአበው ስምና ሥራ ተጽፎ በዝርዝር ተገልፆ እናገኛለን። በበሉይ ኪዳን የአብርሃም፣ የሙሴ፣ የዳዊት ወዘተ. በሐዲስ ኪዳን የሐዋርያትና የተከታዮቻቸው፣ በሌሎች ድርሳናት የጻድቃን የሰማእታት ስምና ሥራ በሰፊው ተዘርዝሮ ይገኛል። ዓላማው ግልጽ ነው። ተተኪው ትውልድ ያለፉትን አበው መልካም ስምና ሥራ አውቆ ከአርአያነታቸውና ከምሳሌነታቸው እንዲማር፣ እንደነሱ እግዚአብሔርን እንዲያከብርና ለሀገሩ ለወገኑ የሚጠቅም መልካም ሥራን እንዲሠራ ለማነሣሣት ነው።

ከዚህ መሠረታዊ ዓላማ በመነሣት የመንፈስ ቅዱስ ልጆችን ዲያቆን መርሻ አለኸኝ በሞተ ሥጋ ተለይተው በዐፀደ ነፍስ የሚገኙ የአበው ኤጲስ ቆጶሳትን፣ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትንና ቅዱሳን ፓትርያርኮችን ታሪክ፣ መንፈሳዊና ሃይማኖታዊ ሥራቸውን፣ ተጋድሎአቸውን የሚያዘክር መጽሐፍ ጽፎ አቅርቧል፤ በመልእክታችን መነሻ ላይ «የአበው ስምና ሥራ ሲዘከር» ያልነው ለዚህ ነው።

በታሪክ እንደ ተመዘገበው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለ1600 ዓመታት በውጭ ሀገር ተወላጅ ጳጳሳትና ሊቃነ ጳጳሳት ስትተዳደር ብትኖርም፣ ከንግሥተ ንግሥታት ዘውዲቱ ዘመነ መንግሥት ከ1921 ዓ.ም ወዲህ ግን ኢትዮጵያውያን ጳጳሳትን ሊቃነ ጳጳሳትንና ቅዱሳን ፓትርያርኮችን በማሾምና በመሾም መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎቷን ስታበረክት ኖራለች። በዚህም ወሰብአ ኢትዮጵያሰ ኢይሤሚ መ ሊቀ እማእምራኒሆሙ /ኢትዮጵያውያን ከሊቃውንቶቻቸው መካከል ኤጲስ ቆጶሳትን አይሹሙ የሚለው የግብፃውያን ገደብ ተነስቷል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በአርቆ ተመልካቹ በዓፄ ኃይለ ሥላሴ ከፍተኛ ጥረትና በአበተዋይና ደጋግ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ጸሎትና ትጋት መንፈሳዊ ብቃትና አስተዳደራዊ ዕውቀት ያላቸው አበው ኢትዮጵያውያን ከኤጲስ ቆጶስነት ወደ ሊቀ ጵጵስና ከሊቀ ጵጵስና ወደ ፓትርያርክነት መዓርግ እንዲሸጋገሩ ተደርገው በአመራራቸው እነሆ ቤተ ክርስቲያናችንን አሁን ካለችበት አስተማማኝ ደረጃ አድርሰዋታል።

እነዚህ ብፁዓን፣ ቅዱሳን አበው እያንዳንዳቸው «ሠናየ ገድለ ተጋደልኩ በድርየኒ ፈጸምኩ ወሃይማኖትየኒ ዐቀብኩ፤ እንከሰ ጽኑሕ ሊተ አክሊለ ጽድቅ ዘየዐስየኒ እግዚአብሔር ... » መልካሙን ገድል ተጋደልሁ፤ ሩጫዬን ጨረስሁ፤ ሃይማኖትንም ጠበቅሁ፤ እንግዲህስ እግዚአብሔር የሚሰጠኝ የጽድቅ አክሊል ይጠብቀኛል /2ኛ ጢሞ. 4÷7 - 8/



በማለት ከምድራዊ ሕይወት ወደ ሰማይ ሕይወት ተሸጋግረው በአፀደ ነፍስ ይገኛሉ። የእነዚህን አባቶች ስምና ሥራ በአንድ ጥራዝ አዘጋጅቶ ለንባብ እንዲበቃ ማድረጉ ጠቀሜታው ብዙና ከፍ ያለ ነው።

በመጀመሪያ ደረጃ ታሪካቸው በአሁኑና በሚመጣው ትውልድ እንዲታወቅ ያደርጋል። ዛሬ «ዜና አበው፣ ሃይማኖተ አበው፣ ገድለ ሐዋርያት፣ ገድለ ሰማዕታት» እያልን የምንማርባቸውና የምናስተምርባቸው መጻሕፍት የሚያገለግሉን ተጽፈው ስለቆዩን ነው። በሁለተኛ ደረጃ የቤተ ክርስቲያናችንን የጽሑፍ እንቅስቃሴ ያጠናክራል፤ ወደ ፊትም ያራምዳል። በሦስተኛ ደረጃ ጥናትና ምርምር በቤተ ክርስቲያናችን ጸሐፊዎች ዘንድ እንዲስፋፋ ያደርጋል።

ስለዚህ «የጻድቅ መታሰቢያ ለዘላለም ይኖራል» /መዝ. 111 ÷ 6/ እንደ ተባለው ወደ ዘላለም ዕረፍት የተሸጋገሩት የጻድቃን አበው ኤጲስ ቆጶሳት፣ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ቅዱሳን ፓትርያርኮች ዜና ሕይወትና ዕረፍት በአንድ መጽሐፍ ተሰብስቦ መቅረቡ በጣም የሚደገፍ ቅዱስ ተግባር ነውና ጸሐፊው በብዙ ድካም አዘጋጅቶ ስላቀረበ «እግዚአብሔር ይባርክህ ይቀድስህ» እንላለን። አንባብያንም ዝግጅቱን በማንበብ ከአባቶች ሥራና ታሪክ በመማር ለበለጠ ሥራ እንዲነሣሡ፣ ክርስቲያናዊ ሃይማኖታቸውን አጽንተው እንዲይዙ መልእክታችንን እናስተላልፋለን። አምላከ ቅዱሳን እግዚአብሔር ከብፁዓን፣ ቅዱሳን አባቶቻችን ረድኤት ያሳትፈን።

አባ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ

ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት

# ምስጋና

ይህን የብፁዓን አባቶቻችንን ዜና ሕይወት የሚያትት የመጀመሪያ ክፍል መጽሐፍ ከዓመት በፊት ለማዘጋጀት ሳስብ በመጀመሪያ ያማከርኳቸው ነፍሳቸውን በገነት ያኑርልንና ባለፈው ዓመት በሚያሳዝን ድንገተኛ ሁኔታ በሞት የተለዩንን ታላቅ አባት ብፁዕ አቡነ ማቴዎስን ነበር። ብፁዕነታቸው በተለመደው ርኃታ የተመላበት የማዳመጥ ጥበባቸው እሳቤን ከተረዱ በኋላ ያሰብኩትን ሥራ ሙሉ በሙሉ እንደ ሚቀበሉት፣ ለተግባራዊነቱም ለምጠይቃቸው እንዳንድ ታሪካዊ ነጥቦች እስከ ሚያውቁት ድረስ መልስ በመስጠት ከጎኔ እንደ ሚቆሙ ገልጸው ምስጋናን ከቡራኬ ጋር ቸሩኝ። ብፁዕነታቸው ምንም እንኳን ከብዙ ድካምና ምርምር እንዲሁም ውይይት በኋላ ዛሬ ለዚህ የበቃውን ይህን መጽሐፍ ጥቂት የመጨረሻ የሕይወት ዘመናቸውን በዝምታ ካሳለፉባት ቤታቸው ሔጄ አበርክቼላቸው፤ የመከሩኝ ምክር ተግባራዊ መሆኑን በማየት የማይጠገበውን ምርቃታቸውንና ጸሎታቸውን ለማግኘት ባልታደልም፤ የአባታዊ ምክራቸውን ፍሬ በሀጸደ ነፍስ ከሚኖሩበት ዓለም ሆነው እንደ ሚያዩልኝ በማመን የልጅነት ምስጋናዬን በታላቅ እክብሮት እቀርባለሁ።

ይህ መጽሐፍ ሕይወታቸውን በሙሉ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በመስጠት የኖሩ፤ በመጨረሻም ለታላቁ የቤተ ክርስቲያን ሥልጣን በመብቃት ለቅዱስ ወንጌል በመላ ሀገሪቱ መዳረስ፣ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መጠበቅ ደፋ ቀና በማለት ሩጫቸውን እየጨረሱ ያለፉ ብፁዓን አባቶችን ዜና ሕይወት የሚያቀርብ በመሆኑ በአንድ ቦታ ተወስኖ የሚሠራ አልነበረም። በመሆኑም ከበርካታ አባቶች እና ወንድሞች ጋር በእያንዳንዱ አባት ዙሪያ ውይይት አድርጌያለሁ። በዚህ ረገድ ሐሳቤን በመረዳት ብዙ የቤተ ክርስቲያናችን አባቶችና ደቀ መዛሙርት የሚያውቁትን ታሪክ በመተረክ፣ የጽሑፍ ማስረጃዎችን በመስጠትና የጻፍኩትን በመተቸት ከፍተኛ ርዳታ አድርገውልኛል። በስዚህ ዝግጅቴን በመደገፍ ለተባበሩኝ ሁሉ ከፍተኛ ምስጋናዬን እቀርባለሁ። በተለይ በቃላት ውስጥ የፊደላትን ኹነኛ ቦታ፤ በሀረፍተ ነገሮችም ውስጥ የቃላትን አገባብና ትርጉም በእጅጉ በመጠንቀቁ ለወጣት ጸሐፍያን አርአያ የሚሆነን ሊቀ ትጉኃን ኃይለ ጊዮርጊስ ዳኜ የመጽሐፉን ረቂቅ በጥንቃቄ በማንበብ፣ በረጅም የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቱ በዚህ መጽሐፍ ዜና ሕይወታቸው የቀረበላቸውን አባቶች በቅርብ የሚያውቀውንና የሰማውን ለጽሑፍ በሚያመች መልኩ በመንገር፣ እንዲሁም የብፁዓን አባቶችን ፎቶ ግራፎች በማፈላለግ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ስላደረገ

ዜና ጳጳሳት ኢትዮጵያውያን

ክፍ ያለ ምስጋናዬን እቀርባለሁ። እግዚአብሔር ዕድሜውን አርዝሞ የምንጠቀምበት ያድርግልን። እንደዚሁም በአባቶች ሕይወት ዙሪያ የጠየኳቸውን ሁሉ በመመለስ ለተራዱኝ ሊቀ መዘምራን መልከ ጼዴቅ፣ ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታየ፣ መምህር ታዬ አብርሃም፣ ቀሲስ ጌታቸው ደጀኔ፣ መምህር ዓሥራት ደስታ፣ አቶ አብርሃ ገ/ሕይወት፣ አቶ ገ/መስቀል ዲሜጥሮስ የቤተ ክርስቲያን አምላክ ዋጋቸውን ይክፈልልኝ እላለሁ። የመጽሐፉን ረቂቅ በኮምፒዩተር በመጻፍ የተባበሩኝ ወ/ት ርብቃ ኃ/ማርያም፣ ወ/ት ጽዮንና በተለይ በመጀመሪያዎቹ ወራት ረቂቁን በማረም እብሮኝ የደከመው አቶ አሉላ ጥላሁን ውለታቸውን አልረሳውም።

የዚህ መጽሐፍ ጥንካሬ መሠረቱ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሊቃውንት ጉባኤ በሚገባ ታርሞና ተስተካክሎ መፈቀዱ ነው። የጉባኤው አባላት አባቶቼ መጽሐፉን በማረም ከጠቀሙኝ ባልተናነሰ በሚያርሙባቸው ጊዜያት አልፎ አልፎ በመካከላቸው በመገኘት የማስተዋልን፣ ያለመሰልቸትንና በአንድ ጉዳይ ላይ በቂ ጊዜ ሰጥቶ በመወያየት የተሻለውን የመያዝን አስፈላጊነት በሚገባ ተምሬያለሁ። የሊቃውንት ጉባኤ አባላት አባቶቼ ላደረጉልኝ ትብብር ሁሉ አመሰግናቸዋለሁ። ሌሎች ወንድሞቼም እንደኔ ቢጠቀሙባቸው መልካም ነው እላለሁ።

የመጽሐፉ ዝግጅት ከተጠናቀቀ በኋላ ከእያንዳንዱ አባት የሕይወት ታሪክ ጋር ፎቶ ግራፍ ለማውጣት እንድችል በጠየኩት ጊዜ ሁሉ ከጎኔ ሆኖ ለተባበረኝ ወንድሜ አቶ ሙሉጌታ በቀለ አምላክ እበው ዋጋውን ይክፈለው።

በመጨረሻም በተለመደው ደገኛ ተግባሯ ሥራው ከተጀመረ አንሥቶ ከጎኔ ሳትለይ ስታበረታታኝ የነበረችዋን ባለቤቴን ወ/ሮ ሉሊት መኩንንን በእጅጉ ላመስግናት እወዳለሁ።

ከላይ በጠቀስኳቸው አባቶቼ፣ ወንድሞቼና እኅቶቼ ጥረት የመጨረሻው ምዕራፍ የደረሰው የዚህ መጽሐፍ ዝግጅት ሩቅ ሀገር ባለው ወንድሜ ወልደ ትንሣኤ /በትውልዱ ኢትዮጵያዊ አይደለም/ የገንዘብ ድጋፍ ለኅትመት ባይበቃ ኖሮ እኔም ለማመስገን ፤ እነሱም ለመመስገን ባልበቁ ነበር። ከአንድ አብራክ የወጡ ወንድማማቾች ሊረዳዱ በተቸገሩበት በዚህ ወቅት በጥቂት ቀናት ትውውቅ ምኞቴን ተረድቶ በፍጹም ፈቃደኝነት የመጽሐፉን የኅትመት ወጭ በመሸፈን ከእኔ እልፎ ቤተ ክርስቲያናችንን የረዳውን ይህንን ወንድሜን በእጅጉ አመሰግነዋለሁ። እግዚአብሔር ከውጭ ወደ ቤቱ እንዳስገባው በቤቱ አቆይቶ ለመንግሥቱ ያብቃው።

*ዲ/ን መርሻ አለኸኝ*

# ማውጫ

የአዘጋጁ ማስታወሻ ........................................................ 11

ቅድመ ምዕራፍ

አባ ሰላማ «ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዘኵላ ኢትዮጵያ»... 14

ምዕራፍ አንድ

1.ማዕዶተ ጵጵስና ........................................................ 19

ምዕራፍ ሁለት

2. ዜና ፓትርያርኮች ........................................................ 41
   2.1. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ /1884 - 1963 ዓ.ም./ ...... 41
   2.2. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ካልአይ ፓትርያርክ /1902 - 1971 ዓ.ም./......... 50
   2.3. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሣልሳይ ፓትርያርክ /1910 - 1980 ዓ.ም./....... 61

ምዕራፍ ሦስት

3. ዜና ጳጳሳት
   3.1. ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ቀዳማዊ /1875 - 1928 ዓ.ም/.................................. 72
   3.2 ብፁዕ አቡነ አብርሃም ቀዳማዊ /1861 - 1931 ዓ.ም/ ................................ 81
   3.3. ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ቀዳማዊ /? - 1929 ዓ.ም/ ........................................ 87
   3.4. ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ ቀዳማዊ /1871 - 1947 ዓ.ም/ .................................. 94
   3.5. ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ቀዳማዊ /1868 - 1925 ዓ.ም/....................................... 100
   3.6 ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ቀዳማዊ /1875 - 1948 ዓ.ም/ .................................... 104
   3.7. ብፁዕ አቡነ ሰላማ ቀዳማዊ /1865 - 1935 ዓ.ም/....................................... 109
   3.8. ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ ቀዳማዊ /1862 - 1939 ዓ.ም/...................................... 112
   3.9. ብፁዕ አቡነ ሉቃስ ቀዳማይ /1837 - 1940/............................................... 115
   3.10. ብፁዕ አቡነ ማትያስ ቀዳማይ /1860 - ?/.................................................. 118
   3.11. ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ቀዳማይ /1878 - ? /................................................ 121
   3.12. ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ ቀዳማይ /1888 - 1980 ዓ.ም/...................................... 127
   3.13. ብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስ ቀዳማይ /1889 - 1970 ዓ.ም/.................................. 132
   3.14. ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ ቀዳማይ /1888 - 1957 ዓ.ም/..................................... 136
   3.15. ብፁዕ አቡነ ማርቆስ ቀዳማይ /1889 - 1971 ዓ.ም/ ..................................... 139
   3.16. ብፁዕ አቡነ ገብርኤል ቀዳማይ /1882 - 1958 ዓ.ም/ .................................. 144
   3.17. ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ቀዳማይ /1872 - 1958 ዓ.ም/ ................................ 148
   3.18. ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ ቀዳማይ /1888 - 1974ዓ.ም/ ....................................... 152
   3.19. ብፁዕ አቡነ ሉቃስ ካልአይ /1900 - 1900 ዓ.ም/......................................... 158
   3.20. ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ካልአይ /1885 - 1959 ዓ.ም/ ...................................... 165
   3.21. ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ካልአይ /18887 - 1983 ዓ.ም/ .................................... 168
   3.22. ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ካልአይ /1901 - 1961 ዓ.ም/ ...................................... 176
   3.23. ብፁዕ አቡነ መርቆሬዎስ ቀዳማይ /1888 - 1968 ዓ.ም/................................... 183

3.24. ብፁዕ አቡነ ሰላማ ካልአይ
/1898 - 1970 ዓ.ም/ .................................. 186
3.25. ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ ቀዳማይ
/1892 - 1979 ዓ.ም/ .................................. 190
3.26. ብፁዕ አቡነ አብርሃም ካልአይ
/1905 - 1995 ዓ.ም/ .................................. 195
3.27. ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ሣልሳይ
/1903 - 1995 ዓ.ም/ .................................. 199
3.28. ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ ቀዳማይ
/191፤ - 1991 ዓ.ም/ .................................. 204
3.29. ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ ቀዳማይ
/1878 - 1953/ .......................................... 209
3.30. ብፁዕ አቡነ እንድርያስ ቀዳማይ
/1906 - 1987 ዓ.ም/ .................................. 212
3.31. ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ሣልሳይ
/1904 - 1991 ዓ.ም/ .................................. 219
3.32. ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል ቀዳማይ
/1924 - 1967 ዓ.ም/ .................................. 223
3.33. ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ ካልአይ
/1896 - 1975 ዓ.ም / .................................. 226
3.34. ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ ካልአይ
/1919 - 1996 ዓ.ም/.................................... 229
3.35. ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ሣልሳይ
/1921 - 1993 ዓ.ም/ .................................. 235
3.36. ብፁዕ አቡነ ሰላማ ሣልሳይ
/1931 - 1996 ዓ.ም/ .................................. 239
3.37. ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልአይ
/1932 - 1982 ዓ.ም/ .................................. 245
3.38. ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል ካልአይ
/1922 - 1993 ዓ.ም/.................................... 251
3.39. ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ ካልአይ
/1921 - 1981 ዓ.ም/.................................... 256

ዜና ጳጳሳት ኢትዮጵያውያን

3.40. ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ ካልአይ
/1920 - 1981 ዓ.ም/ .................................. 260
3.41. ብፁዕ አቡነ በርናባስ ቀዳማዊ
/1917 - 1980 ዓ.ም/ .................................. 264
3.42. ብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ ቀዳማይ
/1911 - 1989 ዓ.ም/.................................... 268
3.43. ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ
/1917 - 1996 ዓ.ም/ .................................. 272
3.44. ብፁዕ አቡነ ተክለ ሃይማኖት
/1938 - 1983 ዓ.ም/ .................................. 275
3.45. ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ ሣልሳይ
/1903 - 1995 ዓ.ም/ .................................. 278
3.46. ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ሣልሳይ
/1936 - 1990 ዓ.ም/ .................................. 281
3.47. ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ ካልአይ
/1938 - 1991 ዓ.ም/ .................................. 285
3.48. ብፁዕ አቡነ ኤልያስ ቀዳማይ
/1933 - 1991 ዓ.ም/.................................... 288
3.49. ብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ ካልአይ
/1932 - 1992 ዓ.ም/.................................... 292
3.50. ብፁዕ አቡነ ሉቃስ ሣልሳይ
/1937 - 1995 ዓ.ም/.................................... 295
ምዕራፍ አራት
4. አባሪ ......................................................................... 299

# የአዘጋጁ ማስታወሻ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ተሹሞ ከመጣው የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ጳጳስ አባ ሰላማ ጀምሮ ለ 1600 ዓመታት ከግብፅ ተቀብተው በሚመጡ ግብፃውያን ጳጳሳት እና ሊቃነ ጳጳሳት ስትመራ ቆይታለች። ይሁን እንጂ በ11ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በንጉሥ ሐርቤ ገብረ ማርያም /1117 - 1157 ዓ.ም/ የተጀመረውና ቤተ ክርስቲያኗ በዕውቀት ከአብራኳ በሚገኙ ልጆቿ ትመራ የሚለው ክርክር ከዘጠኝ መቶ ዓመታት በኋላ በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ውጤት አግኝቶ ግንቦት 21 ቀን 1921 ዓ.ም የመጀመሪያዎቹ አራት ኢትዮጵያውያን አበው ሊቃውንት መዓርገ ጵጵስናን ለማግኘት ቻሉ። ምንም እንኳን በኢትዮጵያ በኩል ጥረቱ ቀላል የሚባል ባይሆንም ከዓመታት በኋላ ደግሞ ጥር 6 ቀን 1942 ዓ.ም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሊቀ ጵጵስናውንም መንበር ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን ተረክባ የራሷን ልጅ አስቀመጠች። በመጨረሻም የተቀዳጀችው ነጻነት ፍጹም ሊሆን በኔ 21 ቀን 1951 ዓ.ም የራሷን መንበረ ፓትርያርክ አደላድላ የምታውቀውንና የሚያውቃትን ልጇን ሠየመች።

መጽሐፍ ቅዱሳዊት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የዘመናት ትግሏ ውጤታማ ሆኖ የመጀመሪያዎቹ ኢትዮጵያውያን አባቶች ጳጳሳት ተብለው ከተሾሙበት ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ ጊዜያት ይበቃሉ ያለቻቸውን አበው እየመረጠች በመሾም ወንጌልን የመስበክ ደገኛ ተግባሯን ስትወጣ ቆይታለች። አሁንም በብቃት በመወጣት ላይ ትገኛለች። ወደ ፊትም ትቀጥላለች።

የዚህ መጽሐፍ ዓላማ ቤተ ክርስቲያናችን ራሷን በራሷ የማስተዳደር ነጻነት ከተቀዳጀችበት ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ ጊዜያት በጵጵስናና ሊቀ ጵጵስና ከዚያም ከፍ ባለ በፓትርያርክነት ተሹመው፣ አስቀድሞ የመረጣቸው አምላክ የፈቀደላቸውን ዕድሜ ያህል አገልግሎታቸውን በትጋት ሰጥተው ሐዋርያው «መልካሙን ገድል ተጋድዬአለሁ ፥ ሩጫውን ጨርሼአለሁ ፥ ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ ፥ ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል» /2 ጢሞ 4 ፥ 7-8/ ባለው መሠረት መልካሙን ገድል ተጋድለው ያለፉትን ጳጳሳት፣ ሊቃነ ጳጳሳትና ፓትርያርኮች ዜና ሕይወት ማዘከር ነው። በሌላው ዓለም እንኳን ብፁዓን ተብለው በከፍተኛ መንፈሳዊ መንበር በመቀመጥ ሲያገለግሉ የቆዩ አባቶች ቀርቶ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ በሚያመዝን ሙያ ተሠማርተው ያለፉ ሰዎች የሕይወት ታሪክ በጥንቃቄና በትጋት በሚጻፍበት በዚህ ዘመን ቤተ ክርስቲያናችን በተለያዩ የአገልግሎት ዘርፎች ተሠማርተው ያለፉ ልጆቿን ዜና ሕይወት ጽፎ በማቆየቱ ረገድ ገድል

በተሰኘው ነባር የሥነ ጽሑፍ ሀብቷ የጸፈችላቸው ቅዱሳን ልጆቿ እንዳሉ ሆነው ብዙ የተራመዱች አትመስልም።

ምንም እንኳን የሁሉም ተመዝግቦ ይገኛል ባይባልም፤ በአባቶች የሕይወት ታሪክ ዙሪያ በሚያርፉበት ጊዜ የቤተ ክርስቲያኗ ልሳናት በሆኑ የኅትመት ውጤቶችና የዓርብ ቀን መታሰቢያቸውን በማስመልከት በሚዘጋጁ መጽሔቶችና በራሪ ጽሑፎች ላይ የአንዳንድ አባቶች ዜና ሕይወት በአጭር በአጭሩ ተዘግቦ ይገኛል። እነዚህ መዛግብት በዚህ መጽሐፍ ዝግጅት ወቅት በምንጭነት ቀላል የማይባል አስተዋጽኦ አበርክተዋል። ለዚህም ጊዜው በሚጠይቀው መሠረት ግልጋሎት ላይ የዋሉት መዛግብት በመጽሐፉ መጨረሻ ላይ ተዘርዝረዋል። ይሁን እንጂ የዚህ መጽሐፍ ዓላማ በተበታተነ ሁኔታ በኅትመቶቹ ከተሠሩት ሰፋ ያለና ዝግጅቱም በመጽሐፍ መልክ እንደ መሆኑ በጋዜጦቹና በመጽሔቶቹ ከተገለጠው የበለጠ በርካታ መረጃዎች እንዲካተቱበት ሆኗል። ይኸውም ከተለያዩ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት፣ የአባቶች የቅርብ ዘመዶችና ለቤተ ክርስቲያኗ ቅርበት ካላቸው ምሁራን ጋር ከተደረጉ ውይይቶች እንዲሁም ከበርካታ ሰነዶች የተገኙ መረጃዎች በመጽሐፉ እንዲካተቱ በመደረጉ ነው። በዓላማም ረገድ ይህ መጽሐፍ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን አገልግለው ያለፉ ብፁዓን አባቶችን ዜና ሕይወት ከማስተዋወቅ ባለፈ በቤተ ክርስቲያኗ የጵጵስና ታሪክ ከየት ተነሥቶ የት እንደ ደረሰ፣ ቤተ ክርስቲያኗ ለረጅም ዘመናት ተነፍጓት የቆየውን ራሷን በራሷ ልጆች የማስተዳደር መብት እንድትጎናጸፍ የተደረጉ ትግሎች፣ በዚህ ረገድ ተመዝግበው የሚገኙ መዛግብት፣ መብቷን ከተጎናጸፈች በኋላም በዚሁ በጵጵስና ሹመት ዙሪያ የተከሰቱ አንዳንድ ውጫዊና ውስጣዊ ችግሮች፣ የተወሰዱ የመፍትሔ ርምጃዎች እና የመሳሰሉትን ታሪካዊ እውነታዎች በማቅረብ ዘርፉን በሚመለከት በኢትዮጵያና ቤተ ክርስቲያኗ ታሪክ ጥናት ለተሰማሩ ምሁራን መጠነኛ መረጃ ይሰጣል ተብሎ ታስቧል።

ከመጽሐፉ ርእስ ለመረዳት እንደ ሚቻለው ይህ መጽሐፍ የርእስ ጉዳዩ የመጀመሪያ ክፍል ነው። ቀጣዩ ክፍል አሁን በጸሎታቸው፣ በቡራኬያቸውና በትምህርታቸው እያገለገሉን ያሉ አባቶቻችን ዜና ሕይወት ነው። ምንም እንኳን እኔ እንዲህ ነኝ ብሎ ስለ ራስ ደግ ደጉን መተረክ አባቶቻችን የሚሹት ባይሆንም ሁለተኛው ክፍል ከዚህ በተሻለ ሁኔታ ሰፋ ያለና መረጃ ጠገብ እንደ ሚሆን ተስፋ አለኝ። ያድርስን። የአባቶቻችን አምላክ እንደ ፈቀደ ይህን የመጀመሪያ ክፍልም ሆነ ወደ ፊት ይታተማል ብዬ የማስበውን ሁለተኛውን ክፍል ወደ እንግሊዝኛ ተርጉሜ ምዕራባውያን ስለ አባቶቻችን እንዲያነቡ አደርጋለሁ የሚል ተስፋ አለኝ።



መጽሐፉ አራት ምዕራፎች አሉት። የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከግብፅ ተሹመው በሚመጡ ግብፃውያን አባቶች መመራቷ እቁሞ ከራሷ ሊቃውንት በተሾሙ አባቶች እንድትመራ፣ ምእመናኗም ቋንቋዋን፣ ትምህርቷንና ባሕሏን በሚገባ በሚያውቁ ሊቃውንት እንዲማሩ ከ11ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ የተለያዩ ነገሥታት ያደረጉትን ጥረትና በመጨረሻም እንዴት ሙሉ በሙሉ ነጻነቷን እንደ ተቀዳጀች የቀረበበት ምዕራፍ ነው። ሁለተኛው ደግሞ በተከታታይ በፓትርያርክነት ተሹመው በመልካም አስተዳደራቸው ቤተ ክርስቲያኗን አገልግለው ያረፉ ሦስት ቅዱሳን አባቶች ዜና ሕይወት የቀረበበት ነው። ሦስተኛው የመጽሐፉ ምዕራፍ ግንቦት 1 ቀን 1921 ዓ.ም ከተሾሙት አራት ብፁዓን አባቶች ጀምሮ በቅርቡ ከዚህ ዓለም በሞት እስከ ተለዩት ብፁዕ አቡነ ሰላማ ድረስ ቤተ ክርስቲያናቸውን አገልግለው ያለፉትን 50 ብፁዓን አባቶች ዜና ሕይወት የቀረበበት ነው። በዚህ ምዕራፍ ፋሺስት ኢጣልያ ሕዝቡን የያዙ መስሎት «ኢትዮጵያውያን የራሳቸውን ጳጳሳት መሾም ይችላሉ ብሎ» በዋጀ ባስነገረ ጊዜ ከየክፍሉ በተሰባሰቡ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ምርጫ፤ በነበሩት አባቶች የተሾሙትን አንዳንድ አባቶች የሕይወት ታሪክም ለማካተት ተሞክሯል። የእነዚህ አባቶች ዜና ሕይወት የተካተተበት ምክንያት ነጻነት ከተመለሰ በኋላ ምንም እንኳን በተለይ ከግብጽ ቤተ ክርስቲያን ጋር የነበረውን ግንኙነት ላለማበላሸት ለጊዜው ከአገልግሎት ታግደው ቢቆዩም ወደ ኋላ ብዙዎቹ ሥልጣናቸው ስለተመለሰላቸውና የመጽሐፉ አዘጋጅ በጣልያን ጊዜ የነበረው ሹመት ትክክለኛ ወይም ቀኖናዊ ነበር ብሎ ስለሚያምን ነው። ታሪካቸው ያልተካተተላቸው አባቶች የቀሩት ምንጭ ስለጠፋ ነው። የብፁዓን አባቶች ዜና ሕይወት በዚህ መጽሐፍ የቀረበው በተሾሙበት ዘመን ቅደም ተከተል ነው።

ሁለት ዓመታት በወሰደው የመጽሐፉ ዝግጅት ወቅት የተገኙት መረጃዎች ተቀናብረው ይህ መጽሐፍ ለዚህ ቢበቃም በሒደት ሊገኙ ያልቻሉ መረጃዎች ሊኖሩ እንደ ሚችሉ አይጠረጠርም። በመሆኑም የመጽሐፉ አንባቢዎች ያልተካተቱ የሚሏቸው መረጃዎች ካሉ ቢልኩልኝ ወደ ፊት መጽሐፉ እንደ ገና ሲታተም ለማካተት ይሞከራል። ይህ ይሆን ዘንድ በመጽሐፉ ዜና ሕይወታቸውን ሳዘከርላቸው የሞከርኳቸውን ብፁዓን አበው በቅርብ የሚያውቁና በሕይወታቸው ዙሪያ የተጻፉ መረጃዎች ያሏቸው አንባብያን በመጽሐፉ መጀመሪያ በተገለጠው አድራሻ እንዲልኩልኝ ከአክብሮት ጋራ እጠይቃለሁ።

*አዘጋጁ*

# ቅድመ ምዕራፍ

## አባ ሰላማ

## «ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዘኵላ ኢትዮጵያ»

ሀገራችን ኢትዮጵያ ምንም እንኳን ክርስትናን የተቀበለችው ባኮስ /አቤሳክ/ በተባለው የኢትዮጵያ ንግሥት የህንደኬ በጅሮንድ አማካኝነት በ1ኛው መ.ክ.ዘ ቢሆንም እስከ 4ኛው መ.ክ.ዘ. ድረስ የኤጲስ ቆጶስነት መንበር አላገኘችም ነበር። ከ4ኛው መ.ክ.ዘ. አጋማሽ እስከ 5ኛው መ.ክ.ዘ. መጀመሪያ ድረስ የኖረው ሩፊኖስ የተባለ የቤተ ክርስቲያን የታሪክ ጸሐፊ ይህንን ታሪክ እንደ ሚከተለው ዘግቧል።

ሜሮጵዮስ የተባለ አንድ ጢሮሳዊ ክርስቲያን ነጋዴ /ፈላስፋም ነበረ የሚሉ አሉ/ ፍሬምናጦስና ኢዴስዮስ የተባሉ ዘመዶቹን በማስከተል ከሀገሩ ተነሥቶ ወደ ሕንድ አቅጣጫ በጀልባ ጉዞውን ጀመረ። በጉዞውም ወደ አፍሪካ የባሕር ጠረፍ በመምጣት በቀይ ባሕር ወደብ ውኃ ለመጠጣትና እግረ መንገዱንም ሀገር ለማየት ጀልባውን ጠረፍ ላይ አቆመ። ነገር ግን እሱ እንዳሰበው ሳይሆን በአካባቢው ይኖሩ የነበሩ ሰዎች በጀልባቸው ላይ አደጋ ጥለው እራሱንና የጀልባዋን ቀዛፊዎች እዚያው ገድለው ሀብታቸውን ዘረፉቸው።

ባላሰቡት ሁኔታ ከሜሮጵዮስ የተለዩት ወጣቶቹ ወንድማማቾች ፍሬምናጦስና ኢዴስዮስ ቋንቋውንና ባሕሉን በማያውቁት ሀገር ብቻቸውን በመቅረታቸው እያዘኑና እያለቀሱ ከዛፍ ሥር ተቀምጠው ይጸልዩ ጀመር። እነዚህን ወጣቶች በማየታቸው የተገረሙት መንገደኞች ከዚህ ቦታ አንሥተው በወቅቱ የአክሱም ንጉሥ ለነበረው ታዜር «ይኸውና ምርኮ አመጣንልህ» በማለት አስረከቧቸው።

ንጉሡም ወጣቶቹ በቤተ መንግሥቱ ውስጥ ያድጉ ዘንድ ፈቃዱ ሆነና ከልጆቹ አብርሃና አጽብሐ ጋር አንድ ላይ ማደግ ጀመሩ። ከዓመታት በኋላ በአእምሮ መብሰላቸውን በጥበብም ማደጋቸውን የተመለከተው ንጉሥ ታዜር ፍሬምናጦስን በጅሮንድ ኢዴዮስን ደግሞ ጋሻ ጃግሬው አድርጎ ሾማቸው። ወጣቶቹም ሹመቱን በመቀበል በቤተ መንግሥቱ በማገልገል ላይ እንዳሉ



ንጉሡ ሀረፈ። በዚህ ጊዜ ግሪካውያኑ ወጣቶች ነፃ ወጣን በማለት ወደ ሀገራቸው ሊሔዱ ተነሡ። ነገር ግን መንግሥቱን በሞግዚትነት የተረከበችው ንግሥት አሕየዋ /ሶፊያ/ ልጆቿ ኢዛናና ሳይዛና /በኋላ አብርሃና አጽብሐ/ አድገው ዙፋኑን እስኪረከቡዋት ድረስ በአስተዳደር እንዲረዱዋት ለመኗቸው። እነሱም ጥያቄዋን ተቀብለው ጉዞዋቸውን በመተው በዚያው በቤተ መንግሥቱ በአማካሪነት ሲያገለግሉዋት ቆዩ።

ከዓመታት በኋላ ታናሽ ወንድሙ ወደ ሀገሩ በመሔዱ ብቻውን የቀረው ፍሬምናጦስ ለክርስትና እምነቱ ቀናኢ ስለነበር አስቀድሞ በኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ተሰብኮ በአክሱምና አካባቢዋ የነበረው የክርስትና እምነት የሚስፋፋበትን መንገድ ዘወትር ያስብ ነበር። ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ሃይማኖት ብቻ እንጂ ክህነት፣ ቁርባን ወዘተ. የመሳሰሉትን ምሥጢራት የሚፈጽምላቸው ካህናትን የሚሾምላቸው ኤጲስ ቆጶስ በለሌላቸው ያዝኑ እንደነበር ተመለከተ። ይህን የሕዝቡን ሐዘን ለማቆምም የበኩሉን ጥረት ለማድረግ ወሰኖ ጉዳዩን የአባታቸውን መንግሥት ለተረከቡት አብርሃና አጽብሐ ማስረዳቱን ቀጠለ።

ነገሥታቱም ጉዳዩን ሙሉ በሙሉ በመቀበል ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ ሲያሰላስሉ በፍሬምናጦስ ምክር ከአንድ ውሳኔ ላይ ይደርሳሉ። እነሱም ፍሬምናጦስን የእኛን ቋንቋና ባህል የእነሱንም ቋንቋና ባህል ከአንተ ሌላ የሚያውቅ የለምና አንተ ወደ እስክንድርያ ሄደኽ ክህነትንና ቁርባንን አምጣልን ብለው እሱን ወደ እስክንድርያ ሰደዱት። ፍሬምናጦስ ወደ እስክንድርያ የተላከው እንደ ኢትዮጵያዊ ሆኖ ነው እንጂ፣ ትውልድ ሀገሩን ወክሎ እንዳልተላከ መገንዘብ ይገባል።

ፍሬምናጦስ እስክንድርያ የደረሰው እለ እስክንድሮስ አትናቴዎስን አስከትሎ በጉባኤ ኒቅያ ለመካፈል በሔደበት ወቅት ነበረና እስኪመለሱ ድረስ በዚያው ትምህርተ ቤተ ክርስቲያንን እየተማረ በትዕግስት መጠበቅ ግድ ሆነበት።

እለ እስክንድሮስ በጉባዔ ኒቅያ በአትናቴዎስ አፈ ጉባዔነት አርዮስን ረትቶ ከተመለሰ በኋላ ወዲያው ስላረፈ በመንበሩ አትናቴዎስ ተተካ። ፍሬምናጦስም የተላከበትን ሀቢይ ጉዳይ ለሐዋርያዊው ቅዱስ አትናቴዎስ አቀረበ። አትናቴዎስ ስለ ኢትዮጵያውያን ሃይማኖት በሚገባ ከተረዳ በኋላ ለፍሬምናጦስ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን አስተምሮ «ኤጲስ ቆጶስ ዘአክሱም ወዘኵላ ኢትዮጵያ» ብሎ በትንባዓትና በአንብሮተ እድ ሹሞ ላከው።ፍሬምናጦስ ጵጵስናውን ተቀብሎ ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሰ በኋላ፡-

- የወንጌልን ትምህርት በስፋት ለሕዝቡ የሚያዳርሱ፣ የሚያጠምቁና የሚያቁርቡ ካህናትንና ዲያቆናትን ሾመ።
- በአብርሃ አጽብሐ አማካኝነት አያሌ አብያተ ክርስቲያናትን አሳነፀ።
- በዘመኑ የኢትዮጵያ ግዛት ወደ ነበሩት ኑብያ፣ አኑኖ እና መርዌ አምስት ቆምሳትን በመላክ ትምህርተ ወንጌል እንዲሰበክ፣ ቤተ ክርስቲያን እንድትስፋፋ አደረገ።
- ቅዱሳት መጻሕፍትን ከሱርስት፣ ከዕብራይስጥና ከግሪክ ወደ ግእዝ እንዲተረጎሙ አደረገ።
- የሳባውያንን የፊደል አቀማመጥ በመለወጥ ከግራ ወደ ቀኝ የመጻፍንና የማንበብን ዘዴ ያስተማረው እርሱ ነው።

በዚህም መሠረት ክርስትና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሃይማኖት ሆኖ በ350 ዓ.ም እንዲታወጅ አድርጓል። ኢትዮጵያውያን ይህንን ታላቅ አባት በሃይማኖቱና በምግባሩ ስለወደዱት «አቡነ» /አባታችን/ የሚለውን መዓርግ ለመጀመሪያ ጊዜ የሰጡት ለእርሱ ነው። በብርሃናዊ ሥራውም «ከሣቴ ብርሃን» /ብርሃን ገላጭ/ ብለውታል።

አቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን የተባለው ፍሬምናጦስ በኢትዮጵያ ክርስትና እንዲስፋፋ ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ ከምዕራብ እስከ ምሥራቅ በመውጣትና በመውረድ የሚገባውን ሁሉ ከፈጸመ በኋላ ሐምሌ 26 ቀን ዐረፈ።

ይህ ታላቅ አባት የኢትዮጵያውያን ባለውለታ፣ የወንጌልን ፋና ይበልጥ እንዲበራ ያደረገ፣ መንበረ ጵጵስናን ያስገኘልን፣ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ለኢትዮጵያውያን የወጠነልን እና አያሌ አብያተ ክርስቲያናትን ያስተከለልን ነውና ዘወትር ልናስበው በዓሉንም ልናከብርለት ይገባናል።

ይህ ቅዱስ አባት ቤተ ክርስቲያኑ በሚገኝበት ትግራይ ውስጥ በተንቤን እንዳባ ሰላማ ባንዳንድ ቦታዎች ካልሆነ በቀር በአብዛኛው የሀገራችን ክፍል ዓመታዊ ክብረ በዓሉ እምብዛም ትኩረት አይሰጠውም።

ኤፍ.ጂ. ሆልዊክ የተሰኘ ጸሐፊ እንደ ገለጠው በጥንታዊቷ ሉዩሲያና /Louisiana/ /በዩናይትድ ስቴት ግዛት/ በ1787 ዓ.ም እ.ኤ.አ. የአካባቢው ሰዎች በከፍተኛ ድምቀት የቅዱስ ፍሬምናጦስን በዓል ሲያከብሩ መመልከቱንና እነርሱም ከዚህ ከአፍሪካ በባርነት የሄዱ ጥቁሮች መሆናቸውን ማረጋገጡን ጽፎ ነበር።



አባ ሰላማ የሮማ ቤተ ክርስቲያን በኦክቶበር 27፣ የግሪክ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ በኖቬምበር 30 በዓሉን ሲያከብሩለት የሾመችውና የላከችው የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ግን ፈጽማ ከበዓላት ቀኖናዋ አውጥታዋለች። አቡነ ሰላማ የቀደሰበት በግሪክ ቋንቋ የተጻፈ ቅዳሴና የባረከበት የእጅ መስቀሉ ዛሬም በተድባበ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ይገኛል። የብፁዕ አባታችን ረድኤት አይለየን። አሜን።

በ4ኛው መ.ክ.ዘ. በቅዱስ ፍሬምናጦስ የተጀመረው የእስክንድሪያ ቤተ ክርስቲያን ኤጲስ ቆጳሳትን ሾሞ ወደ ኢትዮጵያ የመላክ ሥልጣን እስከ 20ኛው መ.ክ.ዘ. ቆይቶ 119 የሚሆኑ ግብፃውያን አባቶች ወደ ኢትዮጵያ እየመጡ በሊቀ ጵጵስና ሲያገለግሉ ቆይተዋል። ከቅዱስ ፍሬምናጦስ /አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን/ በኋላ ሥልጣኑን ሙሉ በሙሉ ኢትዮጵያውያን እስከ ሚረከቡ ድረስ ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን እየተሾሙ ወደ አትዮጵያ በመምጣት በሊቀ ጳጳስነት ያገለገሉ ግብፃውያን አባቶች በም ዝርዝር የሚከተለው ነው።

1. አቡነ ሚናስ
2. አቡነ ጴጥሮስ
3. አቡነ ማቴዎስ
4. አቡነ ማርቆስ
5. አቡነ ዮሐንስ
6. አቡነ ገብርኤል
7. አቡነ ዮሐንስ 2ኛ
8. አቡነ ገብርኤል
9. አቡነ ሚናስ 2ኛ
10. አቡነ ሚካኤል
11. አቡነ ይስሐቅ
12. አቡነ ስምዖን
13. አቡነ ጴጥሮስ 2ኛ
14. አቡነ ሚካኤል 2ኛ
15. አቡነ ገብርኤል 3ኛ
16. አቡነ ዮሐንስ 3ኛ
17. አቡነ ሚካኤል 3ኛ
18. አቡነ ሚካኤል 4ኛ
19. አቡነ ስምዖን 2ኛ
20. አቡነ ዮንሐንስ 4ኛ
21. አቡነ ማርቆስ 2ኛ
22. አቡነ አብርሃም
23. አቡነ ቄርሎስ
24. አቡነ ዮሐንስ 5ኛ
25. አቡነ ሚካኤል 5ኛ
26. አቡነ ስምዖን 3ኛ
27. አቡነ ጴጥሮስ 3ኛ
28. አቡነ ማቴዎስ 2ኛ
29. አቡነ ያዕቆብ
30. አቡነ ፊቅጦር
31. አቡነ ቄርሎስ 2ኛ
32. አቡነ ቆዝሞስ
33. አቡነ ዮስጦስ
34. አቡነ ሚካኤል 6ኛ
35. አቡነ ገብርኤል 4ኛ
36. አቡነ ሚካኤል 7ኛ
37. አቡነ ማቴዎስ 3ኛ
38. አቡነ ዮሳብ
39. አቡነ ዮሴፍ
40. አቡነ ቆዝሞስ 2ኛ

41. አቡነ ፊላታዎስ
42. አቡነ ጴጥሮስ 4ኛ
43. አቡነ ዮሐንስ 6ኛ
44. አቡነ ፊቅጦር 2ኛ
45. አቡነ ዮስጦስ 2ኛ
46. አቡነ በርምያ
47. አቡነ ሚካኤል 8ኛ
48. አቡነ ገብርኤል 5ኛ
49. አቡነ ሚናስ 3ኛ
50. አቡነ ዮሐንስ 7ኛ
51. አቡነ ዮሐንስ 8ኛ
52. አቡነ አብርሃም 2ኛ
53. አቡነ ማርቆስ 3ኛ
54. አቡነ መቃርስ
55. አቡነ ሚካኤል 9ኛ
56. አቡነ ማቴዎስ 4ኛ
57. አቡነ ሚካኤል 10ኛ
58. አቡነ ገብርኤል 6ኛ
59. አቡነ ዮሐንስ 9ኛ
60. አቡነ ቄርሎስ 3ኛ
61. አቡነ ሚናስ 4ኛ
62. አቡነ ማቴዎስ 5ኛ
63. አቡነ ሚካኤል 11ኛ
64. አቡነ ገብርኤል 7ኛ
65. አቡነ ማርቆስ 4ኛ
66. አቡነ ገብርኤል 8ኛ
67. አቡነ ማቴዎስ 6ኛ
68. አቡነ ዮሐንስ 10ኛ
69. አቡነ ሚናስ 5ኛ
70. አቡነ ማርቆስ 5ኛ
71. አቡነ ክርስቶዶሉ
72. አቡነ ዘካርያስ
73. አቡነ ፊላታዎስ 2ኛ
74. አቡነ ሱንትዮስ
75. አቡነ ገብርኤል 9ኛ
76. አቡነ ዮሐንስ 11ኛ
77. አቡነ ሚካኤል 12ኛ
78. አቡነ ገብርኤል 10ኛ
79. አቡነ በርተሎሜዎስ
80. አቡነ ማቴዎስ 7ኛ
81. አቡነ ዮሐንስ 12ኛ
82. አቡነ ማርቆስ 6ኛ
83. አቡነ ይስሐቅ 2ኛ
84. አቡነ ክላድያኑ
85. አቡነ ጴጥሮስ 5ኛ
86. አቡነ ማቴዎስ 5ኛ
87. አቡነ ስምዖን 4ኛ
88. አቡነ ዮሳብ 2ኛ
89. አቡነ ሚካኤል 13ኛ
90. አቡነ ማቴዎስ 9ኛ
91. አቡነ ማርቆስ 7ኛ
92. አቡነ ጴጥሮስ 6ኛ
93. አቡነ ስምዖን 5ኛ
94. አቡነ ማርቆስ 8ኛ
95. አቡነ ሚካኤል 14ኛ
96. አቡነ ዮሐንስ 13ኛ
97. አቡነ ክርስቶዶሉ 2ኛ
98. አቡነ ሲኖዶ
99. አቡነ ማርቆስ 9ኛ
100. አቡነ ክርስቶዶሉ 3ኛ
101. አቡነ ዮሐንስ 14ኛ
102. አቡነ ዮሳብ 3ኛ
103. አቡነ መቅርዮስ 2ኛ
104. አቡነ ቄርሎስ 4ኛ
105. አቡነ ሰላማ 2ኛ
106. አቡነ አትናቴዎስ
107. አቡነ ጴጥሮስ 7ኛ
108. አቡነ ማቴዎስ 10ኛ
109. አቡነ ቄርሎስ 5ኛ



# ምዕራፍ አንድ

## ማዕዶተ ጵጵስና[1]

*ወሰብአ ኢትዮጵያ ኢይሢሙ ባዕሌሆሙ ሊቀ ጳጳሳት እማእምራኒሆሙ፤ ወኢበሥምረተ ርእሶሙ። እስመ ጳጳሶሙ ይከውን እምታሕተ እዴሁ ለበዓለ እስክንድርያ ወውእቱ ዘይደልዎ ይሢም ባዕሌሆሙ ሊቀ እምኀቤሁ፡ ዘውእቱ መትሕተ ሊቀ ጳጳሳት።*

*የኢትዮጵያ ሰዎች ከሀዋቂዎቻቸው ወገን፣ በራሳቸውም ፈቃድ ሊቀ ጳጳሳትን ለራሳቸው አይሾሙ። ጳጳሳቸው ከእስክንድርያው በዓለ መንበር ሥልጣን በታች ነውና። ከሊቀ ጳጳሳት በታች የሆነውን ሊቀ ጳጳስ ከእርሱ ወገን ሊሾምላቸው የሚገባውም እርሱ ነው።*

/ፍትሐ ነገሥት፣ አንቀጽ 4፣ ቁጥር 50/

አያሌ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትና በቤተ ክርስቲያኗ ታሪክ ላይ ምርምር ያደረጉ ምሁራን ይህን የፍትሐ ነገሥት አንቀጽ «ቀንበር ማጥበቂያ አንቀጽ» እያሉ ይጠሩታል። ሊቃውንቱ በተለይ የትርጓሜ መጻሕፍት መምህራን ምንም እንኳን አንቀጹ የተካተተበትን ታላቅ የሕግና የሥርዓት መጽሐፍ ተቀብለው በአንድምታ የትርጓሜ ጥበባቸው የረቀቀውን አጉልተው፣ የራቀውን አቅርበው በማመስጠር ቢያስተምሩትም ከተጠቀሰው አንቀጽ ላይ ሲደርሱ አንድም ብለው ሳይተረጉሙት ያልፉ ነበር። ነገር ግን፤ ምንም እንኳን በሙሉ ልብ «ግብፃውያኑ በስርዋጽ ያስገቡት ተንኮል ያዘለ አንቀጽ ነው» ብለው በድፍረት ባይተቹትም፤ አልፎ አልፎ «ይህ እንኳን ስሕተት ይመስላል» እያሉ የአንቀጹን የግሆት «ቀንበር አጥባቂነት» ለደቀ መዛሙርታቸው ይገልጹ ነበር።

[1] ይህ ምዕራፍ የአሌክሳንድርያ ቤተ ክርስቲያን ለ1600 ዓመታት ያህል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ሹማ በምትልከው ሊቀ ጳጳስ አማካይነት ስታስተዳድርበት የነበረው አካሄድ አቁሞ በምትኩ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከራሷ አብራክ በተከፈሉ፣ በምእመናኗ ቋንቋ በሚናገሩ ኢትዮጵያውያን አባቶች ትመራ ዘንድ የተደረገውን ትግልና ውጤት የሚያተርብ በመሆኑ ይህ ርዕስ ተሰጥቶታል።

ይህ ሲባል ግን የመጣውን ቅጣት ሁሉ ለመቀበል ቆርጠው እንቀጹን በመጥቀስ በድፍረት «ይህ እኛን ኢትዮጵያውያንን ለመግዛት፣ ሀብታችንንም ለማጋዝ ሲሉ በ7ኛው መ.ክ.ዘ. ግብፆች በፍትሐ ነገሥት ውስጥ እንዲካተት ያደረጉት አንቀጽ ነው» በማለት የተቃወሙ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት አልነበሩም ለማለት አይጠ ደለም። በየዘመኑ የተነሡ በጣም ጥቂት ቆራጥ ሊቃውንት ነበሩና። ይሁን እንጂ፤ እነዚህ ሊቃውንት በዘመኑ ቤተ ክርስቲያኗ ትመራ የነበረው በግብፃውያኑ አባቶች ስለ ነበር በግዝት አፋቸውን እንዲይዙ፣ ከዚያም ባለፈ ወንበራቸውን እንዲያጥፉ፣ ከምእመናንም እንዲለዩ ይደረጉ ነበር። በዚህም የተነሣ በተጠቀሰው ዓይነት ጉዳዩ በጣም በተበታተነና በአነስ ሁኔታ በቤተ ክርስቲያኗ አንዳንድ ሊቃውንት ይነሣ ካልሆነ በስተቀር የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እንደ እንዷ.ት መንፈሳዊት ተቋም ጉዳዩን አንሥታ ተቃውሞዋን ሳታሰማ ቆይታለች።

ከዚህ በተሻለ ግን በሀገሪቷ ላይ በየጊዜው የነገሡ ነገሥታት የነበረውን ሒደት በመቃወም ድምፃቸውን ሲያሰሙ ቆይተዋል። እንዳንድ የታሪክ መዛግብት እንደ ሚገልጹት የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ጳጳስ የሆነው ሶርያዊው አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን በግብፃውያኑ ተሹሞ ከመጣ ጀምሮ ጉዳዩን በመቃወም «ቁጥራቸው እጅግ ብዙ ለሆነው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን በራሳቸው ቋንቋ ተዟዙረው የሚያስተምሯቸው ኢትዮጵያውያን ኤጲስ ቆጳሳትና ጳጳሳት ያስፈልጓቸዋል» ብሎ ለመጀመሪያ ጊዜ ድምፁን ያሰማው የኢትዮጵያ ንጉሥ ቅዱስ ሐርቤ /1060 - 1077 ዓ.ም/ ነበር።

በ11ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነግሦ የነበረውና ከነገደ ዛጉዌ የሆነው ንጉሥ ሐርቤ የነገሠበት የኢትዮጵያ እርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመን ቁጥር ብዙ፣ ሀገሩም ሰፊ እንደ ሆነ በማየት ኢትዮጵያውያን ኤጲስ ቆጳሳትን ይሾምለት ዘንድ በወቅቱ ለነበረው ግብፃዊ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ /አባ ሚካኤል ይባል ነበር/ ጥያቄ አቀረበ። ሊቀ ጳጳሱ ግን ፍላጐቱ እንደ ንጉሡ የስብከተ ወንጌል ነገር ሳይሆን ሀገሪቱ በመንበረ ማርቆስ ሥር እንድትቆይ ማድረግ ስለ ነበር የንጉሡን ጥያቄ በእሺታ አልተቀበለም። በምትኩ ጉዳዩን በግሉ ለመወሰንና ተግባራዊ ለማድረግ እንደ ማይችል ገልጦ ከፓትርያርኩ /ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ገብርኤል ይባሉ ነበር/ ጋር ልምከር በሚል ወደ ካይሮ ሔደ።

በወቅቱ በግብፅ ቤተ ክርስቲያን ላይ ተሹሞ የነበረው ፓትርያርክም የፍትሐ ነገሥቱን «ቀንበር ማጥበቂያ አንቀጽ» በመጥቀስ «ሦስት መቶ በሥራ ስምንቱ ሊቃውንት ኒቅያ ላይ ጉባኤ



ሠርተው ያሳለፉትን ውሳኔና ትእዛዝ መተላለፍ ነው» በሚል የንጉሡን ጥያቄ ሳይቀበል ቀረ። ከዚህም በተጨማሪ የኢትዮጵያው ንጉሥ ጥያቄ አበው የደነገጉትን ሥርዓት የጣሰ በመሆኑ አምላከ አበው እግዚአብሔር በኢትዮጵያ ላይ እንደ ተቆጣ አድርጐ መናገርና ማስነገር ጀመረ። የንጉሡን ጥያቄ ለማፈን ያስወራውን አሉባልታም የእርሱ አባቶች ቀንበር ማጥበቂያውን አንቀጽ በፍትሐ ነገሥት ስርዋጽ ገብቶ እንዲጻፍ እንዳደረጉ ሁሉ፤ እርሱም በወቅቱ የነበረውን ሥልጣን ተጠቅሞ የቅዱሳንን ዜና ሕይወትና ተጋድሎ ዘግቦ በያዘው ስንክሳር መጽሐፍ ላይ በስርዋጽ ገብቶ እንዲጻፍ አድርጓል። የአሉባልታው ታሪክም እንደ ሚከተለው ይነበባል፦

.. .. ..

*ደግሞ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ማን እንደ ጻፈው ያልታወቀ ጽሑፍ እናገኛለን። እንዲህም ይላል። በዚህ አባት በአባ ገብርኤል ዘመን በቅዱስ ሐርቤ ዘመነ መንግሥት አባ ሚካኤልም ለኢትዮጵያ ጳጳስ ሁኖ በነበረበት ጊዜ።*

*የኢትዮጵያ ንጉሥ ሐርቤ ለኢትዮጵያ አገሮች ኤጲስ ቆጳሳትን ይሾም ዘንድ አባ ሚካኤልን አዘዘው። አባ ሚካኤልም ያለ ሊቀ ጳጳሳቱ ትእዛዝ ሌሎች ኤጲስ ቆጳሳትን መሾም አልችልም ብሎ ለንጉሡ መለሰለት።*

*ስለዚህም የኢትዮጵያ ንጉሥ ወደ አባ ገብርኤልና ወደ ግብፅ ንጉሥ እየለመነና እየማለደ ንጉሡ አባ ገብርኤልን እንዲአዝለት፤ አባ ገብርኤልም ለአባ ሚካኤል እንዲፈቅድለትና በተጨማሪ ሌሎች ኤጲስ ቆጳሳትን አስቀድሞ በሾሟቸው ላይ እንዲሾም እንዲህ መልእክትን ላከ።*

*የግብፅ ንጉሡም የኢትዮጵያን ንጉሥ ፈቃዱን ሁሉ ይፈጽምለት ዘንድ አባ ሚካኤል እንዲፈቅድለት አባ ገብርኤልን አዘዘው።*

*ከዚህ በኋላ መኳንንቱ ወደ ግብፅ ንጉሥ ዘንድ ገብተው እንዲህ አሉት። በኢትዮጵያ ኤጲስ ቆጳሳት ቢበዙ ደፍረው ጳጳሳትን ይሾማሉ። ከዚያ በኋላ ከኛ ወደ እኛ አይመጡም።*

*ንጉሡም ይህን በሰማ ጊዜ ይህን አባት አባ ገብርኤልን እንዲህ አዘዘው። ከእንግዲህ በኢትዮጵያ አገር ኤጲስ ቆጳሳትን እንዳይሾም ለኢትዮጵያ ንጉሥ*

*የውግዘት ደብዳቤ ላከ እለው።*

*ሊቀ ጳጳሳቱም የግብፅ ንጉሥ እንዳዘዘው ላከ። የውግዘቱ ደብዳቤም ወደ ኢትዮጵያ ንጉሥ ደርሳ በተነበበች ጊዜ የንጉሡ እዳራሽ ተቃጠለ። በኢትዮጵያ አገርም ረኃብና ቸነፈር ሆነ። ዝናብም ተከለከለ። ችግርም ሆነ። የኢትዮጵያ ንጉሥ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ተላልፎአልና።*

*ከዚህ በኋላ የኢትዮጵያ ንጉሥ ተመልሶ ተጸጸተ። ወደ ግብፅም ይህን አባት አባ ገብርኤልን እንዲአዝለትና ከግዝቱ ይፈታው ዘንድ እየለመነ መልእክትን ላከ። የግብፅ ንጉሥም አዘዘለት።*

*አባ ገብርኤልም የመፈቻና የቡራኬ ደብዳቤ ኢትዮጵያውያንን ሁሉ እየባረከ ወደ ኢትዮጵያ ንጉሥ ላከ።*

*ይህች የበረከት ደብዳቤ ወደ ኢትዮጵያ አገር ደርሳ በተነበበች ጊዜ እግዚአብሔር መዓቱን ከላያቸው አርቆ ይቅርታውን ሰጣቸው። ዝናብም ወረደላቸው። ቸነፈርም ተወግዶ ታላቅ ደስታ ሆነ። ይህም በዘመኑ ሆነ።*

/ስንክሳር፣ ሚያዝያ 10/

የንጉሥ ሐርቤ ጥያቄ በዚህ ዓይነት ውጤት ሳያመጣ ተዳፍኖ፣ በምትኩ ግብፃውያን የመረጡትን እየላኩ ከሀገሪቷ ማግኘት ያለባቸውን ጥቅም ሊያገኙ ቆዩ።

«ያለ እኛ ሀገሪቷም ሆነች ቤተ ክርስቲያኗ አይቀኑም» ይሉ የነበሩት ግብፃውያን በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በተደረገው የመስቀል ጦርነት የተነሣ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ባለመቻላቸው፣ እንደ እነሱ አባባል፣ አገሪቷ ካለ ጳጳስ ቆይታለች። ይሁን እንጂ ኢትዮጵያውያን የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ይልቁንም በወቅቱ የታላቁ ገዳም የደብረ ሊባኖስ ገዳም ዕጨጌ የነበሩት ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በኢትዮጵያውያን መምህራንና ሊቃውንት ተመርጠው በመንበረ ጵጵስናው ላይ በመሾም አገሪቷን በመባረክ፣ ተዘጋጅተው ለቀረቡትም ዲቁናና ቅስና ሲሰጡ ቆይተዋል።

ጦርነቱ ከተጠናቀቀ በኋላም የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ስድስተኛውን የኢትዮጵያ ጳጳስ በላከች ጊዜ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መንበሩን አልለቅም አላለችም። በማስተዳደር ረገድ መንፈሳዊና አእምሮአዊ ብቃታቸውን በተግባር ያሳዩት ጻድቁ አቡነ ተክለ



ሃይማኖት ለዓመታት ተግተው ያገለገሉበትን መንበረ ጵጵስና ለመጣው አዲስ ግብፃዊ ጳጳስ ከአክብሮት ጋር አስረክበዋል።

ከንጉሥ ሐርቤ ቀጥሎም በየጊዜው መንበረ ሥልጣኑን የያዙ የኢትዮጵያ ነገሥታት ምንም እንኳን አዎንታዊ መልስ ባያገኙም ጥያቄያቸውን በግብፅ ለነገሡ የእስላም ነገሥታት ሊያነሡ ቆይተዋል። ለምሳሌ ዓፄ ዓምደ ጽዮን /1304 - 1305/ ለመሐመድ ኢብን ካላሁን፣ ዓፄ ይስሐቅ በ1423 ዓ.ም ለሡልጣን ባርሳቤይ፣ ዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ በ1443 ዓ.ም ለሡልጣን ካግማህ፣ ዓፄ እስክንድር በ1481 ዓ.ም ለሡልጣን ካይትባይ ያቀረቧቸው ጥያቄዎች ይጠቀሳሉ።

ወደ 19ኛው መ.ክ.ዘ. ስንመጣም ሀፄ ዮሐንስ አራተኛ /1871-1881/ ይህንኑ ለረጅም ዘመናት መልስ ሳያገኝ የቆየ ጥያቄ ለግብጽ ቤተ ክርስቲያን አቅርበዋል። ዓፄ ዮሐንስ ኢትዮጵያውያን በቋንቋቸው ወንጌል ይሰበክላቸው ዘንድ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን የራሷን አንድ ሊቀ ጳጳሳትና በርከት ያሉ ኢትዮጵያውያን ኤጲስ ቆጳሳት እንድትሾምላቸው በዘመኑ ለነበሩት የእስክንድርያው ፓትርያርክ አቡነ ቄርሎስ አምስተኛ ጥያቄ አቀረቡ። ይሁን እንጂ የንጉሡን ጥያቄ ፓትርያርኩ ሳይቀበሉ በምትኩ በኢትዮጵያ የሚኖሩትን ኤጲስ ቆጳሳት ቁጥር ወደ ሦስት ከፍ በማድረግ ከአንድ ሊቀ ጳጳሳት ጋር ሾመው ላኩ። በዚህም መሠረት በ1874 ዓ.ም አቡነ ጴጥሮስ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ፣ አቡነ ማቴዎስ የሸዋ ኤጲስ ቆጳስ፣ አቡነ ሉቃስ የጐጃም ኤጲስ ቆጳስ፣ አቡነ ማርቆስ የበጌ ምድር ኤጲስ ቆጳስ ሆነው በመሾም መጡ።

ጉዳዩ በዚህ ተደምድሞ የሀፄ ዮሐንስ አራተኛ ዘመነ መንግሥት በሀፄ ምኒልክ ተተካ። በዚህም የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት የነበሩት ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ /በ1910 ዓ.ም ሀርፈው እቲሳ ተ/ሃይማኖት ሳይ ተቀብረዋል/ ወደ ትግሬ ሀገረ ስብከት ተዛውረው በምትካቸው በሸዋ ተሹመው የነበሩት ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ /1874 - 1919/ መንበረ ጵጵስናውን ያዙ። እኒህ አባት በሸዋ ኤጲስ ቆጳስነት ለ8 ዓመታት፣ በኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳትነት ለ37 ዓመታት የተሾሙ ሲሆን ኅዳር 25 ቀን 1919 ዓ.ም ዐርፈው አዲስ አበባ ያኔ መካነ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ይባል በነበረው የዛሬው በዓለ ወልድ ቤተ ክርስቲያን ተቀብረዋል።

ይሁን እንጂ ሊቀ ጳጳሳቱ ከማረፋቸው አንድ ዓመት በፊት የጀመረው የኢትዮጵያውያን ሊቃውንትና መምህራን የሹመት ጥያቄ ካረፉ በኋላም እየተጠናከረ መጣ። የኢትዮጵያውያኑ ጥያቄ በወቅቱ በአማርኛ ቋንቋ እየተዘጋጁ ይታተሙ የነበሩትን «አእምሮ»ና «ብርሃንና ሰላም» የተሰኙ ጋዜጦችንም ሽፋን እያገኘ፣ ሊቃውንቱም

በጎትመቶቹ ሐሳባቸውን እየገለጹ ሔዱ። እየዋለ እያደረም የሊቃውንቱ ጥያቄና ክርክር ከመጠናከሩ የተነሣ ወደ ሰድብና ዘለፋ እስከ መሔድ በመድረሱ በሊቀ ጳጳሱ ከሳሽነት ለእስራትም የተዳረጉ ኢትዮጵያውያን ነበሩ ይባላል። ይህ የኢትዮጵያውያኑ ሊቃውንት፣ መኳንንትና ሠራዊት ክርክርና ፍትሐዊ ጥያቄ በጋዜጦቹ አማካይነት ወደ ቤተ መንግሥቱ ገብቶ ተደማጭነትንና ተቀባይነትን አገኘ።

በወቅቱ በልዑል አልጋ ወራሽነት መዓርግ ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ የነበሩት ራስ ተፈሪ መኰንን /በኋላ ግርማዊ ቀዳማዊ ዓፄ ኃይለ ሥላሴ/ እንደ ቀደሙት ነገሥታት በጥያቄው ተገቢነት በማመን እጅንዳው የቤተ መንግሥቱ እንዲሆን አደረጉ። በዚህም ጉዳዩን በመጀመሪያ ለግርማዊት ንግሥተ ንግሥታት ዘውዲቱ፤ ቀጥሎም ለመሣፍንቱ፣ መኳንንቱና ሊቃውንቱ በማቅረብ ሰፊ ውይይት አደረጉበት። በውይይቱም ከልዑል አልጋ ወራሹ ጀምሮ ሁሉም የጥያቄውን ተገቢነት በማመናቸው በልዑል አልጋ ወራሽ ፊርማ «ባረፉት የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ምትክ ሌላ ሊቀ ጳጳሳት ተሹሞ እንዲመጣ፣ ከእርሱም ጋር በሀገሪቱ ወንጌል ይስፋፋ ዘንድ የሚያስፈልጉ በርከት ያሉ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ይሾሙልን ዘንድ ፈቃዳችሁ ይሁን» በሚል ለወቅቱ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ለብፁዕ አቡነ ቄርሎስ አምስተኛ ደብዳቤ ተላከ።

ደብዳቤው የደረሳቸው የግብፅ ፓትርያርክም ብቻቸውን በጉዳዩ ውሳኔ ሊያሳልፉበት እንደ ማይችሉ፤ በመሆኑም በጥያቄው ላይ የሚመክር ጉባኤ ጠርተው ውሳኔ እንዲሰጥበት እንደ ሚያደርጉ በመግለጽ ለልዑል አልጋ ወራሽ መልስ ሰጡ።

አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪም ሆኑ ኢትዮጵያውያን ፓትርያርኩ በገቡት ቃል መሠረት ጉባኤ የሚጠሩበትንና ውሳኔ የሚያስጡበትን ቀን በመጠባበቅ ላይ ሳሉ የግብፅን ቤተ ክርስቲያን ለ52 ዓመታት ከዘጠኝ ወራት የመሩት ፓትርያርክ ከዚህ ዓለም በሞት እንደ ተለዩ ተሰማ። የፓትርያርኩን ዕረፍት በማስመልከትም ኢትዮጵያ የተሰማትን ኀዘን በመግለጽ፤ ወዲያውም የቀረበው ጥያቄ መልስ እንዲያገኝ በሚል አዲስ አበባ ላይ ሰባት ጊዜ መድፍ እንዲተኮስ ተደረገ።

በዕድሜ ጠገቡ ፓትርያርክ ሞት የተነሣ የቀረበውን ጉዳይ የሚያስፈጽም አዲስ ፓትርያርክ ባለ መሾሙ የኢትዮጵያ ጥያቄ ለአንድ ዓመት ከአምስት ወር ያህል ሊዘገይ ግድ ሆነ። ከዚያም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሐንስ ታኅሣሥ ሰባት ቀን 1921 ዓ.ም 19ኛው የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ሆነው እንደ ተሾሙ በቴሌ ግራም ለልዑል አልጋ ወራሹ ተገለጠ። ልዑል አልጋ ወራሹም በጉዳዩ የተሰማቸውን ደስታ ለፓትርያርኩ ገልጸው ቀደም ሲል



ያቀረቡት ጥያቄ አፋጣኝ ምላሽ እንዲሰጠው የሚያሳስብ ቴሌግራም ላኩ። ይኸውም በአቡነ ማቴዎስ ምትክ አንድ ሊቀ ጳጳስ ተሹሞ እንዲላክ፤ እርሱም አዲስ አበባ ሲደርስ ከኢትዮጵያ መምህራን እየመረጠ ጳጳሳትን እንዲሾም የሚል ጥያቄ ነበር።

ይሁን እንጂ አዲሱ የእስክንድርያ ፓትርያርክ ጥያቄውን ሙሉ በሙሉ ባለመቀበል የሚከተለውን ቴሌ ግራም ለልዑል አልጋ ወራሹ ላኩ።

*ግርማዊነትዎ የላከውን መልእክት ለማን።*

*በግብፅ ቤተ ክርስቲያንና በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መካከል ያለውን መልካም ወዳጅነት አጠንክሮ ለማኖር ስለ ገለጡልን ልባችን በደስታ ተነካ። ለግርማዊነትዎና ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን፤ ለሕዝብዎም ተድላ እንዲሆን ስለ ራሳችን ስለ ግብፅም ሕዝብ ሆነን የምንመኘውን መልካም ምኞታችንን በደስታ እናቀርባለን።*

*ለግርማዊነትዎ በማንኛውም ነገር የሚስማማ መልካም ባሕርይ ያለው አንድ ጳጳስ ለመሾም ከዚህ ቀድሞ መፍቀዳችንን እንደ ገና እናረጋግጣለን። የቤተ ክርስቲያኑ ሕግ የሚፈቅድልን ቢሆን ኖሮ ይህንኑ ሊቀ ጳጳስ ሌሎች ጳጳሳትን ለመሾም እንዲችል አድርገን ብንሾመው ደስ ይለን ነበር። ይህ በተለይ የቤተ ክርስቲያንን ሕግ የሚያውክ ስለሆነ ብፁዕ ፓትርያርክ ሱሪል በዮሴፍ ፓሻ ሱሌይማን በኩል ያስታወቁንን አሳብ እናረጋግጣለን። ጳጳስ ብለን እንድንሾማቸው ብፁዕ ስጨጌን ግርማዊነትዎ ይላኩልን። ከሊቀ ጳጳሱም ጋራ አንድነት ሆነው በኢትዮጵያ በየክፍሉ ባለው ሥራ የሚረዱ ሁለት የግብፅ ጳጳሶችን እንሾማለን። በኢትዮጵያ ልጆችና በናታቸው በግብፅ ቤተ ክርስቲያን መካከል እስካሁን ሳያልቅ የቆየውን ነገር ሁሉ ለሁለቱም ወገን ጥቅም የሚሆንና ለግርማዊነትዎም ደስ በሚያሰኝ መንገድ ለመጨረስ ቁርጥ የሆነ አሳባችን መሆኑን እናረጋግጣለን። ሁለቱንም አገሮች የሚያስተሳስረው የፍቅር ማሰሪያ እየጠበቀ እንዲሔድ እንደ ግርማዊነትዎ ሐዋርያዊ ቡራኬያችንን ለግርማዊት ንግሥተ ንግሥታት ዘውዲቱና ለግርማዊነትዎ ለቤተ ዘመዶቻችሁም ለቤተ ክርስቲያን ልጆቻችን ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንሰጣለን።*

ልዑል እልጋ ወራሽ ተፈሪም የፓትርያርኩን የአቡነ ዮሐንስን ቴሌግራም ከተመለከቱ በኋላ ከዚህ ቀጥሎ የቀረበውን ምላሽ በቴሌ ግራም አስተላለፉ::

*ለብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ዮሐንስ፣ ቴሌ ግራምዎ ደረሰን:: መልካም ባሕርይ ያለው አንድ ሊቀ ጳጳስ ለመሾም እርሱ ከእኛም ለአንዱ ለዕጨጌ ጳጳስነት ለመስጠት መፍቀድዎን የሚያስታውቅ አሳብ ግን እኛ እንጳስብነው የትምህርት ችግራችንን የሚያቀልልን አልሆነም:: የሚጨመሩትንም ሁለቱ ግብፆች መቼም ቋንቋችንን አያውቁትምና ፈቃድዎ ሆኖልን ዛሬ ለጊዜው በቋንቋችን ከሚያስተምሩ ሊቃውንት መርጠን የሚያስፈልገንን ያህል ከመልእክተኞቻችን ጋራ በደንልዎ ስለ ቤተ ክርስቲያኑ ሥርዓት የሚከለከል ሕግ ከተገኘ እኛም ያስፈልገናል ያልንበትን ምክንያት አስታውቀው እርስዎም የቤተ ክርስቲያኑ ሕግ የሚከለከልበትን ሥርዓት አስረድተዋቸው የሚመጣው ሊቀ ጳጳስ ከዚህ ለመሾም የማይቻል ነው ከተባለ እነዚህን መርጠን የምንስድልዎን ሰዎች ከዚያው ተሹመው ከሊቀ ጳጳሱ ጋራ አብረው ይምጡልን::*

*ይህንንም ፈቃድዎን አለመጋፋታችን እስከ አሁን ጸንቶ የኖረው ያባትና የልጅነት መተማመን እንዳ ይጉድል ብለን ነው እንጂ የእኛም የሕዝባችንም ፈቃድ ግን ያው ቀድሞ እንደላክንብዎ ቃል መሆኑን እንዲ ያውቁልን እንለምንዎታለን::*

ንጉሥ ተፈሪ ቴሌግራሙን ከላኩም በኋላ የቴሌግራሙ ውይይት ፍሬ እንደ ማያመጣ በማሰብ በወቅቱ የትምህርት ሚኒ ስቴር ዲሬክተር በነበሩት በአቶ ሣህሌ ጸዳሉ የሚመራ ልዑክ ወደ ምድረ ግብፅ ላኩ:: ልዑኩም ይዞት በሔደው አጀንዳ ዙሪያ ከፓትርያርኩ ጋር ሰፋ ያለ ክርክር አደረገ:: በዚህም ፓትርያርኩ አስቸኳይ የሲኖዶስ ጉባኤ ጠርተው ከተወያዩ በኋላ ከአንድ ግብፃዊ ሊቀ ጳጳሳት ጋር አምስት ኢትዮጵያውያን ኤጲስ ቆጳሳት እንዲ ሾሙ ፈቀዱ:: ፓትርያርኩም ውሳኔውን በሚከተለው ቴሌ ግራም ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ አስተላለፉ::

*ሐዋርያዊ ቡራኬያችን ለግርማዊነትዎ ይሁን:: ከኢትዮጵያ መምህራን አምስት ሰዎች ተመርጠው*



*ጳጳሳት ሆነው አምስት የኢትዮጵያ ኤጲስ ቆጳሳት ሹመት እንዲሾሙ ፈቅደናልና አምስት መነኮሳት እንዲልኩልን እንለምናለን::*

ግርማዊ ንጉሥም በፍጥነት በሚከተለው ቴሌ ግራም የተሰማቸውን ደስታ ገለጹ::

*በሣህሌ ጸዳሉ በኩል ባስታወቅንዎ ጉዳይ ከቡራ ኬዎ ጋር በላኩልን ምላሽ ደስ ብሎናል:: መነኮሳቱንም እንደ ሚያስፈልግ አድርገን እንልካለን:: እግዚአብሔር ቅዱስነትዎን ይጠብቅ::*

ከዚህ በኋላ ግርማዊት ንግሥተ ንግሥታት ዘውዲቱና ግር ማዊ ንጉሥ ተፈሪ ነገሩ ይዋል ይደር ሳይሉ የኢትዮጵያ የዘመናት ጥያቄ መልስ ማግኘቱን ሊቃውንቱን፣ መሣፍንቱንና መኳንንቱን በመሰብሰብ አሳወቁ:: የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ በጠየቁት መሠረትም በትምህርትና በምግባር የተመሰከረላቸውን መምህራን እንዲመርጡ ትእዛዝ አስተላለፉ::

በትእዛዙ መሠረትም ቤተ ክህነቱና ቤተ መንግሥቱ በአንድ ነት ጉባኤ በማድረግ መዓርገ ጵጵስናው ይገባቸዋል የተባሉ ዐሥር መምህራን ተመረጡ:: ይህም ለግርማዊትና ግርማዊ ተገለጠ:: ይሁን እንጂ ለምርጫ የተሰበሰቡት ሊቃውንት በነበራቸው ችኮላና ጉጉት ምክንያት አምስት መምረጥ ሲገባቸው ዐሥር መርጠው ነበር:: የግብፅ ቤተ ክርስቲያን በጠየቀችው መሠረት የተመራጭ ሊቃውንቱን ቁጥር ወደ አምስት ለማውረድ እንደ ገና ሊቃውንቱን ጉባኤ መጥራቱ ጊዜ ስለ ሚወስድ ከተመረጡት ዐሥር መምህራን አምስቱ በሰጣ እንዲለዩ ተወሰነ:: ቀድሞ ከዐሥሩ ውስጥ ተመርጠው ዕጣ ሳይወጣላቸው በመቅረቱ ከቀሩት አባቶች በስም ሊታወቁ የቻሉት መልአከ ገነት ወልደ ሐና፣ አለቃ ወልድ ተክሌ፣ አለቃ ወልደ ትንሣኤ የተባሉት አባቶች ብቻ ናቸው::

በዚህም መሠረት በዕጣው ላይ ለበባት ቀናት በቤተ ክርስቲያን ጸሎትና ሱባኤ ከተያዘበት በኋላ ዕጣው ወጥቶ አምስቱ መምህራን ተሰዩ:: እነርሱም ብፁዕ ዕጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ፣ መምህር ደስታ፣ መምህር ኃይለ ማርያም፣ መምህር ወልደ ኪዳንና መምህር ኃይለ ሚካኤል ናቸው::

ከዚህ በኋላ ከተመረጡት መምህራን አራቱ በወቅቱ የገንዘብ ሚኒስቴር በነበሩት በክቡር በጅሮንድ ዘለቀ አግደውና የትምህርት ሚኒስትር ዲሬክተር በነበሩት በክቡር አቶ ሣህሌ መሪነት ግንቦት 2 ቀን 1921 ዓ.ም ከአዲስ አበባ በባቡር ተሳፍረው ወደ ጅቡቲ ሔዱ::

ዕጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በወቅቱ ባጋጠማቸው ሕመም የተነሣ ወደ ካይሮ ሊሔዱ አልቻሉም:: ነገር ግን በ1922 ዓ.ም ፓትርያርኩ ኢትዮጵያን ለመጎብኘት በመጡ ጊዜ ጥር 1 ቀን 1922 ዓ.ም ሥርዓተ ቅብዓታቸውን እዚሁ አዲስ አበባ በመታሰቢያ ቤት በአታ ለማርያም ገዳም ሳዊሮስ ብለው በመሠየም ፈጽመውላቸዋል:: ፓትርያርኩ በዚህ አፊሴላዊ ጉብኝታቸው ወቅት የመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራልን የመሠረት ድንጋይ አስቀምጠው እንደ ነበር ይነገራል::

ለታላቁ ሹመት የታጩት አራት አባቶችና ሌሎች ልዑካን ከጅቡቲም ግንቦት 5 ቀን በመርከብ ተሳፍረው ወደ ካይሮ ሔዱ:: በካይሮም ለ20 ቀናት ከቆዩ በኋላ ግንቦት 25 ቀን 1921 ዓ.ም ከግብፃዊው የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ቄርሎስ ጋር መምህር ደስታ - አቡነ አብርሃም፤ መምህር ኃይለ ማርያም - አቡነ ጴጥሮስ፤ መምህር ወልደ ኪዳን - አቡነ ይስሐቅ፤ መምህር ኃይለ ሚካኤል - አቡነ ሚካኤል ተብለው በፓትርያርኩ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሐንስ አንብሮተ ዕድ በካይሮ ቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ተሾሙ::

ኢትዮጵያውያኑ አባቶች በተጠቀሰው ቀን ከተሾሙ በኋላ ፓትርያርኩ አቡነ ዮሐንስ ለግርማዊት ንግሥተ ንግሥታት ዘውዲቱና ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ከዚህ ቀጥሎ የቀረበውን ቴሌ ግራም አስተላለፉ::

> *ዛሬ በግንቦት 25 ቀን አባ ቄርሎስን ሊቀ ጳጳሳት አድርገን፤ አራቱን የኢትዮጵያ መምህራን ጳጳሳት አድርገን ስማቸውንም ጴጥሮስ፣ አብርሃም፣ ይስሐቅ፣ ሚካኤል ብለን ቀብተን ሹመናቸዋል::*

የቴሌ ግራሙን መልእክት የተቀበሉት ግርማዊትና ግርማዊም ወዲያውኑ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል በቴሌ ግራም ወደ ፓትርያርኩ ላኩ::

> *ለብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ዮሐንስ፤ የሊቀ ጳጳሱንና የጳጳሳቱን መሾም ስላስታወቁን እናመሰግንዎታለን:: ይኸውም ነገር በቅዱስነትዎ ዘመን መፈጸሙ የኢትዮጵያና የግብፅ ቤተ ክርስቲያኖን አንድነት እያጸና የሚሔድ መሆኑን ያስረዳልናል:: እግዚአብሔር ፓትርያርክነትዎን ይባርክ::*



ግብፃዊው የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ቄርሎስና አራቱ ኢትዮጵያውያን ኤጲስ ቆጶሳት ከላይ በተገለጠው መንገድ መዓርገ ጵጵስና ከተቀበሉ በኋላ ተመሳሳይ የባቡርና የመርከብ የመልስ ጉዞ በማድረግ ሰኔ 21 ቀን 1921 ዓ.ም አዲስ አበባ ገቡ:: ለ1600 ዓመታት ያህል ኢትዮጵያውያን ነገሥታትም ሆኑ አባቶች ሲታገሉለት የነበረው የኢትዮጵያውያን መሾም ጉዳይ እግዚአብሔር በፈቀደው በዚያ ዘመን ሊፈጸም ያዩ ኢትዮጵያውያን፤ ለተሾሙት ብፁዓን አባቶች ወደ ኢትዮጵያ ምድር ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ በየቦታው ከፍተኛ አቀባበል ያደርጉላቸው ነበር:: ለምሳሌ ድሬዳዋ ሲደርሱ ከከተማውና በአካባቢው ከተሰበሰቡት ኢትዮጵያውያን በተጨማሪ ለዚሁ በቤተ መንግሥቱ ትእዛዝ ከአዲስ አበባ በተላኩ ሊቃውንትና ታላላቅ ባለሥልጣናት አማካይነት የሞቀ አቀባበል ተደርጎላቸዋል:: ድሬዳዋን አልፈው ሞጆ ሲደርሱም በወቅቱ የሀገር ግዛት ሚኒስትር የነበሩት ደጃዝማች ወ/ጻድቅ እና የመሳሰሉት ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት አቀባበል አድርገውላቸዋል::

እነዚህ የመጀመሪያዎቹ ኢትዮጵያውያን ብፁዓን አባቶችና በሊቀ ጳጳስነት ተሹመው የመጡት ግብጻዊው አቡነ ቄርሎስ ከሃያ ቀናት በላይ ተጉዘው አዲስ አበባ ባቡር ጣቢያ ሊደርሱ ግርማዊ ቀዳማዊ ዓፄ ኃ/ሥላሴ ከሕዝባቸው ጋር በመሆን ደማቅ አቀባበል አድርገውላቸዋል:: በማግሥቱም ትልቅ በዓል ተደርጎ ለክብራቸውም 25 ጊዜ መድፍ ተተኩሶላቸዋል::

ኢትዮጵያውኑ አባቶች ለአንድ ዓመት ያህል ከቤተ መንግሥቱ ሳይርቁ ሥነ አስተዳደር እንዲ ለማመዱ ከተደረገ በኋላ ቀደም ያሉት ነገሥታትም ጭምር ያልሙት የነበረው የስብከተ ወንጌል አገልግሎት በሀገሪቱ የመስፋፋት ነገር እውን ሊሆን በቤተ መንግሥቱ ሀገረ ስብከት እየተከፈለ ተሰጣቸው:: */የሹመታቸውን ደብዳቤ በአባሪ 1 ይመለከቷል/::*

ኢትዮጵያውያኑ ጳጳሳትም በየተመደቡበት ሀገረ ስብከት በመሠማራት ሕዝባቸውን በትጋት መባረክና ማስተማር ጀመሩ:: ይሁን እንጂ ሕዝቡ ለአባቶቹ ያሳይ የነበረው ፍቅር ብዙም ሳይዘልቅ፣ የአባቶች የስብከተ ወንጌል እንቅስቃሴ ገና በመጀመር ላይ ሳለ ሀገራችንን በግፍ ሊወር በመጣው የኢጣሊያ ፋሺስት ጦር ተደናቀፈ:: ቀደም ባለው የሀገሪቷ ታሪክ እንደ ሆነው በ1928 ዓ.ም ኢትዮጵያ በተወረረች ጊዜም ብሔራዊት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስ

ቲያን ግንባር ቀደም ተጠቂ ነበረች። በርካታ አብያተ ክርስቲያናቷ ወድመዋል። ከመቼውም ጊዜ በበለጠም ሀብቷ ተዘርፏል። ኢትዮጵያውያን ነገሥታትና ሕዝብ ባደረጉት ሰፊ ትግል ለመጀመሪያ ጊዜ ተሹመው የሀገሪቱ ሕዝብ በስስት ከሚያያቸው የመጀመሪያዎቹ ጳጳሳቷ መካከል ሁለቱ በግፍ ተረሸነውባታል።

የጉዳዩን መካረር ያዩት የወቅቱ ግብፃዊ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ ወደ ሮማ ሔጄ ከዱቼ ሙሶሎኒ ጋር ስለ ጉዳዩ ልምክር በሚል ብፁዕ አቡነ አብርሃምን ተጠባባቂ ሊቀ ጳጳሳት አድርገው በመሾም ሔዱ። ይሁን እንጂ ኢትዮጵያውያን ግብፃዊው አቡነ ቄርሎስ ሰላምን ይዘውልን ይመለሳሉ ብለው በጉጉት ቢጠብቋቸውም ከሮማ ሊመለሱ ያመሩት ቀኑ ወደ ጨለመበት የኢትዮጵያ ሕዝብ ሳይሆን ወደ ሀገራቸው ወደ ግብፅ ነበረ።

የአቡነ ቄርሎስን ወደ ሮማ መሔድ አስመልክቶ አንዳንድ የታሪክ መዛግብት ለየት ያለ ሐሳብ ያስፍራሉ። ይኸውም ሊቀ ጳጳሱ ወደ ሮማ ያቀኑት ሙሶሎኒ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳሳት ለመሆናቸው ዕውቅና እንዲሰጣቸው ለመማጸን ነበር የሚል ነው። እነዚህ የታሪክ መዛግብት ሊቀ ጳጳሱ ወደ ኢትዮጵያ ሳይመጡ በዚያው ወደ ሀገራቸው የሔዱበትን ምክንያት ሲገልጹ ሙሶሎኒ ለጥያቄያቸው አዎንታዊ ምላሽ ስላልሰጣቸው እንደሆነ ያትታሉ።

የሆነው ሆኖ በዚህ ዓይነት ብፁዕ አቡነ አብርሃም ተጠባባቂ ሊቀ ጳጳሳት ሆነው የመከራውን ዘመን ሲገፉ የኢጣሊያ መንግሥት በቤተ ክርስቲያናችን ላይ የፈጸመውን ግፍ ለማስረሳትና በዚህም እሷን መሳሪያ አድርጐ ስየቦታው የእግር እሳት የሆኑበትን ኢትዮጵያውያን አርበኞችን ለማሥታገስ ሲል በ1930 ዓ.ም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የራሷን ሊቀ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጳሳት መሾም ትችላለች በማለት ዐወጀ። ይህ ዐዋጅ ወደ ተግባር ይለወጥ ዘንድም ከሸዋ፣ ከጎጃም፣ ከጎንደር፣ ከወሎና ከትግሬ አስራ አምስት አስራ አምስት ሊቃውንት ወደ አዲስ አበባ መጥተው ጉባኤ እንዲሆን ትእዛዝ አስተላለፈ። ምንም እንኳን ኢትዮጵያውያኑ ሊቃውንት የዐዋጁ መንፈስ ምን እንደ ሆነ በሚገባ የተረዱት ቢሆንም አጋጣሚውን ለመጠቀም በመፈለግ ኅዳር 21 ቀን 1930 ዓ.ም ከየክፍሉ የተውጣጡ መምህራንና ሊቃውንት አዲስ አበባ ላይ ጉባኤ አደረጉ።

ጉባኤውም በተለያዩ ነጥቦች ላይ ሰፊ ውይይት ካደረገ በኋላ ቀደም ሲል ወደ ግብፅ ሔደው የተሾሙት ብፁዕ አቡነ አብርሃም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳሳት እንዲሆኑ፣ እርሳቸውም ሌሎች ጳጳሳትንና ኤጲስ ቆጳሳትን እንዲሾሙ የሚል ታሪካዊ ውሳኔ አሳልፎ ተጠናቀቀ። በውሳኔውም



መሠረት በዚያው ቀን ጉባኤው የሚገባውን ጸሎት ካደረሰ በኋላ ብፁዕ አቡነ አብርሃም የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ሆነው ተሾሙ። ብፁዕነታቸውም በዚያው ቀን የሚከተሉትን ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጳስ ሾሙ፡፡

- ንቡረ ዕድ ተክለ ሃይማኖት ይባሉ የነበሩትን ብፁዕ አባ ዮሐንስ ብለው፤ ዕጨጌና የሸዋ ሀገረ ስብከት ጳጳስ፤
- መምህር ገብረ አምላክ ይባሉ የነበሩትን ብፁዕ አባ ማርቆስ ብለው፤ የኤርትራ ሀገረ ስብከት ጳጳስ፤
- መምህር ገብረ አምላክ ይባሉ የነበሩትን ብፁዕ አባ ማቴዎስ ብለው፤ የወሎ ሀገረ ስብከት ጳጳስ፤
- መምህር ገብረ ኪዳን ይባሉ የነበሩትን ብፁዕ አባ ገብርኤል ብለው፤ የጐንደር ሀገረ ስብከት ጳጳስ፤
- መምህር አካሉ ይባሉ የነበሩትን ብፁዕ አባ ሉቃስ ብለው፤ የወለጋ ሀገረ ስብከት ኤጲስ ቆጳስ።

ኢትዮጵያውያን ችግር ባጋጠማቸው ጊዜ በአቡነ ቄርሎስ አማካይነት ሀገሪቷን እሳት ላይ ጥላ የሸሸችው የግብፅ ቤተ ክርስቲያንም ይህንን ውሳኔና ሹመት በሰማች ጊዜ ድርጊቱንም ሆነ የድርጊቱን አስፈጻሚ አቡነ አብርሃምን አወገዘች። ከውግዘትም ጋር ሕዝቡ ከእሳቸውም ሆነ እሳቸው ከሾሟቸው አባቶች መስቀል እንዳይሳለም ጥሪ አቀረበች። ነገር ግን ብፁዕ አቡነ አብርሃምም ሆኑ የተሾሙት አባቶች እንዲሁም ሊቃውንቱና ምእመኑ ለውግዘቱ ቦታ ሳይሰጡ አገልግሎታቸውን ቀጠሉ። ከዓመት በኋላ ሐምሌ 14 ቀን 1931 ዓ.ም ሽምግልና ተጫጭኗቸው የነበሩት ብፁዕ አቡነ አብርሃም ዐረፉ። በመሆኑም በእርሳቸው ቦታ የሚተካውን ሊቀ ጳጳሳት ለመምረጥ ከየክፍሉ የተውጣጡት ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን መስከረም 1 ቀን 1932 ዓ.ም እንደ ገና ጉባኤ አደረጉ። በጉባኤው መጨረሻም ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ መንበረ ሊቀ ጵጵስናውን ተረክበው እንዲያገለግሉ፤ እርሳቸውም ሌሎች ጳጳሳትን እንዲሾሙ በሙሉ ድምፅ ውሳኔ አስተላለፈ። ብፁዕ አቡነ ዮሐንስም በጉባኤው ውሳኔ መሠረት የሚከተሉትን ጳጳሳት ሾሙ።

- ሊቀ ሊቃውንት ገብረ አብ ይባሉ የነበሩትን ብፁዕ አባ ፊልጶስ ብለው፤ የሊቀ ጳጳሳት ዮሐንስ ጸሐፊ፤
- መምህር ገብረ ጊዮርጊስ ይባሉ የነበሩትን ብፁዕ አባ ጎርጎርዮስ ብለው፤ የወሎ ጳጳስ፤

- *መምህር ሣህሌ ይባሉ የነበሩትን ብፁዕ አባ ማትያስ ብለው፤ የሸዋ ጳጳስ፤*
- *መምህር ተክለ ማርያም ይባሉ የነበሩትን ብፁዕ አባ አትናቴዎስ ብለው፤ የጎጃም ጳጳስ፤*
- *መምህር ወልደ አረጋይ ይባሉ የነበሩትን ብፁዕ አባ ቴርሎስ ብለው፤ የኤርትራ ጳጳስ::*

ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ከነዚህም በተጨማሪ ከአምስት ወራት በኋላ በጥር ወር 1932 ዓ.ም አባ ኃይለ ሚካኤል ይባሉ የነበሩትን ብፁዕ አባ ዘካርያስ ብለው፤ የኢየሩሳሌም ኤጲስ ቆጶስ አድርገው ሾሙ::

በዚህ ዓይነት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የጳጳሳትና የኤጲስ ቆጶሳት ቁጥሯን ወደ ሀሥር አሳድጋ በተስመደ ተግባሯ በጠላት ወረራ ይሳቀቁ እና ይንገላቱ የነበሩትን ኢትዮጵያውያን ስታጽናና ስትመክር ቆየች::

እግዚአብሔር በአምስቱ የመከራ ዘመናት በየቦታው የፈሰሰውን የንጹሐን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ደም ጩኸት፤ እንዲሁም በየዋሻው ዘግተው የሚጸልዩትን አባቶችና እናቶች ጸሎት ሰምቶ በ1933 ዓ.ም ሀገሪቷ ከወራሪው ኃይል ነጻ ወጣች:: ንጉሡም ወደ ኢትዮጵያ ተመለሱ:: በዚህ ጊዜ የሁለቱን ወዳጅ ሀገሮች (የግብፅንና የኢትዮጵያን) ፖለቲካዊ ግንኙነት ስመጠበቅ በሚል ምንም እንኳን የእንጻንዶቹ አባቶች ቆይቶ ቢመለስላቸውም በወረራው ወቅት የተሾሙት አባቶች በየሀገረ ስብከታቸው ያለ ምንም ሥራ እንዲቀመጡ ሆነ:: የቤተ ክህነቱንም ሥራ በወቅቱ የደብረ ሊባኖስ ገዳም ዕጨጌ የነበሩት ዕጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ እንዲመሩት ተደረገ::

ከዚህ በኋላ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥቱ ተቋርጦ የቆየው የሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት ግንኙነት እንዲቀጥል ለግብጽ ቤተ ክርስቲያን ጥያቄ አቀረቡ:: በጥያቄውም መሠረት የግብፅ ቤተ ክርስቲያን በወረራው ወቅት ሸሽተው ወደ ሀገራቸው በሔዱት አቡነ ቄርሎስ የሚመራ አንድ ልዑክ ወደ ኢትዮጵያ ላከች:: ከሊቀ ጳጳሱ ጋር የመጡት ሰዎች ሚ/ር ሳዲቅ ፓሻ ዋህቢ፣ ሚ/ር ሜሪት ጋሊ ቤዲ፣ ፊርግ ሚካኤል ሙሳ ቤዲ ይባሉ ነበር:: ልዑኩ በቤተ መንግሥቱ ከተወከሉ ኢትዮጵያውያን ጋር ከተወያየ በኋላ የኢትዮጵያን «ግዝቱ ይነሣልን» ጥያቄ ይዞ ወደ ካይሮ ተመለሰ:: በዚህ ጊዜ አቡነ ቄርሎስ አዲስ አበባ ቀሩ:: ጉዳዩን መስመር ለማስያዝ በሚልም በወቅቱ የሊቀ ጳጳሳትነቱን ቦታ ይዘው የነበሩት ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ



የመንበረ ሊቀ ጳጳሱን ግቢ እንዲለቁ ተደርጎ ግብፃዊው ሊቀ ጳጳሳት በዚያ እንዲቀመጡ ተደረገ::

በአቡነ ዮሳብ ተጠባባቂ ፓትርያርክነት ይመራ የነበረው የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ሰኔ 14 ቀን 1934 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ መጥቶ የነበረው ልዑክ ይዞት በሔደው ጥያቄ ላይ ውይያት ካደረገ በኋላ አንድ ውሳኔ አስተላለፈ:: ውሳኔውም ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥቱ ተላከ:: ይሁን እንጂ ተላለፈ የተባለው ውሳኔ ለኢትዮጵያውያኑ አርኪ አልነበረም:: በዚህ የተነሣም ውይይቱ ለጊዜው ተቋረጠ::

ከወራት በኋላ ጥር 27 ቀን 1936 ዓ.ም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መቃርዮስ 114ኛ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ሆነው ሲሾሙ በራሳቸው በአዲሱ ፓትርያርክ ጥያቄ ግዝቱን አስመልክቶ ተጀምሮ የነበረው ውይይት እንዲቀጥል ተደረገ:: በመሆኑም በፓትርያርኩ የተወከለ በጉዳዩ ላይ መክሮ የሚመለስ በአቡነ ጢሞቴዎስ የሚመራ አንድ ልዑክ ወደ ኢትዮጵያ መጣ:: ከአቡነ ጢሞቴዎስ ጋር የመጡት ሰዎች ጊምዲ ቤይ አብዱል መሊክ፣ እስክንድር ቤይ አሳብረና አስአድ ማርቆስ ቤይ ይባሉ ነበር::

ልዑኩም ከሰኔ 9 - 21 ቀን 1936 ዓ.ም በዕጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ይመራ ከነበረው የኢትዮጵያ ቤተ መንግሥትና ቤተ ክህነት ተወካዮች ልዑክ ጋር ከተወያየ በኋላ በስድስት አንቀጾች የቀረቡትን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን ጥያቄዎች ይዞ ወደ ካይሮ ተመለሰ:: */የውይይቱን ሙሉ ቃለ ጉባኤ በአባሪ 2 ይመለከቷል/::*

ልዑኩ ካይሮ እንደ ደረሰ ጥያቄዎቹን ለፓትርያርኩ አቀረበ:: ፓትርያርኩም ደብዳቤውን ከተመለከቱ በኋላ ኢትዮጵያውያኑ ሊቃውንት በስድስት ነጥቦች ወስነው ባቀረቧቸው ጥያቄዎች ላይ አከራካሪ የሆነ መልስ ያዘለ ደብዳቤ ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥቱ ላኩ:: */የደብዳቤውን ሙሉ ቃል በአባሪ 3 ይመለከቷል/::* ንጉሠ ነገሥቱም ፓትርያርኩ በደብዳቤያቸው የጠየቋቸው ጥያቄዎች መልስ ያገኙ ዘንድ ጥያቄውን ወደ አቀረበው መንፈሳዊ ጉባኤ እንዲያስተላልፉትና መልሱን ከጉባኤው እንዲጠብቁ የሚገልጽ ደብዳቤ ላኩላቸው:: የፓትርያርኩን ጥያቄ ከንጉሡ የተቀበለው መንፈሳዊ ጉባኤም ሳይውል ሳያድር ጥያቄ የተነሳባቸውን አንቀጾች በማብራራት ለፓትርያርኩ በቀጥታ ላከ:: */የደብዳቤውን ሙሉ ቃል በአባሪ 4 ይመለከቷል/::*

የመንፈሳዊ ጉባኤው ማብራሪያ የደረሳቸው ፓትርያርክም ጉዳዩን ለሲኖዶስ አቅርበው ከተወያዩበት በኋላ የጉባኤው ሂደት የተዘገበበትን ቃለ ጉባኤ እና ያስተላለፈውን ውሳኔ ለመንፈሳዊ

ጉባኤው ሳኩ፡፡ ቀድሞ በመከራ ዘመን የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ባደረገችው ፊትን የማዞር ድርጊት፤ ከነጻነትም በኋላ ግዙቱን ላለማንሳት እየሰጠችው ባለው ሐሳፊነት የጎደለው መልስ፤ ከዚያም በላይ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ባስተላለፈው ውሳኔ ከፋኛ ያዘነው የመንፈሳዊ ጉባኤውም በመደበኛ አማካሪዎቹ አማካይነት አዲስ አበባ ላይ ሰፊ ውይይት ያዘ፡፡ በጉዳዩ ላይ በሰፋት ከተወያየበት በኋላም ሐምሌ 6 ቀን 1937 ዓ.ም አንድ ከባድ ውሳኔ አሳለፈ፡፡ ይኸውም «የግብፅ ቤተ ክርስቲያን እየተደረገ ባለው ውይይት ያሳለፈችውን ግዝት ታንሣ፡፡ ከአሁን በኋላም የግብፅን ቤተ ክርስቲያን እምነት ባንለውጥም ከግብፅ ምንም ዓይነት ሊቀ ጳጳሳትን አንፈልግም፡፡ በቋንቋችን የሚናገርና የሚያስተምር ሊቀ ጳጳሳት አንፈልጋለን» የሚል ነበር፡፡ የውሳኔው ሙሉ ቃል በዕጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ እንዲፈረምበት ከተደረገ በኋላ ለንጉሠ ነገሥቱ ተላከ፡፡

ከወራት በኋላም ኅዳር 9 ቀን 1938 ዓ.ም ጠቅላላ መንፈሳዊ ጉባኤው እንደ ገና ተሰበሰበ፡፡ በዚህም መሠረት ባለፉት ጊዜያት የተደረጉትን ውይይቶችና የተከናወኑትን ድርጊቶች ሪፖርት በመስማት በሐምሌ የአማካሪዎች ጉባኤ ያስተላለፈውን ውሳኔ በመቀበል ተጨማሪ የውሳኔ አሳቦችንና ማሳሰቢያዎችን በማስተላለፍ ተበተነ፡፡

በዚህ የሊቃውንቱ ቁራጥ በቋም የተነሣም በችግር ጊዜ ወደ ሀገራቸው ሸሽተው ሔደው የነበሩትና በኢትዮጵያውያን አባቶችና ሊቃውንት እንዲሁም አርበኞች ደም ሰላም ከመጣ በኋላ ተመልሰው መጥተው የነበሩት አቡነ ቄርሎስ ኢትዮጵያን ለቀው ሔዱ፡፡ ከላይ በተገለጠው ዓይነት የተላለፈው የመንፈሳዊ ጉባኤው የመጨረሻ ውሳኔ የደረሰው ቤተ መንግሥትም በጉዳዩ ላይ ከመከረ በኋላ ከመንፈሳዊ ጉባኤው አቋም ለየት ያለ አሳብ አቀረበ፡፡ ይኸውም ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን ጋር በዚህ ዓይነት ከምንለያይ ለተጨማሪ ውይይት ጊዜ መስጠት ይኖርብናል የሚል ነበር፡፡ ቤተ መንግሥቱ ይህንን አሳቡንም በዕጨጌ ገብረ ጊዮርጊስና በሌሎች ወኪሎቹ አማካይነት ለመንፈሳዊ ጉባኤው ገለጸ፡፡

የሊቃውንቱ ጉባኤ ምንም እንኳን «እስከ መቼ እንወያያለን?» በሚል በተወሰነ ደረጃ የቤተ መንግሥቱን ጥያቄ ላለመቀበል ተቃውሞ ቢያሰማም፤ በመጨረሻ ግን «ይሁን፤ ጥቂት ጊዜ ይሰጥ» በሚል ተስማማ፡፡ አቋሙ እንዳልተቀየረ፣ ጥያቄው ተግባራዊ ይሆን ዘንድ ብቻም ተጨማሪ ጊዜ እንደ ሰጠ በማግለጽ እንደ ገና በዕጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ፊርማ ለቤተ መንግሥቱ አቀረበ፡፡ በቀረበው ደብዳቤ የሚከተለው አሳብ ተካቶበታል፡፡



*... መላው ጉባኤ ለኢትዮጵያ የሚገቡት ነገሮች እንዲሰጡ፤ ሊቀ ጳጳሳትም ከኢትዮጵያ ተወላጆች ውስጥ እንዲመረጥ ማስፈለጉን ተስማምቶበታል፡፡ ይኸውም አሳብ በመንግሥታችን ወገን የተደገፈ ስለሆነ መንግሥታችን መልእክተኞችን ልኮ አሳቡን ለማስፈጸም የሚከናወንለት ከሆነ ጉባኤው ተቃዋሚ አይደለም፤ ስለዚህ የቤተ መንግሥታችን አሳብና ምኞት መልእክተኞቹን ልኮ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የጠየቀችውን ሁሉ ከእስክንድርያው ፓትርያርክ ተጠባባቂ ወይም ከጉባኤው ጋር በሰላም ለመጨረስ ስለሆነ ይህንኑ በቶሎ ከፍጻሜ እንዲያደርስላት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስተያን ግርማዊነትዎን በጸሎት እየደገፈች ትለምናለች፤ ነገር ግን ግርማዊነትዎ መልእክተኞችን ልኮ ከአሁን በፊት በዚሁ ነገር ቤተ ክህነት የደከመችውን ያህል በንገሩ ደክመውበት ከእስክንድርያው ፓትርያርክ ተጠባባቂ ወይም ከጉባኤው ፍሬ ያለው ምላሽ ያልተገኘ እንደ ሆነ ግርማዊነትዎ የተስማማ እንደሆነ ባለመጠራጠር እናምናለን፡፡*

ቤተ መንግሥቱም ይህንን የመሰለ ጠንካራ ማሳሰቢያ ከቤተ ክርስቲያኗ ሊቃውንት ከተቀበለ በኋላ በጉዳዩ ላይ ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን ጋር መክረው የኢትዮጵያን ጥያቄ ያስፈጽሙ ዘንድ ክቡር ፊታውራሪ ታፈሰ ሀብተ ሚካኤልንና ብላታ መርሥዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስን ጥር 1 ቀን 1938 ዓ.ም ወደ ካይሮ ላከ፡፡ ልዑኩ ወደ ዚያ ሲሔድ ከንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ ለፓትርያርኩ የተጻፈ ደብዳቤ ይዞ ነበር፡፡ ጉዳዩ በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ዘንድ ተጠናክሮ መቀጠሉን የሰማው የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ሲኖዶስ ግን ኢትዮጵያውያኑ ልዑካን ካይሮ ከመድረሳቸው በፊት አንድ ውሳኔ አሳለፈ፡፡ ይኸውም ከሚሾሙት ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ጋር ሁለት የግብፅ ጳጳሳትም ተሹመው ወደ ኢትዮጵያ ይምጡ የሚል ነበር፡፡

ከባድና ታሪካዊ ተልዕኮ ይዘው የሔዱት ሁለቱ ልዑካንም ካይሮ እንደ ደረሱ ውሳኔው ተገለጸላቸው፡፡ ይሁን እንጂ በቀረበላቸው ውሳኔ ባለ መስማማት ክርክራቸውን ቀጠሉ፡፡ ከብዙ ክርክርና ውይይት በኋላም የግብፅ ቤተ ክርስቲያን የኢትዮጵያን ጥያቄ እንደ ተቀበለች፤ በጥያቄው መሠረትም የኢትዮጵያውያኑ አባቶች ሹመት በግንቦት ወር ከሚደረገው የአዲሱ ፓትርያርክ ሹመት ጋር እንደሚፈጸም፤ ስዚያም አምስት አባቶች ተመርጠው እንዲላኩ ለልዑካኑ ተገለጸላቸው፡፡

በውሳኔውም መሠረት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃው

ንት በዕውቀትና በምግባር የተመሰከረላቸውን አምስት ሊቃውንት መርጠው በፊታውራሪ ታፈሰ ሀብተ ሚካኤልና በብላታ መርሥዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ መሪነት ሚያዝያ 28 ቀን 1938 ዓ.ም ወደ ካይሮ ላኩ። የግብፅ ቤተ ክርስቲያን አስቀድማ በገባችው ቃል ኪዳን መሠረት የግብፅ 115ኛ ፓትርያርክ ከሆኑት አቡነ ዮሳብ ጋር ግንቦት 2 ቀን 1938 ዓ.ም ሊሾሙ ወደ ካይሮ የገሠገሡት አባቶች በሰላም ገብተው ዝግጁነታቸውን ገለጡ። ነገር ግን ባልጠበቁት ሁኔታ በግብፆች የተዘጋጀና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሙሉ በሙሉ ነጻነቷን እንዳታውጅ የሚያደርግ ሰነድ ቀረበላቸው። ሰነዱም የሚሾሙት ጳጳሳት ወደ ኢትዮጵያ ሲመለሱ ሌላ ኤጲስ ቆጶስ እንዳይሾሙ የሚያግድ ሲሆን እትዮጵያውያኑ አባቶች ከመሾማቸው በፊት እንዲፈርሙበት ይጠይቃል።

የግብፆችን ተንኮል በሚገባ የተረዱት አባቶችም ሲኖዶሱ ያሳለፈውን ውሳኔ ባለመቀበል ተቃውሞአቸውን በፊታውራሪ ታፈሰ ፊርማ ለተጠባባቂ ፓትርያርኩ አሳወቁ። ወዲያውኑም ሲኖዶሱ ያቆያቸውን ውሳኔ በተጠባባቂ ፓትርያርኩ በኩል ለግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እንዲላክ አደረጉ። ንጉሠ ነገሥቱም ውሳኔውን በሚገባ ከመረመሩ በኋላ ኢትዮጵያ የማትስማማባቸውን ነጥቦች በዝርዝር በማስቀመጥ ኢትዮጵያውያኑ ልዑካን ከፓትርያርኩ ጋር ይወያዩባቸው ዘንድ ለፊታውራሪ ታፈሰ ላኩላቸው። ይህንን እንዳደረጉም ለፓትርያርኩ በደብዳቤ አሳወቁ። የንጉሡ ደብዳቤ የደረሳቸው ተጠባባቂ ፓትርያርክም ለንጉሡ የመልስ ደብዳቤ ከጻፉ በኋላ ከልዑካኑ ጋር የጋራ ስብሰባ አድርገው ተወያዩ። ከውይይቱም በኋላ ኢትዮጵያውያኑ አባቶች አዲሱ ፓትርያርክ ከመሾማቸው በፊት ሊሾሙ አይቻልም ከሚል ውሳኔ ላይ ስለ ደረሱ እና አንዳንድ ተጨማሪ ግልጽ ያልሆኑ አሳቦች ስለ ነበሩ ተጠባባቂ ፓትርያርኩን በመሰናበት ከወራት ፍሬ ቢስ ቆይታ በኋላ ሐምሌ 29 ቀን 1938 ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ ተመለሱ። በዚህ የተነሣ ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን ጋር የነበረው ግንኙነት ለሁለት ዓመታት ያህል ተቋረጠ። ይህንን በያሉበት ሆነው የሰሙት ኢትዮጵያውያኑ ሊቃውንትና መምህራን ምንም እንኳን እንደ ለፉት ዓይነት ጉባኤያት አድርገው ባይወያዩም በያሉበት ሆነው ድምፃቸውን ሲያሰሙ ቆዩ።

የሊቃውንቱ ድምፅ ከፍ እያለ እንደ ገና ጉባኤ ወደ መጥራት አዝማሚያ ሲደርስ ሐምሌ 9 ቀን 1940 ዓ.ም የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ አቡነ ዮሳብ ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥቱ አንድ መልእክት ላኩ። መልእክቱም የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ኢትዮጵያውያኑን አባቶች ለመሾም መወሰኗን የሚገልጥ ነበር። በዚህም መሠረት ከሁለት ዓመታት በፊት ተመርጠው ይሾሙ ዘንድ ወደ ካይሮ ሔደው የነበሩት አምስት አባቶች እንደ ገና ወደ ካይሮ ሔዱ።



እንደ ደረሱም ኢትዮጵያውያኑ በተስማሙበት አንድ ፕሮቶኮል ላይ ፈርመው ሐምሌ 18 ቀን 1940 ዓ.ም ካይሮ ላይ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሳብ እጅ ተቀብተው ጳጳሳት ሆኑ። ከተፈራረሙበት ፕሮቶኮል ውስጥ «አንድ ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳሳት ከመሾሙ በፊት አሁን በአፌሴል ሊቀ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ተብለው የሚታወቁት ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ ማረፍ አለባቸው» የሚል ይገኝበታል።

ሐምሌ 18 ቀን 1940 ዓ.ም ሥርዓተ ሢመት ተፈጽሞላቸው ሐምሌ 22 ቀን 1940 ዓ.ም አዲስ አበባ የገቡት ኢትዮጵያውያን አባቶች የሚከተሉት ነበሩ።

1. ብፁዕ ዕጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ :- አቡነ ባስልዮስ፤
2. መምህር ገሪማ ወልደ ኪዳን:- አቡነ ሚካኤል፤
3. ሊቀ ሥልጣናት መልእክቱ ወልደ ማርያም:- አቡነ ቴዎፍሎስ፤
4. መምህር ዘፈረ ብርሃን ገብረ ጻድቅ:- አቡነ ያዕቆብ፤
5. መምህር ጌታሁን ወልደ ሐዋርያት:- አቡነ ጢሞቴዎስ፤

ከሦስት ዓመታት በኋላ ግብፃዊው የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ቄርሎስ ሲያርፉ ቀደም ሲል በተፈረመው ፕሮቶኮል መሠረት ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ በብፁዕ አቡነ ዮሳብ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ሆነው ተሾሙ። ይህም ለዘመናት እልህ አስጨራሽ ክርክር ላደረገችው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንና ቤተ መንግሥት ከፍ ያለ ደስታን ፈጠረ።

ብፁዕነታቸው የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ሆነው በተሾሙ ጊዜ የያኔው አለቃ መሐሪ ትርፌ /በኋላ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ/ የሚከተለውን ዋዜማ ቅኔ ተቀኝተውላቸው ነበር።

*ይግባዕ ተጎፊሮ ዘበኒቅዮ ቀነጸ ነዳየ አእምሮ መንፈስ*

*ባስልዮስ አምግነ ገዘማ ለሥርዋፅ በለስ*

*እስከነ በጎዳግ ይጸሐፍ ሥርዋፀ ዚአሁ ሐዲስ*

*ከመስ ኢንበል በመጽሐፍ ቅዱስ*

*ሥርዋፅነ ማኅበቅት ወርእስ።*

ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ይህንን ታላቅ መዓርግ ተቀብለው ወደ አዲስ አበባ ሲመለሱ ከፍ ያለ አቀባበል ተደረገላቸው:: በነበራቸው ሥልጣንም ነሐሴ 28 ቀን 1943 ዓ.ም ተመርጠው የቀረቡ አምስት አባቶችን ጳጳሳት አድርገው ሾሙ:: በዚህ ዕለት የተሾሙት አባቶችም የሚከተሉት ነበሩ::

1. መምህር ዘፈረ ብርሃን፤ አቡነ ታዴዎስ ተብለው፤ የጐሬ ጳጳስ፤
2. ጸባቴ ተክለ ጊዮርጊስ፤ አቡነ ገብርኤል ተብለው፤ የወሎ ጳጳስ፤
3. ሊቀ ሊቃውንት ገብረ እብ፤ እቡነ ፊልጰስ ተብለው፤ የኢየሩሳሌም ጳጳስ፤
4. መምህር ገብረ አምላክ፤ አቡነ ማርቆስ ተብለው፤ የኤርትራ ጳጳስ፤
5. መምህር ገብረ ጊዮርጊስ፤ አቡነ ጎርጎርዮስ ተብለው፤ የከፋ ጳጳስ፤

ከላይ ከተጠቀሱት እባቶች ውስጥ በኤርትራ የተሾሙት መምህር ገብረ አምላክ በጠላት ወረራ ዘመን በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት መራጭነት በብፁዕ አቡነ እብርሃም ከተሾሙት አባቶች አንዱ ሲሆኑ በዚህኛውም ያው ጰንቶላቸው ተሹመዋል:: እንዲሁም በቁጥር 4 እና 5 የተቀመጡት አባቶች ብፁዕ አቡነ አብርሃም ካረፉ በኋላ ብፁዕ እቡነ ዮሐንስ ሊቀ ጳጳሳት ሲሆኑ መስከረም 1 ቀን 1932 ዓ.ም የሾሟቸው ነገር ግን ከላይ በተገለጠው ዓይነት ስሁለቱ ሀገራት ፖለቲካዊ ግንኙነት ሥምረት ሲባል ከሥራ ታግደው የቆዩና በዚህኛው ዓመት ሹመታቸው የጸናላቸው ናቸው::

ከእራት ዓመታት በኋላ የትግሬ ጳጳስ የነበሩት ብፁዕ እቡነ ይስሐቅ ነሐሴ 3 ቀን 1947 ዓ.ም ዐረፉ:: በዚህም የተነሣ ሐምሌ 21 ቀን 1948 ዓ.ም በወቅቱ የአክሱም ንቡረ ዕድ የነበሩት ንቡረ ዕድ ገብረ መስቀል በብፁዕ እቡነ ባስልዮስ እንብሮተ ዕድ እቡነ ዮሐንስ ተብለው ተሹመው የትግሬ ጳጳስ ሆኑ::

በዚህ ዓይነት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እንደ ፍላጐቷና እንደ ሕዝቧ ጥያቄ ኤጲስ ቆጶሳትንና ጳጳሳትን እየሾመች ለአገልግሎት በማሠማራት የስብከተ ወንጌል አገልግሎቷን ማስፋፋቷን ቀጠለች:: ይህ በእንዲህ እንዳለም በ1948 ዓ.ም በግብፅ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ አባላት መካከል መስየየት ተከሰተ:: በዚህም የተነሣ ፓትርያርኩን በተቃወሙ እባላት ምክንያት የግብጽ ቤተ



ክርስቲያን ፓትርያርክ የነበሩትና የሁለቱን አኀት አብያተ ክርስቲያናት ግንኙነት ወደ ላቀ ደረጃ ያደረሱት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሳብ ከመንበረ ፓትርያርክነታቸው ተነሡ:: የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ይህንን ድርጊት በመቃወም ድምፅዋን አሰማች:: አንድ በጉዳዩ መክሮ የሚመለስ ልዑክም ወደ ካይሮ ላከች:: ይሁን እንጂ ፓትርያርኩን ከመንበራቸው ባወረዷቸው አባቶች እምቢታ የተነሣ ልዑኩ ያለ ውጤት ተመለሰ::

በመጨረሻም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ነገሩን አቅልላ ባለማየትና በግብፅ ቤተ ክርስቲያን የአስተዳደር ጉዳይ ያላትን ቦታ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ሰባት አባላት ያሉት የብፁዓን ጳጳሳት ልዑክ ወደ ካይሮ ላከች:: ልዑኩም በቀጥታ ፓትርያርኩ ተቀምጠውበት ወደ ነበረው ገዳመ ቊስቋም በመውረድ በፓትርያርኩ ወገን ከነበሩት ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጳሳት ጋር በመሆን በሁኔታው ላይ ሰፊ ውይይት አደረገ:: በውይይቱ መጨረሻም ፓትርያርኩ ወደ መንበራቸው እንዲ መለሱ የሚል የጋራ ውሳኔ እሳለፉ:: በውሳኔውም መሠረት ኢትዮጵያውያኑ ጳጳሳት ከግብፃውያኑ ጳጳሳት ጋር በመሆን ፓትርያርኩን ይዘው ወደ ካይሮ ሲሔዱ ፓትርያርኩ ወደ መንበራቸው መመለስ እንደማይችሉ ተገለጸላቸው:: ኢትዮጵያውያኑ እባቶች ከዚህ በኋላ ምንም ሊያደርጉ እንደማይችሉ በመገን ዘባቸው ወደ ሀገራቸው ተመለሱ::

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ልዑኳ ካለ ፍሬ ከተመለስ በኋላ ጉዳዩን በርቀት እየተከታተለች መፍትሔ የሚገኝበትን መንገድ ስታፈላልግ ፓትርያርኩ አቡነ ዮሳብ ኅዳር 4 ቀን 1949 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት እንደ ተለዩ ተሰማ:: በዚህም መሠረት በእርሳቸው መንበር የሚተካውን ፓትርያርክ ለመምረጥ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መራጭ ወኪሎችን እንድትልክ ሀቃቤ መንበር ሆነው በተመረጡት አቡነ አትናቴዎስ አማካይነት ግብዣ መጣላት:: ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ «የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በፓትርያርክ ምርጫ ላይ ያላት አግባብ በግልጽ ያልተወሰነ በመሆኑ፤ ባለፉት ፓትርያርክ ላይም ያደረጋችሁት አድራጐት ጥሩ ባለመሆኑ እናዝናለን» በማለት ግብዣውን እንደ ማይቀበለው አሳወቀ::

የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ አቡነ ቄርሎስን 116ኛ ፓትርያርክ አድርጐ ሾመ:: በዚህ የተነሳም በኢትዮጵያና በግብፅ አብያተ ክርስቲያናት መካከል የነበረው ግንኙነት ተቋርጦ ቆየ:: ነገር ግን ከጥቂት ጊዜያት በኋላ አዲሱ ፓትርያርክ ባልተጠበቀ ሁኔታ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን መዓርግ ወደ ፓትርያርክነት ደረጃ ከፍ ለማድረግ ያሰቡ መሆናቸውን የሚያትት ደብዳቤ

አስይዘው ሦስት ጳጳሳትንና አራት ምእመናንን ወደ እዲስ አበባ ላኩ።

መልእክተኞችም አዲስ አበባ ላይ ከቤተ ክህነትና ከቤተ መንግሥት ሰዎች ጋር ሰፊ ውይይት ሲያደርጉ ከሰነበቱ በኋላ ወደ አንድ ስምምነት በመድረሰ የውል ሰምምነት በሁለቱ አብያተ ክርሰቲያናት መካከል ተፈረመ። በስምምነቱም መሠረት በወቅቱ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት የነበሩት ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ሰኔ 21 ቀን 1951 ዓ.ም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቄርሎስ ተቀብተው የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ሆነው ተሾሙ። በሥነ ሥርዓቱም ላይ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ተገኝተው ነበር።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባሰልዮሰ ለእርሳቸውም ሆነ ለሀገራችን የመጀመሪያ የሆነውን ሥልጣነ ፓትርያርክነት ይዘው ሐምሌ 4 ቀን 1951 ዓ.ም አዲስ አበባ ገቡ። በዚህም ወቅት 21 ጊዜ መድፍ ተተኮሰ፤ በአዲስ አበባ የሚገኙ አድባራትና ገዳማትም በደወል ድምፅ ደስታቸውን አሰሙ። ምእመናንም በእልልታ አጀቧቸው።

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የኢትዮጵያ እርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሙሉ ነጻነቷን ዐውጃ፣ ከራሷ ልጆች ሰዚህ ታላቅ አደራና ሐላፊነት የሚበቁትን አየመረጠች፣ ሰአገልግሎትም እያሰማራች ሕዝቧን በማሰተማርና በመባረክ ላይ ትገኛለች።



# ምዕራፍ ሁለት

# 2. ዜና ፓትርያርኮች

## 2.1. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ቀዳማይ ፓትርያርክ /1884 - 1963 ዓ.ም/



ዕጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ይባሉ የነበሩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ የአጥቢያው መሪ ጌታ ከነበሩት አባታቸው ከደብተራ ወልደ ጻድቅ ስሎሞን፤ ከእናታቸው ከወይዘሮ ወለተ ማርያም ባዩ /በኋላ አማሆይ/ በሰሜን ሸዋ ህገረ ሰብከት፣ በመርሐ ቤቴ አውራጃ ሚዳ ሚካኤል ከተባለው ቦታ መጋቢት 14 ቀን 1884 ዓ.ም ተወለዱ:: እንደ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት በዓርባ ቀናቸው ኪሶ ማርያም በተባለች በአጥቢያቸው ቤተ ክርስቲያን ተጠምቀው ገብረ ጊዮርጊስ ተብለው ስመ ክርስትና ተሠየሙ:: አባታቸው ባደረባቸው ሕመም ገና ከመወለዳቸው በፊት በማረፋቸው ወዲያውኑ ከመነኩሱት እናታቸው ጋር በክብካቤ አደጉ:: ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስም በዚያው በትውልድ ቀዬአቸው በምትገኘው አመልሳ ኪሶ ማርያም በተባለቸው ደብር ግብረ ዲቁና ተምረው ከግብፃዊው የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ማቴዎስ መዓርገ ዲቁና ከተቀበሉ በኋላ በዚያው አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሲያገለግሉ ቆዩ::

ዕድሜያቸው 14 ዓመት ሊሆንም ወደ ፊት ለሚጠብቃቸው ከፍተኛ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የትምህርት እና የሥነ ምግባር ዝግጅታቸውን ሊቀጥሉ ወደ ታላቁ ገዳም ደብረ ሊባኖስ ሔዱ:: በዚያም ሁለተኛውን ደረጃ መንፈሳዊ ትምህርት /ጸዋትወ ዜማ/ ተምረው አጠናቀቁ:: በመቀጠልም የቅኔና የመጻሕፍት ትርጓሜ ትምህርታቸውን ከመምህር ገብረ ኢየሱስ ተምረው በሁለቱም ተመረቁ:: ከዚህም ጋር የቅዳሴውን ትምህርት አባ ገብረ ሕይወት ከተባሉት አባት በሚገባ ተማሩ::

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ በተማሪነት ዘመናቸው በምግባራቸው እጅግ ትሑት እና ለትልቅ ለትንሹ ታዛዥ ስለ ነበሩ በመምህሮቻቸውና በጓደኞቻቸው እጅግ ፍቅርን የሚቸሩና የሚከበሩ ነበሩ::

ቅዱስነታቸው በዚህ ዓይነት ትምህርታቸውን በማስፋፋት፡ በገዳሙ ውስጥም በረድዕነት እየገለገሉ ሥርዓተ ገዳምን ሲማሩ ከቆዩ በኋላ ነሐሴ 24 ቀን 1905 ዓ.ም ልክ በሃያ አንድ ዓመታቸው በዚያው በደብረ ሊባኖስ ገዳም ሥርዓተ ምንኩስና ተፈጸመላቸው:: በዓመቱ በ1906 ዓ.ም ደግሞ ከግብፃዊው የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ማቴዎስ መዓርገ ቅስና ተቀበሉ:: ቅዱስነታቸው ሥልጣነ ክህነት ከያዙ በኋላ በዚያው በገዳሙ የደከሙ አባቶችን በመርዳት፣ ሥርዓተ ገዳሙን በመጠበቅና በማስጠበቅ ለዓመታት ሲያገለግሉ ቆዩ:: ከዚያም በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ከደብረ ሊባኖስ ተነሥተው ወደ ዓባይ ሸለቆ በመውረድ ዋሻ ሚካኤል በተባለ ቦታ ለሦስት ወራት ዘግተው በብሕትውና ቆዩ::

ከዚህ በኋላ በ1909 ዓ.ም በመጋቢት ወር በፍጹም



ብሕትውና ሊጸልዩ ከቆዩበት ዋሻ መንፈስ እግዚአብሔር አነሳሥቷቸው በርካታ ባሕታውያን በምናኔ ይኖሩበት ወደ ነበረው የመናገሻ ጋራ በመውጣት በዚያ የተባሕትዎ ሕይወታቸውን ቀጠሉ:: ከዚህም ጋር በጋራው የመድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ስለ ነበር በዚያ የቤተ መቅደስ አገልግሎትም እየሰጡ በትጋት ማገልገል ጀመሩ:: ይህ ደገኛ ተግባራቸው አብረዋቸው በሚኖሩት ባሕታውያንና በአካባቢው ምእመናን ዘንድ እየታወቀ ቅዱስነታቸውም በአገልግሎታቸው እየበረቱ ይህም ከአካባቢው አልፎ እስከ ቤተ መንግሥቱ ደረሰ:: በዚህ የተነሣም በ1910 ዓ.ም በግንቦት ወር ወደ ቤተ መንግሥት ተጠሩ:: ጥሪውን አክብረው ሊቀርቡም ግርማዊት ንግሥተ ንግሥታት ዘውዲቱ በመናገሻ ጋራ ላይ ያሉ ባሕታውያን በተበታተነ ሁኔታ መኖራቸውን አቁመው በማኅበር እየኖሩ ለሀገር ለወገን እንዲጸልዩ መፈለጋቸውን፣ ለማኅበሩ መመሥረት እንዲረዳም በጋራው ላይ የእመቤታችንን ቤተ ክርስቲያን ሊያሠሩ እንዳሰቡ፣ በሚመሠረተው ገዳምም ሆነ ቤተ ክርስቲያን ላይ በእልቅና እንደ ሚሾሟቸው፤ እስከዚያ ድረስ ግን ባሕታውያኑን በማሰባሰብ ሊያበተምሩ እና ሊመክሩ እንዲቆዩ አሳሰቧቸው::

ቅዱስነታቸውም የንግሥቷን ሐሳብ በሙሉ ፈቃደኝነት ተቀብለው ባሕታውያኑን እያስተማሩ ባለው የመድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ማኅበሩን መመሥረት ጀመሩ:: በዚህ እንቅስቃሴ ላይ እያሉም ንግሥቷ ያሠሯት የእመቤታችን ቤተ ክርስቲያን በመጠናቀቋ በ1916 ዓ.ም የገዳሟ መምህር ሆነው ተሾሙ:: ቅዱስነታቸው ይህን የመሰለውን የትሩፋት ሥራ ለመሥራት ዕድሳቸው በለሆነ የቤተ መቅደሱን አገልግሎት በትጋት ከመስጠት ጋር ራሳቸውም ቅዳሴ ከማስተማር ጋር ሌሎች ጉባኤያት በገዳሙ እንዲዘረጉ፣ ማኅበረ መነኮሳትና ባሕታውያኑም ገዳሙን በማልማት እንዲተጉ ማድረጋቸውን ቀጠሉ:: በዚህ ዓይነት አገልግሎታቸውን በብቃት በማበርከት ላይ ሳሉ የካቲት 27 ቀን 1924 ዓ.ም ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ወደ ቤተ መንግሥት ጠሯቸው:: ንጉሡም ለምግባራቸውና ለአገልግሎታቸው ያላቸውን አድናቆት በመግለጽ፤ የመናገሻ ማርያም ገዳምን መምህርነት እንደ ያዙ የአዲስ አበባ መንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤልን ደብር አለቅነት ሾሟቸው::

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስም ሹመቱን በትሕትና ተቀብለው ሁለቱንም ቅዱሳት መካናት በትጋት ማስተዳደር ጀመሩ:: ይሁን እንጂ በዚህ ዓይነት ለሁለት ዓመታት ከቆዩ በኋላ በ1925 ዓ.ም ኅዳር ወር የከተማው ኑሮ ሊኖሩት ካሰቡት የትኅርምት ሕይወት ጋር ሊጣጣምላቸው ባለመቻሉ ግርማዊነታቸውን ከልመና ጋር አስፈቅደው የመንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ሹመታቸውን በማ

ሰረከብ ወደ መናገሻ ገዳም መምህርነታቸው ሙሉ በሙሉ ተመለሱ::

ቅዱስነታቸው በመናገሻ ተቀምጠው ቤተ ክርስቲያናቸውን እያገለገሉ በጾምና በጸሎት እየተጉ መኖር ፍላጎታቸው ቢሆንም ብዙም ሳይቆዩ እግዚአብሔር ወደ ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ሔደው እንዲያገለግሉ ፈቅዷልና መጋቢት 12 ቀን 1926 ዓ.ም በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት ራይስ ሆነው ተሾሙ::

ብፁዕ ውቅዱስ አቡነ ባስልዮስ በመናገሻ ማርያም ገዳም የጀመሩት አገልግሎትና በዚያ ያሉ ማኅበረ መነኮሳት ፍቅር ቢያስቅ ቃቸውም፤ ንጉሡ ከመከሯቸው ምክርና ከጣሉባቸው አደራ ታላቅነት ጋር የተሾሙበት ቦታ ቅድስና ስለ ከበዳቸው ሹመቱን በእኩቴት ተቀብለው ወደ ኢየሩሳሌም ሔዱ:: በዚያም መቀመጫቸውን ከታላ ቁ የኢትዮጵያ ገዳም ዴር ኤል ሡልጣን ገዳም አድርገው የተሾሙባ ቸውን ዘጠኝ የኢትዮጵያ ገዳማት በሚገባ ሲያስተዳድሩ ቆዩ::

ከሁለት ዓመታት በኋላ ቅዱስነታቸው የካቲት 11 ቀን 1929 ዓ.ም ከግርማዊነታቸው በተጻፈ የቴሌግራም መልእክት በአስቸ ኳይ ወደ አዲስ አበባ እንዲመጡ ተጠሩ:: ቅዱስነታቸው ጥሪውን በመቀበል ከ10 ቀናት የባቡርና የመኪና ጉዞ በኋላ የካቲት 21 ቀን አዲስ አበባ ገብተው ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥቱ ፊት ቀርበው እጅ ነሡ:: ከዚያም ማረፊያ ተሰጥቶአቸው ለሦስት ቀናት ከቆዩ በኋላ ለዕጨጌነት መዓርግ ታጭተው ኖሮ አዲስ አበባ በገቡ በአራተኛው ቀን /የካቲት 24/ የጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ወርኃዊ መታሰቢያ ዕለት በግርማዊነታቸው መልካም ፈቃድ «ብፁዕ ዕጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ዘነበረ በመንበረ ተክለ ሃይማኖት» ተብለው የታላቁ የደብረ ሊባኖስ ገዳም 59ኛ እጨጌ ሆነው ተሾሙ::

ይሁን እንጂ ቅዱስነታቸው በታላቁ መንበር ተቀምጠው አገልግሎታቸውን ገና ከመጀመራቸው ወራሪው የኢጣሊያ ጦር በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል በኩል ኢትዮጵያን በግፍ መውረሩ ተሰማ:: ይህን የሰሙት ግርማዊ ጃንሆይም መኳንንቱንና መሣፍንቱን አስከት ለው ወራሪውን ኃይል ለመመከት ወደ ማይጨው ቢወርዱ ቅዱስነ ታቸውም ከሌሎች የቤተ ክርስቲያን አባቶች ጋር የቃል ኪዳኑን ታቦት ይዘው ወደ ማይጨው ጦርነት ወረዱ::

ምንም እንኳን ከንጉሡ ጀምሮ በግንባሩ የነበሩት መላው የኢትዮጵያ አርበኞች በቆራጥነት ቢዋጉም ጠላት በተጠቀመበት የመርዝ ጋዝ የተነሣ በማይጨው ጦርነት ድል ለኢትዮጵያውያን ልትሆን አልቻለችም:: በዚህ ጦርነት የቅዱስነታቸው በቅሉ ከጠላት በተተኮሰ ጥይት ተመትታ እንደ ነበር ይነገራል::

በዚህ ጊዜ የጠላት ጥይትና የመርዝ ጋዝ የበለጠ ብዙ ሰው



ከሚፈጅ ወደ ኋላ መመለሱ የተሻለ እንደ ሆነ የቤተ ክህነቱም ሆነ የቤተ መንግሥቱ ባለሥልጣናት ሐሳባቸውን ለንጉሡ ቢያቀርቡም ንጉሡ እዚሁ እሞታለሁ ብለው እንቢ አሉ ይባላል:: ይሁን እንጂ በንጉሡም ሆነ በቤተ ክህነቱ ከፍተኛ ተሰሚነት የነበራቸው ቅዱስነታቸው፤ ግርማዊ ቀዳማዊ ዓፄ ኃይለ ሥላሴ ምክሩን በእሺታ ተቀብለው ወደ አዲስ አበባ እንዲመለሱ አድርገዋል ይባላል:: ንጉሠ ነገሥቱ ሐሳቡን ተቀብለው እንዲመለሱም አውግዣለሁ ብለው ነበር ይባላል::

በዚሀ ዓይነት ንጉሡና ተከታዮቻቸው የበላይነትን ማግኘት ባለመቻላቸው ወደ አዲስ አበባ ሲመለሱ ቅዱስነታቸውም አብረው ተመለሱ:: አዲስ አበባ እንደ ደረሱም በነበራቸው ቅርበት በአገር ውስጥ መቆየታቸው ጉዳት እንጂ ጥቅም እንደ ሌለው ይልቁንም ወደ ውጭ ሔደው ለኃያላኑ መንግሥታት በሀገራቸውና ሕዝባቸው የተፈጸመባቸውን የግፍ ተግባር እንዲያስረዱ በመምከር ግርማዊ ቀዳማዊ ዓፄ ኃይለ ሥላሴ ከሀገር እንዲወጡ አደረጉ:: እርሳቸውም ሰደተኛውን ታቦት ይዘው አብረው ወጡ:: ግርማዊ ንጉሠ ነገሥቱ ከኢትዮጵያ እንደ ወጡ ያመሩት ወደ ኢየሩሳሌም ነበር:: በዚያም ጥቂት ቆይታ አድርገው ወደ ታላቋ ብሪታንያ ሲሔዱ ቅዱስነታቸው ከእቴጌ መነንና ንጉሡን ተከትለው ከሔዱ ሌሎች መኳንንትና መሣፍንት እንዲሁም ታማኝ ወታደሮች ጋር በዚያው ቀሩ::

ንጉሡ ወደ ለንደን ከሔዱ በኋላ ቅዱስነታቸው ከእቴጌና ሌሎች መኳንንት ጋር በመሆን ከጸሎት ጀምሮ ለኢትዮጵያ ነጻነት መመለስ መሆን ያለበትን ሁሉ ማድረግ ጀመሩ:: በዚህም ለንደን በሚገኙት ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትና በሀገር ውስጥ ከጠላት ጋር የሞት ሽረት ትግል እያደረጉ ባሉት አርበኞች መካከል ሆኖ መረጃ የሚያቀብል አንድ የ«ኢትዮጵያውያን ሰደተኞች ማኅበር» እንዲ ቋቋም አደረጉ:: በተጨማሪም ንጉሡም ባሉበት የሀገሪቱን ችግር ለዓለም ሕዝብ እንዲያሰሙ፡ ሀገር ቤት ያሉት አርበኞችም «ተጋድሎአችሁ ለሃይማኖታችሁ፣ ለሀገራችሁ፣ ለባንዲራችሁ ነው:: በዚህም ብታልፉ ሰማዕታት ናችሁ:: በጉንፋንና በወረርሽኝ የምትወሰድ ነፍሳችሁን ለሀገራችሁ አትንፈጓት:: በርቱ!!» የሚሉ ደብዳቤዎች በራሳቸው እጅ እየጻፉ ወደ ኢትዮጵያ ይልኩ ነበር:: ለንደን ላይ ሀገራቸው ኢትዮጵያ በግፍ መወረሯን በቻሉት መንገድ ሁሉ ለዓለም ማኅበረሰብ ሲያሰሙ የነበሩት ንጉሠ ነገሥቱም በኢየሩሳሌም ይገኝ የነበረውን ታቦተ መድኃኔ ዓለምን /ስደተኛው መድኃኔ ዓለም - በአዲስ አበባ ምስካዬ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ገዳም የሚገኝ/ ከቀዳሲያን ካህናት ጋር ወደ ለንደን እንዲ ልኩላቸው ለቅዱስነታቸው ላኩባቸው::

ቅዱስነታቸውም ሳይውሉ ሳያድሩ ታቦተ መድኃኔ ዓለምን በአባ ሐና ጅማ አማካይነት ከአምስት ካህናት ጋር ላኩላቸው:: ይህ ታቦት ወደ ኢየሩሳሌም የሔደው በ1895 ዓ.ም በዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ ትእዛዝ መምህር ፈቃደ እግዚእ የተባሉ መምህር በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ገዳማት ራይስ ሆነው ሲሔዱ እንደ ነበር ይነገራል::

ኢትዮጵያ ከአምስት ዓመታት ወረራ በኋላ በብሪታንያ ርዳታ ነጻ እንደ ምትወጣ ከስምምነት ላይ ሲደረስ ንጉሡ ከብሪታንያ ገሥግሠው ሱዳን ደረሱ:: ይህን የሰሙት ቅዱስነታቸው፣ ሰኔ ዘጠኝ ቀን 1932 ዓ.ም ከክቡር ፊታውራሪ ብሩና ከሌሎችም ታላላቅ መኳንንት ጋር ከኢየሩሳሌም ተነሥተው ወደ ሱዳን በመጓዝ ከግርማዊነታቸው ጋር ተገናኙ:: በሱዳን ቆይታ ካደረጉ በኋላ ንጉሡ በድል አድራጊነት ወደ ኢትዮጵያ ጉዟቸውን ሲጀምሩ ቅዱስነ ታቸውም አብረው በመጓዝ ጥር 12 ቀን 1933 ዓ.ም ብዙዎች የተ ሠውላት ሰንደቅ ዓላማችን ኦሜድላ ላይ በግርማዊነታቸው ስትተከል ጸሎተ ቡራኬ አድርገዋል ይባላል:: ከዚያም በኋላ ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥቱ ሳይለዩ ከኦሜድላ ጀምረው ተጉዘው ሚያዝያ 27 ቀን 1933 ዓ.ም አዲስ አበባ ገቡ::

ነጻነት ተመልሶ ቤተ መንግሥቱ ሀገሪቱን የመገንባት መርሐ ግብር አውጥቶ ሲንቀሳቀስ ቅዱስነታቸውም በነበራቸው የዕጨጌነት ሥልጣንና ሐላፊነት ቤተ ክርስቲያኗን መልሶ የመገንባት እንቅስቃሴ ያቸውን ቀጠሉ:: በዚህ ረገድ በተለይ የሚጠቀሰው ሥራ በ1936 ዓ.ም ከንጉሡ ጋር በነበራቸው ቅርርብ ቤተ ክርስቲያኗ በወረራው ከደረሰባት ጉዳት እንድታገግም እና ለኢትዮጵያውያን የምትሰጠው አገልግሎት እንደ ቀድሞው የተሟላ እንዲሆን ከቤተ መንግሥቱ ርስት ጉልት እንድታገኝ አድርገዋል::

ቅዱስነታቸው ከዚህም ጋር በጠርነቱ ክፉኛ ወደ ተጎዱት አብያተ ክርስቲያናት ሔደው እየጎበኙና ካህናቱንና ምእመናኑን በምክር እያረጋጉ እንዲሁም የፈረሱት እንዲጠገኑ፣ የወደሙት እንዲ ተኩ ገንዘብ በመርዳት ሰፋ ያለ እንቅስቃሴ አድርገዋል:: በተለይ በ1935 ዓ.ም ቤተ ክርስቲያኗ ከነበራት ርስትና ጉልት የሚገኘው ገንዘብ በቀጥታ ወደ ቤተ ክርስቲያኗ ካዝና እንዲገባ መንግሥትን በማስፈቀድ በገንዘቡ በየአውራጃውና ወረዳው መምህራን እንዲቀጠ ሩና አብነት መምህራን ድጎማ እንዲያገኙ አድርገዋል::

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ከነጻነት በኋላ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት በጋራ ሆነው ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን ጋር ባደረጉት ሰፊና ረጅም ውይይት እንዲሁም ክርክር በሁለቱ አብያተ



ክርስቲያናት ታሪክ ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ካይሮ ሔደው ከተሾሙት ኢትዮጵያውያን አባቶች አንዱ በመሆን ሐምሌ 18 ቀን 1940 ዓ.ም «ብፁዕ አባ ባስልዮስ ጳጳስ ዘሸዋ ወለጨጌ ዘደብረ ሊባኖስ» ተብለው በእስክንድርያው ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሳብ አንብሮተ ዕድ ተሾሙ:: በወቅቱ ኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳቱም ከእኔ ይሁን ብላ የነበረ ቢሆንም፣ ይህ መሆን ያለበት በሕይወት ካሉት ከኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ግብፃዊው አቡነ ቄርሎስ ዕረፍት በኋላ ነው የሚል ስምምነት ተደርሶ ነበር:: ከአራት ዓመት በኋላ ግን አቡነ ቄርሎስ እንዳረፉ ሲሰማ ቀደም ሲል በተደረገው ስምምነት መሠረት ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ወደ ካይሮ ሔደው ጥር 6 ቀን 1943 ዓ.ም በአቡነ ዮሳብ አንብሮተ እድ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ሆነው ተሾሙ::

በሊቀ ጳጳሳትነት ቤተ ክርስቲያንን በስፋት ሲያገለግሉ የቆዩት ቅዱስነታቸው በእርሳቸው መልካም አስተዳደርና በቤተ መንግሥቱ ድጋፍ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሙሉ በሙሉ ነጻነቷን እንድታውጅ በመፍቀዷ ከ11 ዓመታት የሊቀ ጵጵስና አገልግሎት በኋላ ሰኔ 21 ቀን 1951 ዓ.ም ብፁዕ ወቅዱስ ተብለው የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ሆነው ተሾሙ::

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ በዘመነ ሥልጣናቸው ለቤተ ክርስቲያኗ ሰፋ ያለ አገልግሎት አበርክተዋል:: ቤተ ክርስቲያኗ በልማት እንቅስቃሴዋ እንድትጠናከር፣ ከዓለም ዐቀፉ ማኅበረሰብ ጋር የሠመረ ግንኙነት እንዲኖራት፣ ምእመናን በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን እንዲተዳደሩ፣ ቀደም ሲል ሥርዓት ሳልተሠራላቸውም ሥርዓት እንዲሠራላቸው በማድረግ /ለምሳሌ:- የልቅሶ ሥርዓት/፣ በቅዱስ ሲኖዶስ በብቃት እንድትመራ በማድረግ ሰፋ ያለ አገልግሎት አበርክተዋል::

ስስብከተ ወንጌል አገልግሎት መፋጠንም በ1948 ዓ.ም የስብከተ ወንጌል ድርጅትን ከማቋቋም ጋር በዘመነ ፓትርያር ክነታቸው አስራ ሰባት የሚደርሱ ኤጲስ ቆጶሳትን በመሾም፣ የቤተ ክርስቲያኗንም አህጉረ ስብከት ዓሥራ ስድስት በማድረስ ታላቅ ሥራን ሠርተዋል::

ቅዱስነታቸው የቤተ ክርስቲያኗ ኢኮኖሚያዊ እድገት እንዲፋጠን ከፍተኛ ፍላጎት ስለ ነበራቸው ማንም ይሥራው ማን እኔ ሳልፈቅድና ሳልመክርበት በሚል ስሥራ እንቅፋት እንዳልነበሩ በቅርብ የሚያውቋቸው ሊቃውንት ይመሰክራሉ:: በዚህ የተነሣ ከእሳቸው ጋር በነበሩ የቤተ ክህነቱ ሠራተኞች በርካታ የልማት ሥራዎች ተሠርተዋል:: በዚህ ረገድም ዛሬም ቤተ ክርስቲያኗን እያገለገሉ ያሉ ብዙዎቹ ሕንፃዎችና መኖሪያ ቪላዎች የተሠሩት

በእሳቸው የአገልግሎት ዘመን ነው:: ቅዱስነታቸው ሥራው ተጠናቅቆ ለቡራኬ ሲጠሩ ከቦታው ድረስ በመገኘት አባታዊ ቡራኬያቸውን ሰጥተው ሠራተኞቹን አመስግነውና አድንቀው ሽልማት ለሚገባው ሽልማት ሰጥተው ይመለሱ ነበር::

ወቅቱ በሚጠይቀው አስተዳደር. መሠረት ሹመት፣ ርስትና ጉልት ወዘተ. ፈልገው ወደ ጠቅላይ ቤተ ክህነቱ መጥተው ለረጅም ጊዜያት ደጅ ሲጠኑ የሚቆዩ ሊቃውንት ነበሩ:: ታዲያ እነዚህ ደጅ ጠኚዎች እንዳይቸገሩ ቅዱስነታቸው በየጊዜው ግብር እያደረጉ ይመግቡ፣ ማረፊያ እንዲያገኙም ያደርጉ ነበር ይባላል:: በተለይ ቅዱስነታቸው ከምንም በላይ ለቅድስናና ለሊቅነት ከፍተኛ ቦታ ይሰጡ ስለ ነበር በአካባቢያቸው በቅድስናቸውም ሆነ በሊቅነታቸው ለተመሰከረላቸው አባቶች ርስት ጉልት እንዲሰፈርላቸው ያደርጉ ነበር ይባላል:: በዚህ ረገድ በተለይ ደብረ ጽጌ ላይ ዛሬም ሲዘከር የሚኖር ሥራ እንደ ሠሩ ይነገራል::

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ በቤተ መንግሥቱ በነበራቸው ከፍተኛ ተቀባይነት የተነሣ በመኳንንቱና መሣፍንቱ፣ በልዕልታቱና ወይዛዝርቱ መካከል የሚፈጠርን ማንኛውንም ዓይነት ቅራኔ በቀላሉ ይፈቱና ዕርቅ ይመሠርቱ ነበር ይባላል:: በተለይ ከፖለቲካዊ ቅራኔ በመለስ ማንም ንጉሠ ነገሥቱ ግንባራቸውን መለሱብኝ የሚል ባለ ሥልጣን ምልጃን ሲሻ ሮጦ የሚመጣው ወደ እሳቸው ነበር ይባላል::

ቅዱስነታቸው ከቤተ መንግሥቱ ጋር የነበራቸውን ቅርርብና ታማኝነት በይፋ የመሰከረ ድርጊት የፈጸሙት በ1953 ዓ.ም የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ወቅት ነበር ይባላል:: በጄነራል መንግሥቱ ንዋይና ግርማሜ ንዋይ የተመራው የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ተፋፍሞ ቤተ መንግሥቱ በተናጋበት ጊዜ ቅዱስነታቸው ከመንበረ ፓትርያርክናቸው ሆነው «ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ዓፄ ኃይለ ሥላሴ የማትገዛ አውግዤሃለሁ፤ ጠብ መንጃህን ጣል» የሚል መልእክት ያዘለ ደብዳቤ ጽፈው በከተማዋ በሄሊኮፍተር እንዲበተን አድርገው ነበር:: ይህንን ውግዘታቸውን ተከትሎም ሁሉም ባይሆን መፈንቅለ መንግሥቱን ይደግፉ የነበሩ የክቡር ዘበኛ አባላት ጠብ መንጃቸውን ጥለዋል ይባላል:: በዚህ ጊዜ መፈንቅለ መንግሥቱን ይመሩ የነበሩት ሰዎች «ከጄኔራሎቹ የበለጠ እኛን የጎዳን ይህ መነኩሴ ነው» ብለው ነበር ይባላል:: መፈንቅለ መንግሥቱ ከከሸፈ በኋላም እንቅስቃሴውን ይደግፉ የነበሩ ሰዎችና ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ቅራኔ የነበራቸው አካላት ቅዱስነታቸውን የቤተ መንግሥቱ ቀኝ እጅ አድርገው ይመለከቷቸውና ይጠሏቸው ነበር ይባላል::

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ በቤተ ክህነቱም ሆነ በቤተ መንግሥቱ በነበራቸው ላቅ ያለ አገልግሎት የተነሣ የግርማዊ ቀዳማዊ ዓፄ ኃይለ ሥላሴን የመጀመሪያ የክብር ኮከብ ኒሻን ተሸልመዋል:: ይህ ኒሻን ቅዱስነታቸው ባረፉ ጊዜ ወደ ቤተ ክህነት ሳይሆን ወደ ቤተ መንግሥቱ ተመልሶ እንደ ገባ ይነገራል::




ቅዱስነታቸው በሕይወታቸው የመጨረሻዎቹ ዓመታት በነበረባቸው ከፍተኛ ደረጃ የደረሰ የስኳር ሕመም የተነሳ ዓይናቸውን ታውረው አልጋ ላይ ዋሉ:: በእርግጥ የዓይናቸው መታወር ምክንያት ጣና ገዳማትን ሲጎበኙ ወደ ዚያው በሔዱ ጊዜ በባሕር ላይ በጀልባ ሲጓዙ የውኃ ነጸብራቅ ዓይናቸውን ስለ ጎዳቸው ነው ይባላል:: ቤተ ክርስቲያኗም ሆነች ቤተ መንግሥቱ የሚቻለውን ሕክምና ሁሉ አግኝተው ጤናቸው እንዲመለስ ከፍተኛ ጥረት ቢደረግም ፈውስን ሊያገኙ አልቻሉም:: በመጨረሻም ለተመሳሳይ የሕክምና አገልግሎት ወደ ኢየሩሳሌም ሔደው ከተረዱ በኋላ ይዘዋቸው የሔዱት አባቶች እንመለስ ቢሉ «እኔ ከእንግዲህ ወደ ኢትዮጵያ አልመለስም፤ እዚሁ እቀበራለሁ» በሚል እንቢታቸውን ገልጸው ለጥቂት ጊዜ እዚያው ቆዩ:: ነገር ግን ይህንን የሰሙት ንጉሠ ነገሥቱ በእንደራሴነት ያገለግሉ የነበሩትን ብፁዕ /በኋላ ብፁዕ ወቅዱስ/ አቡነ ቴዎፍሎስን በአማላጅነት ልከው አስመጧቸው::

ይሁን እንጂ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው ብዙም ሳይቆዩ ለጥቅምት ሁለት ቀን 1963 ዓ.ም ከቀኑ በዘጠኝ ሰዓት በተወለዱ በ79 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ:: ዜና ዕረፍታቸው እንደ ተሰማ በመላ ሀገሪቱ 12 ብሔራዊ የኀዘን ቀናት ታውጆ ሰንብቷል:: ሥርዓተ ቀብራቸውም ግርማዊ ቀዳማዊ ዓፄ ኃይለ ሥላሴ እና ብፁዓን አባቶች እንዲሁም መኳንንቱና መሣፍንቱ በተገኙበት ፈደል ቆጥረው ባደጉበት የደብረ ሊባኖስ ገዳም ጥቅምት 4 ቀን 1963 ዓ.ም ተፈጸመ:: የቅዱስነታቸው በረከት ከሁላችን ጋራ ይሁን:: አሜን::

# 2.2. ሰማዕቱ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ

## ካልአይ ፓትርያርክ

## /1902 - 1971 ዓ.ም/





ሊቀ ሥልጣናት መልአክቱ ወልደ ማርያም ይባሉ የነበሩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ በቀድሞው የጎጃም ጠቅላይ ግዛት፣ በደብረ ማርቆስ አውራጃ፣ በማቻከል ወረዳ፣ ደብረ ገነት ኤልያስ በሚባል ታላቅ ደብር ሚያዝያ 16 ቀን 1902 ዓ.ም ተወለዱ:: የአባታቸው ስም አቶ ጀንበሬ ውቤ፤ የእናታቸው ስም እመት ዘር ትሁን አደላሁ ይባል ነበር::

በወላጆቻቸው ክብካቤ በመንፈሳዊ የልጆች አስተዳደግ ሥርዓት ያደጉት ቅዱስነታቸው ለድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በዚያው በተወለዱበት አጥቢያ በደብረ ኤልያስ ከአያታቸው ከወ/ሮ ሙሉ ነሽ ወዳጄ ነህ ጋር እየኖሩ ከመሪ ጌታ ረዳኸኝና ግራ ጌታ ሣህሉ ዘንድ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ መንፈሳዊ ትምህርታቸውን በሚገባ ተማሩ:: ከዚያም ወደ አዲስ አበባ በመምጣት በወቅቱ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ከነበሩት ግብፃዊው አቡነ ማቴዎስ መዓርገ ዲቁናን ተቀበሉ::

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ዲቁናቸውን ከተቀበሉ በኋላ ወደ ሀገራቸው ተመልሰው ገይማ ጊዮርጊስ በሚባለው ቤተ ክርስቲያንና በደብረ ኤልያስ በዲቁና ሲያገለግሉ ቆዩ:: ከማገልገልም ጋር በዚያው ፈደል ቆጥረው ዜማ በዘለቁበት ታላቁ ደብር /ደብረ ኤልያስ/ ከታላቁ ሊቅ ከመምህር ገብረ ሥላሴ ቅኔ ከነአገባቡ ተምረው በመምህርነት ተመረቁ:: ትምህርታቸውንም በመቀጠል ከተጠቀሱት መምህር ውዳሴ ማርያምን፣ ቅዳሴ ማርያምንና የወንጌል ትርጓሜን በሚገባ አሔዱ::

ቅዱስነታቸው በተማሪነታቸው የነበራቸውን ቀለም የመ ቀበል ፍጥነት መምህሮቻቸውና ባልንጀሮቻቸው ያደንቁ ነበር ይባላል:: የጸዋትወ ዜማ ትምህርታቸውን በአጭር ጊዜ ካጠናቀቁ በኋላ ቀጥሎ የሚመጣው የቅኔ ትምህርትም በመደበኛ መልኩ የሚጠይቀውን ያህል ጊዜ አልወሰደባቸውም ነበር:: ለቀለም ብሩህ የነበረው አእምሮአቸው ቅኔን በአጭር ጊዜ እንዲቀኙ አስቻላቸው:: በቅኔ ለለ ነበራቸው ልዩ ስጦታ የትምህርት ቤት ጓደኞቻቸው በአያሌው ያደንቋቸው ነበር:: በደብረ እልያስ ማኀሌት በሚቆሙበት ሰዓት የሚቀኙ ተማሪዎች ወይም መሪ ጌቶች እሳቸው ካሉ ይፈሩ ነበር ይባላል:: ከፍርሃታቸውም የተነሣ ቅዱስነታቸው ዓይናቸውን ገለጥ አድርገው ያዩአቸው እንደ ሆነ ቅኔው ጭራሹኑ ይጠፋቸው ስለ ነበር «አባክህ መልአክቱ፣ ስንቀኝ አትየን፤ ይጠፋብናል» ይሏቸው እንደ ነበር ስለ እሳቸው የተጻፉ መዛግብት ያስረዳሉ::

ቅዱስነታቸው እንዲህ መሪ ጌቶችንም ጭምር የሚያስፈራ ዕውቀት እንደ ነበራቸው ሁሉ ማንኛውንም ትምህርት ለመማር የፈጠኑ፤ የተማሩትንም በተግባር የሚያሳዩ ብልህ አባት እንደ ነበሩ

## 2.2. ሰማዕቱ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ

## ካልኣይ ፓትርያርክ

## /1902 - 1971 ዓ.ም/



ይነገራል:: አንድ ጊዜ የደብረ ኤልያስ ቤተ ልሔም በማፍሰሱ ሳር ታጭዶ ከመጣ በኋላ ለጊዜው የሚከድን ባለ ሞያ ጠፋ:: በዚህ ወቅት ተማሪ መልእክቱ እኔ እከድነዋለሁ ብለው ቤተ ልሔሙን አሳምረው ከፍክፈው ስለ ከደኑት ቤቱ ለብዙ ዓመታት ሳያፈስ ኖሯል ይባላል::

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ በዚህ ዓይነት በመምህሮ ቻቸውና በጓደኞቻቸው ተፈቅረውና ተከብረው እየተማሩ ለዓመታት ከቆዩ በኋላ የወደ ፊት የትምህርት ሕይወታቸውን በሚመለከት አንድ አሳብ መጣላቸው:: ይኸውም ምንም እንኳን ከወላጆቻቸውና ካሳደጓቸው አያቶቻቸው ጀምሮ እስከ መምህሮቻ ቸውና ባልንጀሮቻቸው ድረስ የሚፈልጉት የቅዱስነታቸውን በዚያው መቆየትና ጉባኤ ዘርግቶ ማስተማር ቢሆንም፣ ቅዱስነታ ቸው ወደ ሌላ ቦታ ሔደው ዕውቀታቸውን ለማስፋፋት ወሰኑ:: በመሆኑም ይህን ከፍተኛ የመማር ፍላጐት የወለደውን ውሳኔያቸ ውን ለማንም ሳያዋዩ በ1920 ዓ.ም በአንድ ቀን ሌሊት ጠፍተው በእግራቸው ወደ ሸዋ ገሠገሡ:: ከዚያም የቀረኝን ትምህርት አገኝበታለሁ ወዳሉት አዲስ ዓለም ማርያም ሔደው በወቅቱ በዚያ ያስተምሩ የነበሩትን ንቡረ ዕድ ሐዲስ ተክሌን /በኋላ አቡነ ዮሐንስ/ እጅ ነሥተው የጉባኤው አባል ሆኑ::

ቅዱስነታቸው አዲስ ዓለም ደርሰው ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ተማሪዎች ይጐርፉላቸው ከነበሩት ንቡረ ዕድ ሐዲስ ተክሌ ጋር ቢተዋወቁ ንቡረ ዕድ «ታላቅ ሰው መጣ» አሉ ይባላል:: ወደ ጉባኤ ገብተው የቅዱስነታቸውን ትምህርት ተቀባይ ነት ካዩም በኋላ ከሌሎች ተማሪዎቻቸው ለይተው ምግብና መኝታ እንዲዘጋጅላቸው አድርገው በማስቀመጥ የልጅ ያህል እያቀረቧቸውና ለሥራም እያዘዟቸው መኖር ጀመሩ:: ቅዱስነ ታቸው በተማሪነታቸው ብስክሌት መንዳት ተምረው ስለ ነበር ንቡረ ዕድ ለአንዳንድ ጉዳዮች ወደ አዲስ አበባ ቢልኳቸው በብስክሌት እየተመላለሱ ጉዳይ ይፈጽሙላቸው ነበር ይባላል:: ተሹመው አዲስ አበባ ከመጡ በኋላም ብስክሌቷ አብራቸው እንደ ነበረችና በመጨረሻ ግን ለአንድ ወዳጃቸው እንደ በጡአት ይነገራል::

ከላይ እንደ ተገለጠው ቅዱስነታቸው ከደብረ ኤልያስ ተነሥተው ወደ አዲስ ዓለም የመጡት ወላጆቻቸውንም ሆነ መምህሮቻቸውን ሳያስፈቅዱና ሳይሰናበቱ በመሆኑ በቅዱስነታቸው ከአካባቢው መሰወር ያላዘነና ያልተጨነቀ አልነበረም:: በተለይ በእጠገባችን ተቀምጦ አይዞአችሁ ይለናል፣ ብናረጅ ይጦረናል፣



ብንሞት ይፈታናል፤ ይጸልይልናል ባሉት የመጀመሪያ ልጃቸው መጥፋት በእጅጉ ያዘኑት አባታቸው አቶ ጀንበሬ ውቤ ይሔዱበ ታል ባሉት ቦታ ሁሉ ማፈላለጋቸውን ተያይዘውት ነበር:: ታዲያ አቶ ጀንበሬ ጉዳዩን ሲያጠያይቁ ልጃቸው ያለበትን ቦታ ዐወቁ:: በዚህም በእጅጉ ተደስተው ወደ አዲስ ዓለም በመሔድ ከተገናኙ በኋላ «ወደ ሀገራችን እንሒድ፣ ይህንን ያህል የተሰደድክበትን ዕውቀትም እዚያው ታገኘዋለህ» ብለው ቅዱስነታቸውን ጠ የቁአቸው:: ቅዱስነታቸው ግን የአባታቸውን ሐሳብ እንደ ማይቀ በሉት በአክብሮት በመግለጽ «አባቴ ሆይ፤ አሁን ፍትሐ ነገሥቱ ንም ሐዲሳቱንም ጨርሼ በመክለስ ላይ እገኛለሁ:: ክለሳውን ከጨረስኩ በኋላ እመጣለሁ» በማለት ሐሳባቸውን ገለጹላቸው:: አቶ ጀንበሬም ምንም እንኳን ከዓመታት ልቅሶ እና ኀዘን በኋላ ያገኟቸውን ልጃቸውን ትተው ለመሔድ ቢቸገሩም ባስረዷቸው ሐሳብ በመስማማት፤ የጀመሩትን ትምህርት ሲጨርሱ ግን ወደ ጎጃም እንዲመጡ ከተማኅፀኖ ጋር አደራ ብለው ወደ ሀገራቸው ተመለሱ::

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ አዲስ ዓለም ላይ በዚህ ዓይነት ትምህርታቸውን ቢያደላድሉ ከቆዩ በኋላ በ1930 ዓ.ም ወደ ደብረ ሊባኖስ በመውረድ መዓርገ ምንኩስናን ተቀበሉ:: ብዙም ሳይቆዩ ከአቡነ አብርሃም መዓርገ ቅስናን ተቀበሉ:: ቅዱስነታቸው ከዚህ በኋላ ከጎጃም ሸዋ ድረስ መጥተው ወደ ሀገራቸው ይሔዱ ዘንድ የለመኗቸው፤ በዚህም ከቅዱስነታቸው አንደበት የተስፋ ቃል ይዘው የተመለሱት አባታቸውም ሆኑ እናታቸው እንዲሁም ወዳጅ ዘመዶቻቸው ተስፋ ይቆርጡ ዘንድ መንኩሰው የተነሡትን ፎቶ ግራፍ አንዳንድ ቅጂ ለወላጆቻቸውና ለዘመዶቻቸው ላኩ ይባላል::

የቅዱስነታቸውን መመንኮስ ከፎቶ ግራፉቸው ያዩት ሁሉ በውሳኔያቸው ተደስተዋል:: ትምህርትም አግኝተዋል:: በተለይ አባታቸው ፎቶ ግራፉ እንደ ደረሳቸው ምንም እንኳን ለወዲያው በእጅጉ ቢደነግጡም «እንግዲህ ትላንት የወለድኩት ልጄ እንደዚህ ዓለሙን ንቆ የእንጦንስን ቆብ በመጫን ራሱን የክርስቶስ ሙሽራ ሲያደርግ እኔ ለምን በዓለም እደክማለሁ!?» በማለት ቤት ንብረታቸውን ትተው መንነዋል:: የአቶ ውቤ አድራሻ ለዓመታት ሳይታወቅ ቆይቶ በመጨረሻ በቤተ በዎቻቸው ፍለጋ እዚያው ጎጃም ውስጥ ሥርወ ኢየሱስ ከተባለ ገዳም ገብተው አባ ወልደ ማርያም በመባል ከቆዩ በኋላ በዚያው ማረፋቸው ተረጋገጠ::

የአባታቸውን ዜና ዕረፍት የበሙትና በወቅቱ የመንበረ

ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ሊቀ ሥልጣናት የነበሩት ቅዱስነታቸው ለአባታቸው ከነበራቸው ጽኑዕ ፍቅር የተነሣ በእጅጉ አዝነው እንደ ነበር በአሳቸው ሕይወት ዙሪያ የተጻፉ መዛግብት ይመሰክራሉ:: በዚህ ከባድ ኀዘናቸው የተነሣም ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ጨምሮ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት ቤታቸው ድረስ በመሔድ አስተዛዝነዋቸዋል:: የአባታቸውን የመጨረሻ ሕይወት ለማስታወስም የአባታቸውን ስም ከጀንበሬ ወደ ወልደ ማርያም ቀይረው ይጠሩበት ነበር ይባላል::

የኢጣልያ ጦር ሀገራችንን በወረረ ጊዜ ቅዱስነታቸው በጣም ይወዷቸው ከነበሩትና በወረራው ጊዜ ከተሾሙት ኤጲስ ቆጳሳት አንዱና ኋላም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳሳት ከነበሩት መምህራቸው ሐዲስ ተክሌ ዘንድ ስላልተለዩ በፈጣን የመማር ችሎታቸው የጣልያንኛና የእንግሊዝኛ ቋንቋን ተምረው እንደ ነበር ይነገራል::

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ኢትዮጵያ በኢጣልያ በተወረረችባቸው ዓመታት የቋንቋውን ትምህርት እየተማሩ የመምህራቸውና ከአቡነ አብርሃም ቀጥሎ ሊቀ ጳጳስ ተብለው ተሹመው የነበሩት ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ አርዌ ብርት ያዥ /ጸሐፊያቸውም ነበሩ ይባላል/ እና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ዲያቆናት ሆነው እንደ ነበር ይነገራል::

ኢትዮጵያ ነጻነቷን ከተጎናጸፈች በኋላ ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ የንቡረ ዕድ ሥልጣናቸውን እንደያዙ በእዲስ ዓለም ማርያም ገዳም እንዲቀመጡ ሲደረግ ቅዱስነታቸውም ወደዚያው በመሔድ ትምህርታቸውን ሲያጠናክሩ ቆዩ::

አዲስ ዓለም ላይ ጥቂት እንደ ቆዩም በቤተ መንግሥቱ ሙሉ ፈቃድ 1935 ዓ.ም በነበራቸው ትምህርት ወደ አዲስ አበባ ቢመጡ ብዙ ሊሠሩ እንደ ሚችሉ በሰ ታመነበት ያኔ መካነ ሥላሴ ይባል ለነበረው ደብር መምህር ሆነው ተሾሙ:: ቆይቶም በ1938 ዓ.ም የመካነ ሥላሴ ደብር «መንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል» ተብሎ በሊቀ ሥልጣናት ማዓርግ እንዲተዳደር ሊደረግ ቅዱስነታቸውም «ሊቀ ሥልጣናት አባ መልአከቱ» ተብለው ማስተዳደር ጀመሩ::

ቅዱስነታቸው በተቀበሉት ታላቅ የቤተ ክርስቲያን ሥልጣን በአግባቡ በመጠቀም ሐላፊነታቸውንም በብቃት በመወጣት ለካቴድራሉ መልካም አስተዳደራዊ መዋቅርን ዘርግተዋል::



ከዚህም በተጨማሪ የካቴድራሉን ማኅበረ ካህናትና ምእመናንን በማስተባበርም ልዩ ልዩ የልማት ሥራዎችን አከናውነዋል:: ይህ መልካም አርአያነት ያለው ተግባራቸውም በቤተ መንግሥቱም ሆነ በቤተ ክህነቱ እየታወቀ መጣ:: በዚህም በ1940 ዓ.ም ለመዓርገ ጵጵስና ተመርጠው ከተሾሙት አምስት አባቶች አንዱ ሆኑ::

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ በነበራቸው የቋንቋ ችሎታና የአርቆ አስተዋይነት ሀብት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ላይ ለዘመናት ተጭኖ የኖረው የግብፅ ቤተ ክርስቲያን የግዞት ቀንበር ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተበብሮ እንዲወድቅ በማድረግ ቢታሪክ መዝገብ በወርቃማ ቀለም የተመዘገበ አስተዋጽኦ አበርክተዋል:: ጉዳዩን በሚመለከት በተለያዩ ጊዜያት ወደ ግብፅ በመሔድ ከአባቶች ጋር የተወያዩትን ልዑካን በመምራት ታሪክ የማይረሳውን ሥራ ሠርተዋል::

ሐምሌ 18 ቀን 1940 ዓ.ም በካይሮ ቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሳብ እንብሮተ ዕድ ከተሾሙት አባቶች አንዱ የሆኑት ቅዱስነታቸው የቅድስት ሥላሴ ሊቀ ሥልጣናትነታቸውን ሳይተው «ጳጳስ ዘሐረር» ተብለው እስከ 1951 ዓ.ም አገልግለዋል:: ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ በ1951 ዓ.ም የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ሆነው ከተሾሙ በኋላ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ በ1952 ዓ.ም የሊቀ ጵጵስናውን መንበር ተረከቡ::

በተመሰከረላቸው የአስተዳደር ብቃት ሀገረ ስብከታቸውን ከማስተዳደር ጋር ከ1943 ዓ.ም እስከ 1963 ዓ.ም ድረስ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ እንደ ራሴ በመሆን አገልግለዋል::

ቅዱስነታቸው በእነዚህ የአገልግሎት ዓመታት በፊና ለዛሬዋ ቤተ ክርስቲያን መሠረት የጣሉ ሀበይት ሥራዎችን ሠርተዋል:: በነበራቸው ሠርቶ የማሠራት ጥበብና ችሎታ ወቅቱ የሚጠይቃቸው አስተዳደ ራ ዊ መዋቅሮች በቤተ ክህነቱ እንዲዘረጉ፣ መመሪያዎችና ደንቦችም እንዲወጡ በማድረግ የቤተ ክርስቲያኗ ሁሉን ዐቀፍ አገልግሎት እንዲጠናከር አድርገዋል:: ባህላዊና ዘመናዊ ትምህርት ቤቶችን አቀናጅተው መርተዋል:: በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ስብከተ ወንጌል እንዲስፋፋ አድርገዋል:: በተለይ ቤተ ክርስቲያኗ ከቤላው ዓለም ጋር ያላት

ግንኙነት የተጠናከረ ይሆን ዘንድ የቤተ ክርስቲያኒቱን የውጭ ግንኙነት መርሕ በመቅረጽና በመተግበር ታሪካዊ አስተዋጽኦ አድርገዋል::

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ በዘመነ እንደ ራሴነታቸው ከሠሯቸው ዐበይት ተግባራት የሚጠቀሰው የቤተ ክርስቲያኗ አስተዳደራዊ መዋቅር እንዲሻሻል በማድረግ በቤተ ክርስቲያኗ አስተዳደር ምእመናን ቀጥተኛ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚያስችሏቸውን የሰበካ ጉባኤ ማደራጃና የሰንበት ት/ቤቶች ማስተባበሪያ የተሰኙት መምሪያዎች እንዲዘረጉ፤ በተጨማሪም የቅርስ ምዝገባና ጥበቃ መምሪያና የቤተ ክርስቲያኗ ልማትና ክርስቲያናዊ ተራድዖ ኮሚሽን እንዲዋቀሩ አድርገዋል:: በትምህርቱ መስክም በ1935 ዓ.ም የተቋቋመው የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ት/ቤት /አሁን ኮሌጅ/ የበላይ አስተዳዳሪና የቦርድ ሰብሳቢ በመሆን ት/ቤቱ እንዲጠናከር ከፍተኛ አስተዋጽዖ አድርገዋል:: በሀገረ ስብከታቸውም በሐረርና በቀልቢ ደብረ ኃይል ቅዱስ ገብርኤል ገዳም ሁለት ዘመናውያን ት/ቤቶችን አቋቁመው በርካታ የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች በመንፈሳዊና በዘመናዊ ትምህርት እንዲገነቡና ሀገራቸውን እንዲሁም ቤተ ክርስቲያናቸውን እንዲረከቡ አድርገዋል:: ምንም እንኳን ብዙዎቹ ተመልሰው የሠሯቸውን ኀመመልከት ባይታደሉም ተማሪዎች በሀገር ቤት በተከፈቱላቸው መንፈሳውያን ት/ቤቶች ከመማራቸው በተጨማሪ ወደ ውጭ እንዲሔዱና ከፍተኛ የነገረ መለኮት ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ አድርገዋል::

የቅዱስነታቸው የዘወትር ዓላማ ስብከተ ወንጌልና ትምህርተ ወንጌል ይስፋፋና ይጠናከር ዘንድ ነበረና በ1958 ዓ.ም የስብከተ ወንጌል ማስፋፊያ ፕሮግራም አውጥተው በአዲስ አበባና በተለያዩ አህጉረ ስብከት በመዘዋወር የስብከተ ወንጌል ድርጅት የሚባለውን አቋቁመዋል:: አስፋፍተዋልም:: ወደ ኋላ በጠቅላይ ቤተ ክህነቱ መምሪያ እንዲሁም በየአጥቢያው የተቋቋመው የሰበካ ጉባኤ ምንጩ ይኸው የቅዱስነታቸው እንቅስቃሴ ነው:: ከዚህም በተጨማሪ የነገው የቤተ ክርስቲያን ተረካቢ ትውልድ ዝግጁ ሆኖ ይገኝ ዘንድ የወጣቶችን ማዕከላዊ ጽ/ቤት በመንበረ ፓትርያርኩ መሥርተው በየደብሩ ቅርንጫፍ የወጣቶች መንፈሳውያት ማኅበራት እንዲቋቋሙና የሰንበት ትምህርት እንዲስፋፋ አድርገዋል::

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ግንቦት 1 ቀን 1963 ዓ.ም በመጀመሪያው የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ተተክተው በመንበረ ፓትርያርክነቱ ከተቀመጡም በኋላም ቀድሞም ቢሆን ሙሉ ተሳታፊ የነበሩበትን የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር የበለጠ በማጠንከር ልዩ ልዩ ጠቃሚ ተግባራትን አከናውነዋል:: ቤተ ክርስቲያኗ በሰሜን



አሜሪካና በካሪቢያን ደሴቶች እምነቷን እንድታስፋፋና እንድ ታስተምር፣ አብያተ ክርስቲያናትም እንዲቋቋሙና እንዲታነፁ፣ የራሷን ካህናት እየላከች ሐዋርያዊ ሥራ እንድ ትሠራ አድርገዋል::

በሀገር ውስጥም በ1964 ዓ.ም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን እንዲቋቋም አድርገዋል:: ይህ የልማት ኮሚሽን ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ካህናትን በተለያዩ ልማት ነክ ሥራዎች በማሠልጠንና በያሉበት የሀገሪቱ ክፍሎች በሚካሔዱ የልማት ሥራዎች እንዲ ባተፉ በማድረግ፣ የበጎ አድራጐት ሥራዎችንና የምግብ ለሥራ ፕሮ ግራሞችን በማካሔድ፣ በሀገሪቱም ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት ሥራዎች በመሳተፍ በቤተ ክርስቲያኒቱ ስም ጠቃሚ አገልግሎቶችን እያበረከተ ይገኛል::

ከዚህም በተጨማሪ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር የተቃና ይሆን ዘንድ የተለያዩ አስተዳደራዊ ደንቦችንና መመሪያዎችን በፊር ማቸው አጽድቀው ሥራ ላይ እንዲውሉ አድርገዋል:: ከእነዚህም ውስጥ «ቃለ ዐዋዲ» የተሰኘውና የተለያዩ ደንቦችን ያካተተው ዐቢይ የቤተ ክርስቲያኗ የአስተዳደር ደንብ ተጠቃሽ ነው:: ከዚህም ጋር ጥቅምት 15 ቀን 1965 ዓ.ም ዛሬም ቢሆን ቤተ ክርስቲያኗ እየተገለገለችበት ያለውን የሰበካ ጉባኤ ደንብ፣ ግንቦት 1 ቀን 1965 ዓ.ም የቤተ ክርስቲያኒቱን ንዋያተ ቅድሳትና መጻሕፍት አመዘጋገብና አጠባበቅ ደንብ፣ ታኅሣሥ 16 ቀን 1967 ዓ.ም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅን ሥልጣንና ተግባር የሚወስን ደንብ አውጥተው ሥራ ላይ አውለዋል::

ቅዱስነታቸው በነበራቸው የሰከነና የአርቆ አስተዋይነት ችሎታ ቤተ ክርስቲያናችን በመንግሥት ችሮታ ታገኘው የነበረው ገቢ አንድ ቀን እንደ ሚቀር በመረዳት ቀደም ቢል ከታነፁት ጋር አከራይታ የምትጠቀምባቸውን ሕንጻዎች በአዲስ አበባ ከተማ የተለያዩ ቦታዎች አሠርተዋል:: ከሚከራዩ ሕንፃዎችም በተጨማሪ አዲስ አበባ ላይ የሚገኘውን የጎፋ መካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ካቴድራልን አሳንፀዋል:: በተጨማሪም ፈደል ቆጥረው ያደጉበትንና በምስራቅ ጎጃም የሚገኘውን የደብረ ገነት ኤልያስ ቤተ ክርስቲያንን በዘመናዊ መልክ አሳድሰዋል::

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ በዚህ በተጠቀሱትና ባልተጠቀሱት በርካታ አገልግሎቶች ተጸምደው ሳለ በ1966 ዓ.ም የንጉሡ ዘውዳዊ መንግሥት በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ መንግሥት ተተካ:: የወጠኗቸውን የቤተ ክርስቲያን ልማቶች ሳይፈጽሙ፣ ያሰቧቸውን የሥራ ዕቅዶች ወደ ተግባር ሳይለውጡ የካቲት 9 ቀን 1968 ዓ.ም ከመንበረ ፓትርያርክነታቸው ወርደው ለእስር ተዳረጉ::

ቅዱስነታቸው በእስር በታላቁ ቤተ መንግሥት በዙፋን አዳራሽ ምድር ቤት ውስጥ ታላላቅ የዘውድ መንግሥት ባለሥልጣናት ታስረውበት ወደ ነበረው አንድ ቀዝቃዛ ክፍል ውስጥ ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ የነበረውን የቅዱስነታቸውን ሁኔታ ከቅዱስነታቸው ጋር የቅርብ ትውውቅና የሥራ ግንኙነት የነበራቸው አቶ አበራ ጀምበሬ የዓይን እማኝነታቸውን «የእስር ቤቱ አበሳ» በሚል ርእስ ባሳተሙት መጽሐፍ እንደ ሚከተለው ተርከውታል።

*«. . . በታላቁ ቤተ መንግሥት ታስረው የነበሩ የቀድሞ መንግሥት ባለ ሥልጣኖች ንጹሕ አየር ለማግኘት፣ በፀሐይ አካላቸውን ለማሞቅ፣ የተሳሰሩ እግሮቻቸውን ለማፍታታት በዙፋን አዳራሽ አጠገብ በሚገኝ በሽቦ በታጠረ ጠባብ ክልል ውስጥ ይንከላወሳሉ። ቀኑ መጋቢት ሦስት ቀን 1968 ዓ.ም ከእኩለ ቀን በኋላ ነበር። በዚህ ወቅት ታላቁ መንፈሳዊ አባት ሁለት እጆቻቸው በአንድ ላይ በሠንሠለት ታስረው እየተገፈተሩ ያለ መጫሚያ በባዶ እግራቸው ሲመጡ የተመለከቱት እነዚያ እስረኞች ባሉበት ክው ብለው ቀሩ። በዚህ ወቅት ነበር አንዱ እስረኛ ልቡ ተነክቶ «አዲዮስ የኢትዮጵያውያን ሰብአዊነትና መንፈሳዊነት» ያለው።*

*«. . . የኢትዮጵያ ሕዝብ ግብረ ገብነትና መንፈሳዊነት በእነዚህ ጋጠ ወጦች አይለካም» አለ ሌላው በድርጊቱ መብገኑን ሁኔታው እየነገረበት። «ካህኑን እንደ ፖለቲከኛ፣ መንፈሳዊ አባቱን እንደ ወንጀለኛ የሚመለከት ወታደራዊ ቡድን በዚህች ቅድስት አገር መነሳቱ ያሳዝናል። መንፈሳዊ አባት በግፍ ሲንገላታ ከማየት መሞት ይመረጣል» አለ ሌላው በመበሳጨት።*

*«የአደፈ ሸሮአማ ቀሚስ እንደ ለበሱ ከቀኝም፣ ከግራም፣ ከኋላም ሳንጃ የተሰካበት ጠብ መንጃ ተደግኖባቸው ወደ ዚያች የፖለቲካ እስረኞች መቀየጃ ቅጥር ግቢ ሲገቡ መንፈሳዊው አባት «የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው» በማለት ግፍ ለሚፈጽሙባቸው የሚጸልዩ እንጂ የተበሳጩና የተሸበሩ አይመስሉም ነበር።*

*«እስረኛው ከድንጋጤው ገና ሳይላቀቅ፣ ምን እንደ ሚልና እንደ ሚያደርግ አሰላሰሉ ሳይጨርስ፣ ከቆመበት ሳይላወስ ነበር ከአንድ ትንሽ ክፍል ውስጥ አስገብተው የቆለፉባቸውና እግራቸውን በእግረ ሙቅ፣*



*እጃቸውን በሠንሠለት ጠፍረው ከአልጋ ጋር ያሠሯቸው። 'ይህን እዚ መኛ ቄስ ተጠንቀቃችሁ ጠብቁ' በማለት ለወታደሮቹ ጥብቅ ትእዛዝ ሰጥቶ የዘቡ አዛዥ ከአጥሩ ወጥቶ ሔደ።*

*«መንፈሳዊው አባት የታሰሩባት ክፍል በማግሥቱ የአሳሪዎች ምልልስ ታየባት። ሹማምንት በመፈራረቅ ጉበኙት። ፈንጠር፣ ፈንጠር፣ ቀበጥበጥ ብለው እንዳልገቡ ተሰፋ ቆርጠው ሲወጡ ተስተዋሉ። ይህ ሁሉ ምልልስ፣ ይህ ሁሉ ጋጋታ የተከሰተው ከአንድ ክፍል ውስጥ እግር እጃቸው ከአልጋ እግር ጋር የታሰረው መንፈሳዊ አባት ምግብ አልበላም ብለው በመወሰናቸው ነበር። ሻለቃ ዳንኤል አስፋውና ሌሎች የእስር ቤቱ ኃላፊዎቹ የሚመጣላቸውን ምግብ እንዲመገቡ ለማድረግ ቢሞክሩም ቆራጡ አባት አልተበገሩም። ከዚህ በኋላ ነበር ምግብ አልበላም በማለት ማስቸገራቸውን በመግለጽ ሻለቃ ዳንኤል ለደርግ የፀጥታ ጥበቃ ኮሚቴ ሊቀ መንበር ባቀረበው ማስታወሻ ግርጌ ላይ «ምግብ እንዲ ገባላቸው አድርጉ እንጂ ቢበሉ ባይበሉ የራሳቸው ጉዳይ ነው» ሲል ሻለቃ ተካ ቱሉ ምልክት ያደረገው።*

*«እኒያ አባት በዚያች መሰኮት በሌላት ጠባብ ክፍል ምግብ ብቻ ሳይሆን ንጹሕ አየርም ሳያገኙ ሰባት ቀን ጠማቸውን ውለው አደሩ። ከዚያ በኋላ ነበር ሌሎች እስረኞች አግባብተው ምግብ እንዲበሉ እንዲያደርጉ ለአንድ ቁጥር ኃላፊ ትእዛዝ በመስጠት አሳሪዎቻቸው ከሰው እንዲቀላቀሉ ያደረጉት። እግር እጃቸው ከብረት ተላቅቆ ከመንፈስ ልጆቻቸው ጋር ተቀላቀሉ። ለጸሎት እንዲያመቻቸው በዙፋን አዳራሽ መግቢያ ዋና በር ደረጃ ሥር የሚገኘው ጉሮኖ ለእርሳቸው መኝታ ተለቀቀላቸው። በአንድ ቁጥር ክፍል ውስጥ የሚገኙት እስረኞች በተለይም ብርጋዴር ጄኔራል ሳሙኤል በየን ዐቅማቸው በፈቀደ መጠን የሚጉድላቸውን እሟልተውና እንጥፈው ተቀበሏቸው። ምግብ ሲያቀርቡላቸው ግን «እግዚአብሔር ይስጣችሁ፤ አልበላም» የሚል ሆነ መልሳቸው። የደረቀ ጉሮሮአቸውን በውኃ እያጉመጠመጡ ብቻ ምግብ ሳይ በሉ፣ ውኃ ሳይጠጡ መጾሙን ቀጠሉ። ጠንካራነታቸውን አስመሰከሩ፣ የመንፈስ ብቻ ሳይሆን አካላዊ ምግባቸውም ጾም ጸሎት ሆነ። የዕለት ተዕለት ሁኔታቸውም ለሌሎች እስረኞች መንፈሳዊ ጽናትን ሰጠ።»*

*ይሁንና ፋሲካ በዋለ በማግሥቱ ከእስረኞች መካከል በዕድሜ የገፉት አንደኑ ደጅ አዝማች ሐረጉት ግብይ ያሉት አጥብቀውና አስጨንቀው ስለ ለመኗቸው አህል ሊበሉ መቻላቸውን አብረዋቸው ታስረው ከነበሩት ለማረጋገጥ ተችሏል:: /የእስር ቤቱ አበሳ በታላቁ ቤተ መንግሥት፣ ከ1966 እስከ 1974 ዓ.ም፣ አበራ ጀንበሬ ገጽ 9-12/::*

ቅዱስነታቸው በዚህ ዓይነት ለ28 ወራት ከአራት ቀን በመሪር ኀዘንና ጸሎት ከቆዩ በኋላ ሐምሌ 7 ቀን 1971 ዓ.ም በሰሜን አዲስ አበባ ወረዳ 12 ቀበሌ 22 ወደ ሚገኘው የልዑል ራስ ዓሥራተ ካሳ ቤት ተወስደው በሚያሰቅቅ ሁኔታ በገመድ ታንቀው ተገደሉ:: አስከሬናቸውም የእርሳቸውን ዓይነት የሞት ጽዋ ከተቀበሉ ሰዎች ጋር በዚያው ቅጽር ግቢ ተቀበረ::

የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ዐጽም ከ13 ዓመታት በኋላ አሟሟታቸውንና የት እንደ ተቀበሩ በዐይኑ ባየ በወቅቱ የደርግ የደኅንነት ክፍል ወታደር ጥቆማ ወጥቶ ሐምሌ 4 ቀን 1984 ዓ.ም በጎፋ መካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ካቴድራል በክብር ዐረፈ:: በዚህ ወቅት ከላይ በአጭሩ የተገለጠውን የመከራ ጽዋዕ ተቀብለው ያለፉት ቅዱስ አባት በቤተ ክርስቲያኗ ቅዱስ ሲኖዶስ «ሰማዕት» ተብለው እንዲጠሩ የተላለፈው ውሳኔ በንባብ ተሰምቷል:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ቅዱስነታቸው «ሰማዕቱ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ» ተብለው ይጠራሉ:: ለቅዱስነታቸው መታሰቢያ ይሆን ዘንድ ዐጽማቸው ባረፈበት ካቴድራል ሐውልት ቆሞላቸዋል:: የቅዱስነታቸው ረድኤትና በረከት ከሁላችን ጋር ይሁን:: አሜን::



## 2.3. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሣልሳይ ፓትርያርክ /1910 - 1980 ዓ.ም/



# 2.3. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት
## ሣልሳይ ፓትርያርክ
## /1910 - 1980 ዓ.ም/



አባ መልአኩ ይባሉ የነበሩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት መስከረም 10 ቀን 1910 ዓ.ም የንጉሥ ወልደ ጊዮርጊስ ታማኝ ወታደር ከነበሩት አባታቸው ከወ/ር ወልደ ሚካኤል አዳሙና ከእናታቸው ከወ/ሮ ዘውዲቱ ካሣ በቀድሞው ጎንደር ጠቅላይ ግዛት ማኅደረ ማርያም ተብላ በምትታወቀው ገዳም አካባቢ ጋዠን በምትባል ቦታ ተወለዱ:: ወላጅ አባታቸው ወ/ር ወልደ ሚካኤል እናታቸውን ወ/ሮ ዘውዲቱን ያገኟቸው ለውትድርና አገልግሎት ከጎንደር ወደ ጎጃም መጥተው ዘርዘር በተባለው አካባቢ በቆዩበት ጊዜ ነበር:: የቅዱስነታቸው ወላጆች በዚህ ዓይነት ከተዋወቁ በኋላ አባታቸው የጎጃሙን ተልእኮ አጠናቀው ወደ ጎንደር ሲመለሱ ወ/ሮ ዘውዲቱንም ይዘው ተጓዙ:: ጎንደር ደርሰው ጥቂት ከቆዩ በኋላ የሁለቱ ፍሬ የኾኑት ቅዱስነታቸው ተገኙ::

ወ/ር ወልደ ሚካኤል ምንም እንኳን ባልታሰበ ሁኔታ ካገኟት የትዳር ጓደኛቸው ዓይናቸውን በዓይናቸው ለማየት ቢታደሉም ባደረባቸው ሕመም የተነሣ ልጃቸው ገና ዕርጥብ አራስ ሳሉ ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ:: ባለቤታቸውን ተከትለው ወንዝ በመሻገር ወደ ማያውቁት ሀገር የሔዱት ወ/ሮ ዘውዲቱ አራስ ልጃቸው በመጠኑ ጠንከር እስኪሉ በዚያው ቆይተው ልጃቸውን በመያዝ የባለቤታቸውን ዘመዶች ተሰናብተው ወደ ሀገራቸው ተመለሱ:: ገና በአራስነታቸው ወላጅ አባታቸውን ያጡት ቅዱስነታቸውም ዘርዘር ሚካኤል በተባለ የእናታቸው ሀገር ማደግ ጀመሩ:: ለድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ እዚያው ከእናታቸው ጋር ሆነው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን ጀመሩ:: ነገር ግን በዚህ ምድር በፈተና ጸንተው ስማያዊውን ቤታቸውን በሚገባ ሠርተው ሊሔዱ የተፈቀደላቸው ቅዱስነታቸው ገና ፊደል እንኳን ሳይለዩ ወላጅ እናታቸውም በሞት ተለዩአቸው::

የወላጅ አባታቸውን መልክ በልጅነት እጃቸው ለመዳሰስ፣ በከንፈራቸው ለመሳም፣ በዓይናቸው ዐይተው በአእምሮአቸው ለመሣል ያልታደሉት ቅዱስነታቸው ይባስ ብሎ እናታቸውን ሲያጡ ተደናገጡ:: ምንም እንኳን የእናታቸው ዘመዶች አይዞህ ቢሏቸውም ከእነርሱ እንደ አንዱ ሆነው በግብርና እንዲሠማሩ ለማድረግ ስለ ነበረ ቅዱስነታቸው እናታቸው በሞት ከተለዩአቸው በኋላ በአካባቢው ሊቆዩ አልፈለጉም:: በመሆኑም ከዘርዘር ዘመዶቻቸውን ተሰናብተው ጎንደር ወደ ሚገኙት የአባታቸው ዘመዶች ተጓዙ:: ጉዟቸውን አጠናቀው ማኅደረ ማርያም አካባቢ በምትገኘው ጋዠን ከተባለች ቦታ ደርሰው የመማር ፍላጎታቸውን ለዘመዶቻቸው ገለጹ:: የድሃ አደጉን ሕፃን አሳብ የተረዱት ዘመዶችም በእዚያው አካባቢ ታዋቂ መምህር ለነበሩት መሪ ጌታ ወርቅነህ ሰጧቸው:: በዚያም ፊደል ከቆጠሩ በኋላ ወደ ደብረ ታቦር ተሻግረው እናቲቱ ማርያም በተባለችው



ደብር ያስተምሩ ወደ ነበሩት አለቃ ቀለመ ወርቅ ዘንድ ሔደው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀቁ:: ከዚህም በኋላ ወደ አዲስ አበባ መጥተው በወቅቱ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ከነበሩት ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ መዓርገ ዲቁናን ተቀበሉ::

ከዚያም ወደ ማኅደረ ማርያም ተመልሰው በዲቁና ሲያገለግሉ ቆዩ:: ወላጆቻችውን በሞት በመነጠቃቸው ብቸኝነት የተሰማቸው ቅዱስነታቸው ቀጣይ ሕይወታቸውን በቤተ ክርስቲያን ትምህርት አኀልምሰው በትኅርምትና እግዚአብሔርን በማገልገል ሊኖሩ ወሰኑ:: በውሳኔያቸው መሠረትም ቅኔ ሊማሩ ከጓደኛቸው ጋር ከማኅደረ ማርያም ተነሥተው ወደ ጎጃም ተመለሱ:: በዚያም በእናታቸው ሀገር አጠገብ ወደ ሚገኘውና የረዝ ሚካኤል ወደ ተባለው ቦታ ሔደው መምህር ልሳነ ወርቅ ከተባሉ መምህር ዘንድ ቅኔንና ዜማን ለስምንት ዓመታት ያህል ተማሩ:: በሚማሩ በትም ጊዜ የእናታቸው ዘመዶች በልብስና በምግብ መጠነኛ ድጋፍ ያደርጉላቸው ነበር ይባላል::

የዜማውንና የቅኔውን ትምህርት በሚገባ ካጠናቀቁ በኋላ በተማርኩት ደግሞ ጥቂት ላገልግል በማለት ወደ ደብረ ታቦር ሔዱ:: ይሁን እንጂ ወዲያውኑ የኢጣልያ ፋሺስት ጦር ኢትዮጵያን በግፍ በመውረሩ እንዳሰቡት በሰላም ሊያገለግሉ አልቻሉም:: በመሆኑም የአገልግሎት አሳባቸውን በመተው ራቅ ወዳለ ቦታ ሔደው በብሕትውና እየኖሩ ለመማር ወሰኑ:: ይህንን ውሳኔያቸውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚሔዱበትን ሀገር ለመወሰን ሲያወጡ ሲያወርዱ እና የጓደኞቻቸውን ምክር ሲጠይቁ አንድ ጓደኛቸው በደቡብ ኢትዮጵያ ወላይታ አካባቢ አጎቱ በመንግሥት ሥራ ተሠማርቶ እንደ ሚኖር፣ አካባቢው በ13ኛው መ.ክ.ዘ. ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የተጋደሉበት፣ እንደ ደብረ መንክራት አቡነ ተክለ ሃይማኖት ዓይነት ታላላቅ ገዳማት እንዳሉበት፣ ቦታው በጥምቀት የቅድስት ሥላሴን ልጅነት ያላገኙ ሰዎች የሚበዙበት በመሆኑ ለብሕትውናና ለአገልግሎት የሚመች መሆኑን መክሮ አብረው ቢሔዱ ለጊዜው አጎቱ ቤት እንደ ሚያርፉ ይነግራቸዋል:: ቅዱስነታቸውም የጓደኛቸውን አሳብ ተቀብለው በ1926 ዓ.ም ሁለቱም ወደ ወላይታ ጉዞአቸውን ጀመሩ::

አድካሚ ከሆነው ከብዙ ቀናት የእግር ጉዞ በኋላ ወላይታ ደርሰው ከጓደኛቸው አጎት ቤት ዐረፉ:: አካባቢውን እስከ ሚላመዱ በእንግድነት ከቆዩ በኋላም ዝናው ከጎንደር ስቦ ወዳ መጣቸው ደብረ መንክራት አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም ገቡ:: እግዚአብሔር እንደነ ጻድቁ አቡነ ዜና ማርቆስና ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በአካባቢው ሥራ እንዲሠሩ መርጧቸዋልና ወደ ገዳሙ ሲገቡ በቦታው ረዘም ላለ ጊዜ የቆዩትን አለቃ ደስታ የተባሉትን ባሕታዊ አገኙ:: ከእርባቸ

ውም ጋር በአንድ በአት ተወስነው መኖር ጀመሩ::

ቅዱስነታቸው በደብረ መንከራት ገብተው ጥቂት ከቆዩ
በኋላ የገዳሙ አበ ምኔት ከነበሩት መምህር ወልደ ኢየሱስ የቅዱሳት
መጻሕፍትን ትርጓሜ በተለይም የማር ይስሐቅንና የመጻሕፍተ
ሊቃውንትን ትርጓሜ በጥልቀት ተማሩ:: ቅዱስነታቸው ከመማር
ጋር በነበራቸው የቁም ጽሕፈት ችሎታ በመምህራቸው ታዝዘው
ቅዱሳት መጻሕፍትን እየጻፉ ለገዳሙ ማኅበር እንዲዳረስ አድርገ
ዋል:: በዚህ ዓይነት የቅዱሳት መጻሕፍትን ምሥጢር ሲመረምሩና
ሥርዓተ ገዳምን ሲያጠኑ ከቆዩ በኋላ በዚያው መዓርገ ምንኩስናን
ተቀበሉ:: ከዚያም ወደ አዲስ አበባ መጥተው ከግብፃዊው ብፁዕ
አቡነ ቄርሎስ መዓርገ ቅስናን ተቀብለው ወደ በኣታቸው ተመለሱ::

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ወደ ገዳማቸው
ከተመለሱ በኋላ በጾም በጸሎት፣ በስጊድና በትኅርምት በገድልና
በልዩ ልዩ ትሩፋት ተወስነው እስከ 1940 ዓ.ም ድረስ በአታቸውን
አጽንተው ቆዩ:: ይህም የተባሕትዎ ጊዜ ከፈጣሪያቸው ከእግዚአ
ብሔር ልዩ ጸጋና በረከት የተቀበሉበትና ለወደ ፊት ዓላማቸው ሁሉ
መመሪያ ያገኙበት ወቅት ነበር::

በዚህ ዓይነት ለዓመታት በፍጹም ትኅርምት እና ተጋድሎ
እንደ አባቶቻቸው እግዚአብሔርን በጸሎት ከለመኑ በኋላ በ1940
ዓ.ም በአታቸውን በዚያው ገዳም አድርገው በአውራጃው ልዩ ልዩ
ቦታዎች በመዘዋወር ማስተማር ጀመሩ:: ቅዱስነታቸው በሚያስ
ደንቅ ሁናቴ በአውራጃው ውስጥ በሚገኙት ሰባት ወረዳዎች እየተዘ
ዋወሩ ሲያስተምሩ ከሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስ
ዘንድ በአካባቢው እንዲንቀሳቀሱ የፈቃድ ደብዳቤ ከማግኘታቸው
በስተቀር የተቆረጠላቸው ደመወዝ የተሰፈረላቸው እህል አልነበረም::
በቅዱስነታቸው ትምህርት ከ300,000 /ሦስት መቶ ሺህ/ በላይ የሆኑ
ኢ አማንያን አምነው እንደ ተጠመቁና የክርስቶስ ተከታዮች እንደ
ሆኑ ይነገራል:: በጣዕመ ስብከታቸው ይህንን ያህል ምእመን ካፈሩም
በኋላ ምእመናኑ እየተሰበሰቡ የሚጸልዩባቸውና ምሥጢራተ ቤተ ክር
ስቲያንን የሚቀበሉባቸው በሁሉም ወረዳዎች 65 አብያተ ክርስ
ቲያናትን አሠርተዋል:: እንዲሁም ልጆቻቸው መንፈሳዊውንና ሥጋ
ዊውን ትምህርት የሚማሩባቸውን 24 ትምህርት ቤቶችን አቋቁ
መዋል::

ቅዱስነታቸው ከዚህም በተጨማሪ በወላይታ ሶዶ ከተማ
በደብረ መንክራት ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም አካባቢ 11
ክፍል የድኩማን ቤት በማሠራት ራሳቸውን ለመርዳት የማይችሉ
ድኩማን ምግብ፣ ልብስና መጠለያ እንዲያገኙ በማድረግ ሐዋርያዊ
ግዳጃቸውን ተወጥተዋል:: እንዲሁም በዚሁ ከተማ ውስጥ ከ400



ያላነሰ ሕዝብ በአንድ ጊዜ መያዝ የሚችል «የወጣቶች የመጽሐፍ
ቅዱስ ማኅበር አዳራሽ» የተሰኘ መሰብሰቢያ አዳራሽ አሠርተው
በአገልግሎት ላይ ይገኛል:: ከዚህም ሌላ አንድ ክሊኒክ በዚሁ ከተማ
ውስጥ አቋቁመው ሕዝቡ እንዲጠቀምበት አድርገዋል:: እንደዚሁም
ከከተማው ወጣ ብሎ በሚገኘው ቆንቶ በተባለው ቀበሌ በ1954 ዓ.ም
ባሠሩት አዳራሽ የቃጫና የልዩ ልዩ ጥበበ እድ ሥራዎችን
በማቋቋም የአካባቢው ችግረኞች እየሠሩ ራሳቸውን እንዲረዱ
አድርገዋል::

ስብከተ ወንጌልንም በተመለከተ አካባቢው በመናፍቃን
የተያዘ ስለ ነበር ባቋቋሙት ማኅበር አማካይነት ሰባክያንን በመቅጠ
ር አባላቱም በፈቃዳቸው በአገልግሎቱ እንዲሠማሩ በማድረግ ሰፋ
ያለ አገልግሎት አበርክተዋል:: ቅዱስነታቸው ባቀናጁት የስብከተ
ወንጌል አገልግሎት ተሳታፊ ከነበሩት የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች
የያኔው ዲያቆን መርሐ ጽድቅ /የዛሬው ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ ሊቀ
ጳጳስ/ አንዱ ነበሩ::

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከላይ በመጠኑ የተዘረ
ዘሩትን መንፈሳዊና ማኅበራዊ ሥራዎች የሠሩት በቤተ መንግሥቱ
ዕውቅና የነበረውንና በአካባቢው የሚገኙ ሰባት አውራጃዎች ተወካዮ
ችን በአባልነት የያዘ «የመገበሪያ ቦርድ» የተሰኘ አካል በማቋቋም
የአካባቢው ሕዝቦች ገንዘብ እንዲያዋጡ በማድረግ፣ ከዚህም ጋር
የአካባቢውን የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ማፋጠንን ቀዳሚ ዓላማው
ያደረገውን «ብርሃነ ሕይወት» የተሰኘ ግብረ ሠናይ ድርጅት አቋቁ
መው ነበር::

በዚህ ዓይነት ሰፊ አገልግሎት ላይ ተጸምደው ቤተ ክርስ
ቲያን የሰጠቻቸውን ሐላፊነት በመወጣት ላይ ሳሉ ንጉሣዊው
መንግሥት በወታደራዊው የደርግ መንግሥት ተተካ:: በመሆኑም
እንደ ቀድሞው ሁሉ ከሕዝቡ ገንዘብ ማሰባሰብ አልቻሉም:: በዚህ
የተነሣም የልማት አገልግሎታቸው እንዳይቋረጥ ወደ አዲስ አበባ
እየመጡ ከቤተ ክርስቲያኗና ከምእመናን መለመን ጀመሩ:: በዚህ
ዓይነት በተወሰነ ደረጃ እየተንቀሳቀሱ እያለ ደርግ ሁለተኛውን
የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስን አሳግቶ
አሰረ:: ከቤተ ክርስቲያኗ ቀኖና ውጪም ሌላ ፓትርያርክ እንዲ
መረጥ አዘዘ:: ራሱ ባቋቋመው አስመራጭ ኮሚቴ አማካይነት ከየክ
ፍሉ ለፓትርያርክነት እንዲመረጡ የሚፈለጉ አባቶች እንዲጠቆሙ
አደረገ:: በመጨረሻም የማጣሪያ ምርጫ አድርጎ ከተጠቆሙት
አባቶች ውስጥ አምስቱ ብቻ እንዲቀሩ ካደረገ በኋላ ከ565 ወረዳ
ዎች ሁለት ሁለት ተወካዮች እንዲላኩና በአምስቱ አባቶች ላይ
የፓትርያርክነት ምርጫ ድምፅ እንዲሰጡ ጥሪ አደረገ:: በእጩነት

የቀረቡት አምስት አባቶች አቡነ አንድርያስ /በወቅቱ የቤጌምድርና ስሜን ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ/፣ ብፁዕ አቡነ ሰላማ /በወቅቱ የጋሞ ጎፋ ሊቀ ጳጳስ/፣ አባ ተወልደ ብርሃን ወ/ሥላሴ ዘቢዘን /በወቅቱ የደብረ ቢዘን ገዳም አበምኔት/ ፣ አባ ዮሐንስ ከሐሊ ዘኢየሩሳሌም፣ አባ መላኩ ወ/ሚካኤል ዘደብረ መንክራት ተክለ ሃይማኖት ነበሩ:: ባላሰቡት ሁኔታ ለዚህ ታላቅ ኃላፊነት መታጩታቸውን የሰሙት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት መንበሩ ለእኔ አይገባም ብለው ተቃውመው እንደ ነበር ይነገራል:: በዚህ የተነሣ ቅዱስነታቸው ቤተ ክህነት ውስጥ በምትገኝ አንዲት ክፍል ውስጥ ተቀምጠው በዘበኛ እንዲጠበቁ ተደርጎ እንደ ነበር ይነገራል::

ምንም እንኳን ከተጠበቁት 1130 ወኪሎች 909 ብቻ ቢገኙም በተገኙት ወኪሎች አማካይነት ምርጫው እንዲከናወን ተደርጎ ከደብረ መንክራት አቡነ ተክለ ሃይማኖት የመጡት አባ መላኩ ከጠቅላላው 909 ወኪሎች 317 ድምፅ በማግኘት የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሦስተኛው ፓትርያርክ ሆነው ተመረጡ:: የቅዱስነታቸው ሹመት እውን ይሆን ዘንድ ሐምሌ 11 ቀን 1968 ዓ.ም መዓርገ ጵጵስና ተቀበሉ:: ስማቸውም ብፁዕ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ተብለው ተሠየሙ:: በኋላም ነሐሴ 23 ቀን 1968 ዓ.ም በቅዱስ ሲኖዶስ «አባ ተክለ ሃይማኖት ሣልሳዊ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ» ተብለው ተሾሙ::

የቅዱስነታቸውን የአመራረጥ ሒደት የሰሙት የግብፅ ቤተ ክርስቲያን፣ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት እንዲሁም የአፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ጉባኤ አንድን ፓትርያርክ በኃይል ከመንበሩ አንሥቶ ሌላ ፓትርያርክ መሾም አይገባም ሲሉ በመቃወም ለሹመቱ ዕውቅና አንሰጥም በማለት መግለጫ አውጥተው ነበር::

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በዚህ ዓይነት የቤተ ክርስቲያኗን ታላቅ ሐላፊነት ከተረከቡበት ጊዜ ጀምሮ ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እስከ መንበረ ፓትርያርክ ድረስ ያለውን የሰውና የገንዘብ ኃይል በማሰባሰብ ጊዜው የሚጠይቀውን መንፈሳዊና ማኅበራዊ ግዴታ ይፈጽሙ ጀመር:: ቅዱስነታቸው የሥራቸው መጀመሪያ ያደረጉት ቀደም ሲል በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ መሠረቱ ተጥሎ የነበረውን የቃለ ዐዋዲ ደንብ በማሻሻልና አንዳንድ ሁኔታዎችን ከወቅቱ ጋር እንዲሔዱ በማድረግ ሰበካ ጉባኤያት በማዕከል በሚቋቋመው መምሪያ እንዲመሩ ሆነው በየአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናቱ እንዲቋቋሙና ምእመናን በቤተ ክርስቲያኗ አስተዳደር ቀጥተኛ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ ነበር::

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት



ዘኢትዮጵያ ስለ ስብከተ ወንጌል መስፋፋትና መጠናከር ከጥንት ጀምሮ በነበራቸው ጽኑዕ ዓላማ ሰበካ ጉባኤን በማጠናከር አዳዲስ ሰባክያንን በመምረጥና በማሠልጠን ስብከተ ወንጌል እንዲስፋፋና እንዲጠናከር አድርገዋል::

ቅዱስነታቸው የነገዪቱ ቤተ ክርስቲያን ተረካቢዎች የዛሬ ሕፃናት መሆናቸውን ስለ ሚያውቁ ለሰንበት ት/ቤት ተማሪዎች ከፍ ያለ አመለካከትና ትኩረት ነበራቸው:: ቀደም አድርገው በየአንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ት/ቤት እንዲቋቋም በሰጡት መመሪያ መሠረት በየአህጉረ ስብከቱ በርካታ የሰንበት ት/ቤቶች ተቋቁመው ሰፋ ያለ አገልግሎት እንዲ ያበረክቱ አድርገዋል:: በአዲስ አበባ አብያተ ክርስቲያናት በተቋቋሙት የሰንበት ት/ቤቶች እየተዘዋወሩ ለሚያስተምሩ መምህራን መጓጓዣ ይሆን ዘንድ ከወር ደመወዛቸው በየወሩ 730 ብር ይሰጡ ነበር::

አብነት ትምህርት ቤቶች ለቤተ ክርስቲያኗ ቀጣይ አገ ልግሎት ወሳኝ እንደ ሆኑ የተገነዘቡት ቅዱስነታቸው ከዘመኑ መለወጥ ጋር የሕዝቡ ኑሮም ስለ ሚለወጥ ለዘመናት በአካባቢያቸው ከሚኖሩ ምእመናን ቁራሽ ለምነው ሲማሩ የኖሩት ተማሪዎችና መምህራን እንዳይቸገሩ በማሰብ በየዓመቱ በመንበረ ፓትርያርክ በሚደረገው አጠቃላይ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ላይ እንዲወሰን አድርገው ለበርካታ የአብነት መምህራን የወር ደመወዝ እንዲመደብላቸው፣ ተማሪዎችም ተመሳሳይ ድጎማ እንዲደረግላቸው አድርገዋል:: ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርትን በሚመለከትም ለተወሰኑ ዓመታት ሥራውን አቁሞ የነበረውን የሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት በ1974 ዓ.ም እንደ ገና ተከፍቶ ሥራውን እንዲጀምር አድርገዋል::

ቅዱስነታቸው ቤተ ክርስቲያኗ በካህናቷ አማካይነት መንፈሳ ዊውንም ሆነ ማኅበራዊውን አገልግሎት ለኅብረተሰቡ በተሟላ ሁኔታ መስጠት እንድትችል በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ በድስት የሚሆኑ የካህናት ማሠልጠኛዎች እንዲቋቋሙና ሥራቸውን እንዲጀምሩ አድርገዋል::

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ በዘመነ ፓትርያርክነታቸው ለቤተ ክርስቲያኒቱ ዕድገትና ሐዋርያዊ ተልእኮ ለስብከተ ወንጌልም መስፋፋት የጳጳሳት ቁጥር መጨመር አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ በተለያዩ ጊዜያት 28 ኤጲስ ቆጳሳትን ሾመዋል:: በሀገሪቱ ውስጥ ያሉትን አብያተ ክርስቲያናት ቁጥር ለማበራከት በተደረገው ከፍተኛ ጥረትና የም እመናንንም መንፈሳዊ ፍላጎት ለማሟላት ሲባል ምእመናን በሚኖ ሩበት አካባቢና በየአቅራቢያቸው በርከት ያሉ አዳዲስ አብያተ ክር

ስቲያናት እንዲቋቋሙላቸው አድርገዋል።

ልማትን በሚመለከትም ቅዱስነታቸው በሚሰጡት መመሪያ በድርቅ የተጎዱ ወገኖች በሚገኙባቸው አካባቢዎች ያለ ምንም የሃይማኖት ልዩነት ኢትዮጵያውያን የሚገለገሉባቸው የእህል ወፍጮ ቤቶችና ጸበ ቤቶች እንዲቋቋሙ አድርገዋል። ከዚህም በተጨማሪ የውኃ ጉድጓዶችን በማስቆፈርና መጋቢ መንገዶችን በማሠራት፤ በልዩ ልዩ ገዳማትና አድባራት የጨርቃ ጨርቅ ሽመና፣ የሹራብ ሥራ፣ የከብትና የንብ ርባታ፣ የአዝርእትና አትክልት ልማት፣ ችግኝ ማፍላትና የደን ዛፍ መትከል፣ የወንበርና ጠረጴዛ፣ የመስቀል ቅርጻ ቅርጽ ወዘተ የሚሠሩባቸውን ጎጆ ኢንዱስትሪዎች ተቋቁመው አገልግሎት እንዲሰጡ አድርገዋል።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ለዚህ ከፍተኛና የመጨረሻ የፓትርያርክነት ሐላፊነት በልዑል እግዚአብሔር ፈቃድ በምእመናን ከመመረጣቸው በፊት «ለድሆችና ለድሃ አደጎች ፍረዱ፤ ለችግረኛውና ለምስኪኑ ጽድቅን አድርጉ፤ ብቸኛውንና ችግረኛውን እርዱ» በሚለው ቃል በመመራት በትምህርተ ወንጌል ምእመናንን በማስተባበር ደኻ አደጎችንና ድኩማንን ሰብስበ መርዳትና ማስተማር በገዳም ይፈጽሙት ከነበረው ምግባር ትሩፋት ዋናው ክፍል ነበር። ቅዱስነታቸው በፓትርያርክነቱ የቅድስና መንበር ላይ ከተቀመጡ ወዲህም ቢሆን ይህን የተቀደሰ ዓላማ ዋና ተግባራቸው አድርገው በመያዝ የሃይማኖትና የብሔር ልዩነት ሳያደርጉ ከየአቅጣጫው እያሰባሰቡ በምግበ ሥጋና በምግበ ነፍስ የሚረዷቸው ድኻ አደጎችና ድኩማን እጅግ ብዙዎች ነበሩ። በተለይም በሀገራችን የድርቅ ችግር ከተከሰተ ወዲህ ቅዱስነታቸው ከየሥፍራው ሰብስበው የሚረዷቸው ወላጅ አልባ ሕፃናት ከቁጥር በላይ ነበሩ። ይህንን የቅዱስነታቸውን ምግባረ ሠናይ ከያሉበት ሆነው የሚሰሙ ወልዶ ማሳደግ ያቃታቸው ችግረኞች ምእመናንም ልጆቻቸውን ወደ መንበረ ፓትርያርኩ በማምጣት ለቅዱስነታቸው ሲያስረክቡ ወይም ለማስረከብ ደጅ ሲጠኑ ማየት የተለመደ ነበር።

ቅዱስነታቸው ደኻ አደጎችን መርዳት ከቤተ ክርስቲያን ዐበይት ዓላማዎች አንዱ በመሆኑ በተሾሙ ማግሥት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሕፃናት አስተዳደግ ጉባኤ ማእከል ተከፍቶ እጓለ ማውታ እንደ ማንኛውም የኅብረተሰብ ልጆች ሥርዓትና መልክ ባለው ሁኔታ ክብካቤ እየተደረገላቸው እንዲያድጉ አድርገዋል። በዚህም ረገድ ባሰጡት መመሪያ በእርሳቸው ዘመነ ፓትርያርክነት በየሀገረ ስብከቱ የተቋቋሙ የቤተ ክርስቲያኗ የእጓለ ማውታ ማሳደጊያዎች 36 ደርሰው ነበር። በእነዚህ ማእከላት አድገውና ተምረው ለደረጃ የበቁት ኢትዮጵያውያን ዛሬ በልዩ ልዩ



ሞያዎች ተሠማርተው ሀገርንና ወገንን በማገልገል ላይ ይገኛሉ።

በውጭ እህጉር ለሚገኙ የቤተ ክርስቲያናችን ምእመናን መንፈሳዊ አገልግሎትን ለማሟላትና እንዲሁም በቤተ ክርስቲያናችን ትምህርትና እምነት እምልኮተ እግዚአብሔርን ለመፈጸም ለሚፈልጉ የውጭ አህጉር አማንያን ቤተ ክርስቲያን በማቋቋምና አገልጋዮችንም በመላክ ለቤተ ክርስቲያናችን ከፍተኛ የሆነ ታሪክ አስመዝግበዋል። ለዚህም ድርጊት በምዕራብ ጀርመን፣ በጅቡቲና በኬንያ የተቋቋሙት አብያተ ክርስቲያናት በግንባር ቀደም ከሚጠቀሱት መካከል ናቸው።

ቅዱስነታቸው ለዘመናት የምእመናን ጥያቄዎች ሆነው ሲያነጋግሩ የነበሩ ጉዳዮችን በማድመጥ ቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ እንዲያሳልፍባቸው በማድረግ በኩል የሚጠቀሱ ሥራዎችን ሠርተዋል። ከእነዚህም ውስጥ ከሰባቱ አጽዋማት አንዱ የሆነው የልደትና የጥምቀት ጾመ ገሐድ ፣ ጾመ ነቢያት የሚገባው በየዓመቱ ኅዳር 15 እንደ ሆነና ዓሣ በጾም ወራት እንደማይበላ ያስወሰኗቸው ውሳኔዎች ይጠቀሳሉ።

እንደ ሚታወቀው እሳቸው በሥልጣን ላይ በነበሩበት ጊዜ በሀገሪቱ የነበረው ርእዮተ ዓለም ከእምልኮተ እግዚአብሔር ጋር የሚሔድ አልነበረም። በዚህ የተነሣም ብሔራዊት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አንዳንድ ፈተናዎች ተጋርጠውባት ነበር። ይሁን እንጂ በቅዱስነታቸው ጥበብና ትዕግሥት በሩስያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የደረሰው በእኛዋ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሳይደርስ ፈተናውን እንድታልፍ ማድረጋቸው በሰፊው የሚነገር እውነታ ነው።

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከሢመተ ፓትርያርክነት በፊትም ሆነ በመዋዕለ ሢመታቸው በትግሀ ጸሎት በገድል በትሩፋት የተፈተነ መንፈሳዊ ሕይወት የነበራቸው፣ ከፍቅረ ንዋይ የነጹ፣ ለተቸገሩት የሚሰጡትን ርዳታና በጎ አድራጎትም ማንም በአፍአ እንዲናገር የማይፈልጉ፣ የዚህንም ምክንያት ሲያስረዱ «እናት ለልጆችዋ የምትሰጠውን ሁሉ ሀገር ይወቅልኝ ትላለችን?» ሲሉ በተደጋጋሚ ይናገሩ የነበሩ፣ ሠርቶ የማሠራትና በየጊዜውም አዳዲስ የሥራ መቀቅሮች እንዲከፈቱ የማበረታታት ልምድ ያላቸው ደግ አባት እንደ ነበሩ በቅርብ የሚያውቋቸው ሁሉ ይናገራሉ።

ቅዱስነታቸው እንደ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ሀገረ ሙላድ እያላቸው ተወልጄ ያደግሁበት ቦታ ይህ ነው ብለው ከመናገር ይልቅ በፍጹም ኢትዮጵያዊነታቸው ብቻ ያምኑ ነበር። የካህነ እግዚአብሔር መልከ ጼዴቅን አሠረ ፍኖት በመከተል እንደ

አብርሃም እበ ብዙኃንነትን እጉልተው በማሳየት ሁሉን እኩል በመመልከት ብቃታቸው ብዙዎችን ሲያስገርሙ የኖሩ አባት ነበሩ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት መቼም ቢሆን አልጋ ላይ ተኝተው የማያውቁ ፍጹም ተጋራሚ አባት እንደነበሩ በቅርብ የሚያውቋቸው ሁሉ ይመሰክሩላቸዋል። በዚህ ረገድ በብዙ ሰዎች አንድ የሚነገር ታሪክ አላቸው። በአንድ ወቅት ቅዱስነታቸው ፓትርያርካዊ ጉብኝት ለማድረግ ሌሎች ብፁዓን አባቶችን አስከትለው ወደ ፖላንድ ይጓዛሉ። በዚያም ያረፉት በካርዲናሉ መኖሪያ ቤት ነበር። ለቅዱስነታቸው ክብር ሲባል የተሰጣቸው ክፍል የካርዲናሉ ክፍል ነበር። ታዲያ ቅዱስነታቸው እሺ ብለው ሲመሽ ወደ ክፍሉ ይግቡ እንጂ አልጋው ላይ አይተኙም ነበር። ጠዋት ግን አልጋውን የተኙበት ለማስመሰል የተነጠፈውን ብርድ ልብስም ሆነ አንሶላውን ያመስቃቅሉት ነበር። አንድ ቀን ምሽት በአጋጣሚ የካርዲናሉ ሠራተኛ ዕቃ ለማውጣት ወደ ክፍላቸው ስትገባ አልጋው እንደ ተነጠፈ፣ ቅዱስነታቸው ከመሬት ላይ ተኝተው ታገኛቸዋለች። እርስዋም በእጅጉ ደንግጣና ተደንቃ ለካርዲናሉ ነገረችው። ካርዲናሉም የብፁዕ ወቅዱስ እቡነ ተክለ ሃይማኖትን ቅድስናና ትኅርምት አድንቆ ጉብኝቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ በራሱ መኪና ራሱ እየነዳ ሲያገለግላቸው ሰንብቷል ይባላል።

ቅዱስነታቸው በአመጋገብም በኩል ቢሆን በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ከበሶ ወይም የተቀቀለ ድንች በስተቀር ሌላ ነገር ቀምሰው አያውቁም ይባላል።

ቅዱስነታቸው በጾም፣ በጸሎት፣ በቀዊምና በስግደት ተወስነው ቤተ ክርስቲያናቸውን ሲያስተዳድሩ ከቆዩ በኋላ በመጨረሻ ስፊ አገልግሎትና ተጋድሎ ሲፈጽሙበት የቆዩበትን የደብረ መንክራት አቡነ ተክለ ሃይማኖትን ገዳም በመጎብኘት ላይ ሳሉ በድንገት ታመሙ። ወደ አዲስ እበባ ባስቸኳይ መጥተው በዳግማዊ ምኒልክና የጦር ኃይሎች ሆስፒታል በሕክምና ሲረዱ ቢቆዩም ሊድኑ አልቻሉም። በመሆኑም ከዐሥራ ሁለት ዓመታት የፓትርያርክነት አገልግሎት በኋላ ግንቦት 28 ቀን 1980 ዓ.ም በተወለዱ በ 70 ዓመት ዕድሜያቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። ቅዱሰነታቸው መላ ዘመናቸውን በጾም፣ በጸሎትና በስጊድ ያሳለፉ ከመሆናቸው ጋር ባደረባቸው ሕመም የተነሣ ነፍሳቸው ከሥጋቸው ስትለይ የሰውነታቸው ክብደት 25 ኪሎ ግራም ደርሶ እንደ ነበር ይነገራል። አስከሬናቸውም በመንበረ ፓትርያርኩ እርፎ ሌሊቱን ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጸሎተ ፍትሐቱን ሲያደርሱ አደሩ። በማግሥቱም ግንቦት 29 ቀንም በመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ገዳም ጸሎተ ቀጥሎ ሥርዓተ ቀብራቸው ግንቦት 30 ቀን 1980 ዓ.ም



ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት፣ የየመምሪያው ኃላፊዎችና ሠራተኞች፣ የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት አድባራትና ገዳማት አለቃዎች፣ የሰንበት ት/ቤቶች አባላትና ምእመናን እንዲሁም የመንግሥት ባለ ሥልጣናት በተገኙበት በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በክብር ተፈጽሟል። የቅዱስነታቸው አገልግሎት ሲዘከር ይኖር ዘንድ አስከሬናቸው በክብር ባረፈበት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል የመታሰቢያ ሐውልት ቆሞላቸው ዛሬም ይገኛል። የቅዱስነታቸው ረድኤት እና በረከት ከሁላችን ጋር ይኑር። እሜን።

# 3.1. ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ቀዳማዊ «ጳጳስ ዘምሥራቀ ኢትዮጵያ ተላዌ አሠሩ ለአቡነ ኢየሱስ ሞዓ» /1875 - 1928 ዓ.ም/





ጴጥሮለ የሚለውን በመ ጽጽለና ከማግኘታቸው በፊት መምህር ኃይለ ማርያም ይባሉ ነበር። ብፁዕ አቡነ ጴጥሮበ ቀዳማዊ በ1875 ዓ.ም. በሰሜን ሸዋ ህገረ በብከት ሰላሌ አውራጃ ፍቼ ከተማ ተወለዱ። የልጃቸውን የዕውቀት ብልጥግና ለማየት የጓጉት ወላጆቻቸው ዕድሜያቸው ገና ለትምህርት ሳይደርስ ወደ ደብረ ሊባኖስ ገዳም በመውሰድ ሰጋ አእምሮአቸውን በዕውቀት ያንፁላቸው ዘንድ ባሕታዊ ተድላ ለተባሉ መምህር አደራ ሰጧቸው።

ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስም የወላጆቻቸው ሕልም እውን ይሆን ዘንድ በንጹሕ አእምሮአቸው እንደ ጥንታዊው የቤተ ክርስቲያኗ ሥርዓተ ትምህርት ከንባብ እስከ ቅኔ ያሉትን ትምህርቶች እዚያው በተወለዱበት አካባቢ በሚያስገርም ሁኔታ በአጭር ጊዜ አጠናቀቁ። በኋላም የቅኔ ትምህርታቸውን ለማስፋፋት በምዕራብ ጎጃም ህገረ ሰብከት ወደ ሚገኘው የቅኔ ትምህርት ቤት ዋሸራ ተሻገሩ። በዚያም በውስጣቸው በሰነቁት የመማር ፍላጐት እየታገዙ ደብረ ሊባኖስ ላይ መሠረቱን የጣሉት የቅኔ ትምህርት በመቀጠል ለመምህርነት የሚያበቃውን ትምህርት ፈጽመው በመምህርነት ተመረቁ።

ብፁዕ አቡነ ጴጥሮለ ፊደል ቆጥረው ያደጉበትን ገዳም ለቀው ዓባይን እንዲሻገሩ ያደረጋቸውን የቅኔ ትምህርት በአጥጋቢ ሁኔታ ቢያጠናቅቁም ወደ ሸዋ አልተመለሱም። ትምህርት ገና በሕፃንነታቸው የወላጆቻቸውን ፍቅር ሳያጣጥሙ የመነኑለት ነውና እንደ ቅኔው ሁሉ የዜማውንም ትምህርት በሚገባ ለመማር ከቅኔው ፀውድማ ጎጃም ወደ ዜማው አዝመራ ጎንደር ተሻገሩ። በዚያም እንደ ቅኔው ሁሉ እስከ ማስመስከር ባይደርሱም የዜማውን ትምህርት በአጥጋቢ ሁኔታ ተማሩ።

ብፁዕነታቸው አሁንም «ያወጣኸኝ አግሬ መልሰኝ ወደ አገሬ» አላሉም። ከፍተኛውን የትምህርት ደረጃ አላዳረሱምና። ገና በሕፃንነታቸው ከወላጆቻቸው ለይቶ ወደ ታላቁ ገዳም ደብረ ሊባኖስ፣ ከዚያም ወንዝ እሸግሮ ወደ ጎጃም፣ ቀጥሎም ወደ ጎንደር የወሰዳቸው የትምህርት ፍቅር በመጨረሻ ወደ ወሎ አደረሳቸው። በወቅቱ ወሎ ቦሩ ሜዳ ከተባለው ቦታ ላይ ወንበር ዘርግተው የመጻሕፍትን ምሥጢር በየዓይነቱ ሲመግቡ ወደ ነበሩት ስመ ጥርው መ/ር አካለ ወልድ ዘንድ በመሔድ ዋና ዋናዎቹን የመጻሕፍት ትርጓሜ ትምህርቶች ማለትም ብሉያትን፣ ሐዲሳትንና ሊቃውንትን በብቃት አሔዱ።

ከዚህ በኋላ በ1900 ዓ.ም. እንደ እርሳቸው ሁሉ ዕውቀትንና ጥበብን ፍለጋ የገቡትን ደቀ መዛሙርት ለማስተማር እዚያው ወሎ አማራ ሳይንት በተባለው ቦታ ወደ ሚገኘው ምስካበ ቅዱሳን ገዳም

# 3.1. ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ቀዳማይ

## «ጳጳስ ዘምሥራቀ ኢትዮጵያ ተላዌ አሠሩ

## ለአቡነ ኢየሱስ ሞዓ»

## /1875 - 1928 ዓ.ም/



በመሔድ ወንበር ዘረጉ። በዚያው ቦታ ለዘጠኝ ዓመታት ያህል ቅኔንና መጻሕፍትን አሰተማሩ።

ገና ከሕፃንነታቸው ጀምሮ በተገለጠው ዓይነት በመንፈሳዊ ትምህርት እየተኮተኮቱ ያደጉት ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ራሳቸውን በእግዚአብሔር ቃል በሚገባ ከገነቡ በኋላ በ1909 ዓ.ም. ወደ ደብረ ሊባኖሰ ገዳም በመሔድ ሥርዓተ ምንኩስናን ፈጸሙ። ብዙም ሳይቆዩ መዓርገ ቅስናን ተቀብለው ከወንበሩ አገልግሎት ጋር የቤተ መቅደሱን ተልዕኮም ደርበው ያዙ።

ሥርዓተ ምንኩሰናንና ቅስናን በተቀበሉ በዓመታቸው በ1910 ዓ.ም. መምህር ኃይለ ማርያም ተብለው በያኜው ወላሞ ወረዳ በሚገኘው ደብረ መንክራት ምሁር ኢየሱስ ገዳም በመምህርነት ተሾሙ። በዚያም የተሰጣቸውን ሐላፊነት ለሰድስት ዓመታት ከተወጡ በኋላ በ1916 ዓ.ም. እንደ ገና በዝዋይ ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ገዳም በመምህርነት ተሾሙ። በዝዋይም የመምህር ነትተግባራቸውን ለሦስት ዓመታት ያህል በአጥጋቢ ሁኔታ ካከናወኑ በኋላ በ1919 ዓ.ም. ወደ አዲስ አበባ በመምጣት የመንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስ መምህርና በቤተ መንግሥት የግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ እበ ንስሐ ሆኑ።

የግብፅ ቤተ ክርሰቲያን ምንም እንኳን ለጊዜውም ቢሆን የሊቀ ጵጵስናውን መንበር አለቅም ብትልም፤ ከአንድ ሺ ሰድስት መቶ ዓመታት በኋላ የኢትዮጵያ እርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዕውቀት መንፈሳዊ ከእርስዋ ተወልደው በዕቅፏ ውስጥ ባደጉ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት እንድትመራ ፈቃዷን ስትገልጽ በትምህርታቸውና በስነ ምግባራቸው የተመሰከረላቸው አምስት ኢትዮጵያውያን እባቶች ተመርጠው ነበር። ከተመረጡትም አባቶች አንዱ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ነበሩ።

በዚህም መሠረት ብፁዕነታቸው ከሌሎች አባቶች ጋር ግንቦት 18 ቀን 1921 ዓ.ም. በእስክንድርያው መንበረ ማርቆስ ቤተ ክርሰቲያን መዓርገ ጵጵስናን ተቀበሉ። ወደ አገራቸው ከተመለሱ ከዓመት በኋላም «አቡነ ጴጥሮሰ ጳጳስ ዘምሥራቀ ኢትዮጵያ ተላዌ አሠሩ ለአቡነ ኢየሱሰ ሞዓ» ተብለው በያኜው መንዝና ወሎ ሀገረ ሰብከት ተሾሙ። */የሹመት ደብዳቤያቸውን በአባሪ አንድ ይመለከቷል።/*

ብፁዕ እቡነ ጴጥሮሰ ቤተ ክርስቲያን በእደራነት የሰጠቻቸውን ሐላፊነት ለመወጣት ሕዝበ ክርስቲያኑን በጸሎታቸው እየደገፉ፣ በትምህርታቸው እያበረቱ በማሰተዳደር ላይ እንዳሉ በ1928 ዓ.ም. አረመኔው የኢጣሊያ ፋሺስት በግፍ ሀገራችንን



ለመውረር ከተት ሠራዊት ምታ ነጋሪት በማለት ባሕርን አቋርጦ መጣ። ቅድስት ቤተ ክርሰቲያን በሀገር በመጣ ወራሪቀጥተኛ ተጠቂ ናትና ሊቃውንቷ፣ ገዳማትና አድባራቷ እንዲሁም ንዋያተ ቅድሳቷ በወራሪው የኢጣልያ ኃይል ይጨፈጨፉና ይቃጠሉ ገቡ። ይህ ግፍ በዕውቀት ኮትኩታ ባሳደገቻቸው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ላይ ቢፈጸም ያዩት ብፁዕነታቸው ወራሪውን ኃይል ከኢትዮጵያውያኑ አርበኞች ጋር በመሆን በጸሎት ሊዋጉት ወሰኑ።

በመጀመሪያ የወቅቱ የሀገሪቱ መሪ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል ከአረመኔው ፋሺስት ጦር ጋር በመፋለም ላይ የነበረውን አርበኛ ለማበረታታት ወደ ማይ ጨው በሔዱ ጊዜ ብፁዕነታቸው ተከትለው ሔዱ። ይሁን እንጂ ንጉሡም ሆኑ ብፁዕነታቸው ከሠራዊቱ ጋር ተቀላቅለው ብዙም ሳይቆዩ የጠላት ጦር በመርዝ የታገዘ ጥቃት በሰፋት በመክፈቱ የኢትዮጵያ ሠራዊት ወደ ኋላ እንዲያፈገፍግ ሆነ። በዚህም የተነሣ ንጉሡ ወደ አዲስ አበባ ቢመለሱ ብፁዕነታቸውም አብረው ተመለሱ። እዚሁ እሞታለሁ ብለው እንቢ ያሉት ንጉሡ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለሱ ከሌሎች አባቶች ጋር የብፁዕነታቸው ሚና ቀላል እንዳልነበር ይነገራል።

ይሁን እንጂ በጠላት የግፍ ጥቃት ከፉኛ ያዘኑት ብፁዕነታቸው በአዲሰ አበባ ለመቀመጥ አልፈቀዱም። በታላቁ የደብረ ሊባኖስ ገዳም ተሰባስበው የቤተ ክርሰቲያን አምላክ እግዚአብሔር በኢትዮጵያውያን ላይ የመጣውን ችግር እንዲያሥታግስ በጸሎት እየለመኑ ወደ ነበሩት አባቶችና አርበኞች በመሔድ ለሀገርና ለነጻነት መሞት ቅዱስ ተግባር መሆኑን በመስበክ ሁሉም እንዲጋደሉ ማሳሰብ እና ማትጋት ጀመሩ። ምንም እንኳን ድልን ባይቀዳጅም በእርሳቸው ሰብከት የተነሣሡት አርበኞችም ወደ አዲስ አበባ በመምጣት ጠላትን ወግተዋል። በዚህ ጊዜ ብፁዕነታቸውም አብረው ነበሩ።

ብፁዕነታቸው የነበሩበት የአርበኞች ጦር ወደ አዲስ አበባ ቢመጣም ድልን ላለመቀዳጀቱ ምክንያቱ የመረጃ ልውውጥ ክፍተት እንደ ነበረ ይነገራል። ይኸውም «የሰላሌ አርበኞች» ተብሎ የሚታወቀው፣ በነደጃዝማች አበራ ካሣ ይመራ የነበረውና በደብረ ሊባኖስ ጫካዎች ውስጥ መሽጎ የነበረው አርበኛ ጦር በሸንኮራ በኩል ከነበረውና በደጃዝማች ፍቅረ ማርያም ይመራ ከነበረው አርበኛ ጦር፣ በምዕራብ በኩል ከነበረውና በደጃዝማች ባልቻ አባ ነፍሶ ይመራ ከነበረው አርበኛ ጦር ጋር በአንድ ጊዜ ተንቀሳቅሶ አዲስ አበባ ላይ ወንበሩን አደላድሎ የተቀመጠውን የግራዚያኒን ጦር ሊወጋ ይነጋገራል። ይሁን እንጂ በሰምምነቱ መሠረት ሦስቱም የጦር ኃይል ምታ ነጋሪት ከተት ሠራዊት ብሎ ወደ አዲስ አበባ

ቢንቀሳቀስም በሦስቱም አቅጣጫ በአንድ ጊዜ ባለ መድረሱ በጠላት ላይ ያደረሰው ጉዳት ቀላል የሚባል ባይሆንም፤ በተናጠል እየተመታ ወደ መጣበት ተመለሰ። በመጀመሪያ በኮተቤ በኩል የደረሰው የደጃማች ፍቅረ ማርያም ጦር ነበር። ይህ ጦር የካ ሚካኤል ላይ ሲደርስ ተመትቶ ተመለሰ። የጠላት ጦር የደጃዝማች ፍቅረ ማርያምን ጦር ወደ መጣበት መልሶ ወደ አዲስ አበባ ሲመለስ የደጃዝማች ባልቻ ጦር በባቡር ጣቢያ በኩል መጣሁ አለ። እሱንም መትቶ መለሰ። በመጨረሻ ደግሞ የደጃዝማች አበራ ጦር በእንጦጦ በኩል አድርጎ መጣ። እሱም በጠላት ጦር ተመትቶ ተመለሰ። በዚህ ዓይነት ሦስቱም ኃይሎች በአንድ ጊዜ ባለ ማጥቃታቸው ወደ የመጡበት ሲመለሱ ከሰላሌ አርበኞች ጋር የነበሩት ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ጠላት ከኢትዮጵያውያኑ ነጥቆ አገሬ ከተማዬ ብሎ በመቀመጥ በመላ ሀገሪቱ የሚያካሒደውን ጭፍጨፋ የሚመራባትንና ትእዛዝ የሚያስተላልፍባትን የአዲስ አበባ ከተማ ትተው ለመሔድ አልፈቀዱም። በመሆኑም «ብችል ጠላት በኢትዮጵያውያን ላይ እያደረሰ ያለውን ግፍ በቅርብ ርቀት ሆኖ የሚመለከተውን ሕዝብ በማትጋት በጠላት ላይ እንዲነሣ አደርገዋለሁ፤ ካልሆነ ደግሞ እዚሁ እሞታለሁ» ብለው ከአርበኞች ተነጥለው በአዲስ አበባ ቀሩ።

ይሁን እንጂ ጠላት በመላ ከተማዋ ባሠማራቸው በርካታ ባንዳዎች መካከል ብፁዕነታቸው እንዳሰቡት ሲንቀሳቀሱ አልቻሉም። በመጨረሻ እዚሁ ከተማ ተሰውሬ መኖር አልፈልግም፤ ወደ ገጠርም ፈቴን አልመልስም በማለት ሐምሌ 22 ቀን 1928 ዓ.ም. በወቅቱ የኢጣልያ እንደራሴ ለነበሩት ለራስ ኃይሉ እጃቸውን ሰጡ። ራስ ኃይሉም ወዲያውኑ ለግራዚያኒ አሳልፈው ሰጧቸው።

ብፁዕነታቸው በተጠቀሰው ቀን እጃቸውን ከሰጡበት ጊዜ ጀምሮ በጠላት የጥይት አሩምታ በሰማዕትነት እስካለፉበት ጊዜ ድረስ የነበረውን ሒደት ኮርየሬ ዴላሴራ የተባለው ጋዜጣ ወኪልና የምሥራቅ አፍሪካ ዜና መዋዕል አዘጋጅ የነበረው ፖጃሊ የተባለ ጋዜጠኛ እ.ኤ.አ ሰኔ 15 ቀን 1936 ዓ.ም. አዲስ አበባ በነበረ ጊዜ በብፁዕነታቸው ላይ የተሰጠውን ፍርድና የተፈጸመውን ግድያ ባየውና በተመለከተው መንገድ እንደ ሚከተለው ጽፎ ነበር።

«ሐምሌ 22 ቀን 1928 አቡነ ጴጥሮስ ተይዘው ወደ ግራዝያኒ ቀረቡ። በዚህ ጊዜ አቡነ ቄርሎስ የተባሉት «ግብፃዊ ጳጳስ ቀርበው ለእስክንድርያው መንበረ ፓትርያርክ ምክር ቤት ሳታሰማ በአቡነ ጴጥሮስ ላይ አንዳች ነገር ማድረግ አይገባህም» ሲሉ ለግራዝያኒ ነገሩት። ምክንያቱም ይላሉ አቡነ ቄርሎስ፤ «አቡነ ጴጥሮስ ታላቅ ሰው ናቸው። በመሠረቱ ሲያዙ ባልተገባ ነበር። ከተያዙም ደግሞ ልትገድላቸው ትችላለህ። ነገር ግን በእርሳቸው ላይ



የምታደርገውን ነገር ሁሉ ለእስክንድርያው መንበረ ፓትርያርክ ምክር ቤት ሳታሰማ ምንም ማድረግ አይገባህም» አሉት።

አቡነ ቄርሎስ ይህን ማለታቸው በዲፕሎማቲክ ደረጃ ለዓለም ለማሰማትና የአቡነ ጴጥሮስን ሕይወት ለማትረፍ አስበው እንደ ነበር ግልጥ ነው። ነገር ግን ግራዝያኒ ይህ የአቡነ ጴጥሮስ የሞት ፍርድ እንኳንስ አስከ ግብፅ ከአዲስ አበባ ውጭ እንኳ ከመሰማቱ በፊት በግማሽ ቀን እንዲፈጸም ትእዛዝ አስተላለፈ። በእርግጥ ምንም እንኳን ከመገደል ባያመልጡም ብፁዕነታቸው እንደ ተያዙ ንቡረ ዕድ ተክለ ሃይማኖት /ሐዲስ ተክሌ/ና ሌሎች ሊቃውንት ወደ አቡነ ጴጥሮስ ዘንድ በመሔድ ማልደዋቸው ነበር ይባላል።

«ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ቁመታቸው ረዘም፣ ፊታቸውም ዘለግ ያለ፣ መልካቸው ጠየም ያለ፣ ዐዋቂነታቸውና ትሕትናቸው ከገጻቸው የሚነበብ ሲሆን በዚህ ጊዜ ለብሰውት የነበረው ልብሰ ጵጵስና ጥቁር ካባ ያውም በጭቃ የተበከለ ነበር። በዚህ ሁኔታ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ወደ ችሎት ቀረቡ። ለፍርድም የተሠየሙት ዳኞች ሦስት ሲሆኑ እነዚህም ጣሊያኖችና የጦር ሹማምንት ናቸው። የመካከለኛው ዳኛ ኮሎኔል ነበር። የቀረበባቸውም ወንጀል ሕዝብ ቀስቅሰዋል፣ ራስዎም ዐምፀዋል፣ ሌሎችንም እንዲያምፁ አድርገዋል የሚል ነበር። ዳኛውም «ካህናቱም ሆኑ የቤተ ክህነት ባለሥልጣኖች ሊቀ ጳጳሱ አቡነ ቄርሎስም የኢጣሊያንን መንግሥት ገዢነት አምነው አሜን ብለው ሲቀበሉ እርስዎ ለምን ዐመፁ? ለምን ብቻዎን አፈንጋጭ ሆኑ?» ሲል ጠየቃቸው።

«አቡነ ጴጥሮስም የሚከተለውን መለሱ። «አቡነ ቄርሎስ ግብፃዊ ናቸው፤ ስለ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን የሚገዳቸው ነገር የለም። እኔ ግን ኢትዮጵያዊ ነኝ። ሐላፊነትም ያለብኝ የቤተ ክርስቲያን አባት ነኝ። ስለዚህ ስለ ሀገሬና ስለ ቤተ ክርስቲያኔ አቀረቆራለሁ። ከዚህ በቀር ለእናንተ ችሎት የማቀርበው ነገር የለኝም። ለፈጣሪዬ ብቻ የምናገረውን እናገራለሁ። እኔን ለመግደል እንደ ወሰናችሁ ዐውቃለሁ። ስለዚህ በእኔ ላይ የፈለጋችሁትን አድርጉ። ግን ተከታዮቼን አትንኩ» አሉ።

«ይህንንም ብለው በጥይት ተደብድበው ሲገደሉ እንዲያይ ተጋብዞ ለተሰበሰበው ሕዝብ የሚከተለውን ሕያው መልእክት አስተላለፉ፦ «አረማዊ የሆነው የፋሺስት መንግሥት ቤተ ክርስቲያንን ለማቃጠል፣ ሕዝበ ክርስቲያንን ለመግደል፣ ሃይማኖትን ለማጥፋት፣ ታሪካችንን ለማበላሸት የመጣ ነው፤ እንጂ በጎ ለመሥራት እውነተኛ ፍርድ ለመስጠት ስላልመጣ ለዚህ ለግፈኛ አትገዙ። ስለ ውድ ሀገራችሁ፣ ስለ ቀናች ሃይማኖታችሁ ተከላከሉ። ነጻነታችሁ ከሚረክስ ሙታችሁ ስማችሁ ሲቀደስ ታላቅ ዋጋ ያለው

ክብር ታገኛላችሁ:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዚህ ለጠላት እንዳይገዛ አውግዣለሁ፤ የኢትዮጵያ መሬት ጠላትን ብትቀበል የተረገመች ትሁን:: በፈጣሪዬ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የተገዘተች ትሁን::»

ጋዜጠኛው ይቀጥላል:: «እኒህ ጳጳስ ሐቀኛ ነበሩ:: ነገር ግን ለኢጣሊያ ለጋስዮን ታዝዞ የመጣው አስተርጓሚ ዳኞች የሚሉትን ብቻ ከማስተርጐም በቀር ጳጳሱ የሚናገሩትን ሐቀኛ ንግግር አላስተረጐመም:: እኔ እንኳን የሰማሁት በአዲስ አበባ ለሠላሳ ዓመት የኖረው የእቴጌ ሆቴል ሐላፊ የነበረው የግሪክ ዜጋ ማንድራኮስ አጠገቤ ተቀምጦ ስለ ነበር የተናገሩትን ሁሉ ስለ ገለጠልኝ ነው:: እኔ እንደ ሰማሁት ፍርዱን ለመስማት በብዛት የተሰበሰቡት ጣሊያኖችና ታዝዞ የወጣው የአዲስ አበባ ሕዝብ ሐቀኛ የሆነውን ንግግራቸውን ቢሰሙ ኖሮ ልባቸው ይነካ ነበር» ይላል::

«ሆኖም አስተርጓሚው በጳጳሱ ላይ ተጽዕኖ ስላሳደረባቸው እውነተኛ ንግግራቸው ሳይገለጥ ቀረ:: ቀጥሎም ብፁዕነታቸው በፍርድ ችሎት ላይ እንዳሉ ሕዝቡ ሁሉ ስለ ርሳቸው አያዘነ ሳለ መስቀላቸውን አውጥተው እየጸለዩ ሕዝቡን ባረኩ:: ወዲያው የሞታቸው ፍርድ ሲሰማ ሕዝቡ በኢጣልያ የእጅ ሰላምታ ዓይነት እጁን እንዲያነሣ ታዘዘ:: በዚያን ጊዜ አቡነ ጴጥሮስ የሞታቸው ሰዓት መድረሱን ሀውቀው ሰዓታቸውን ከኪሳቸው አውጥተው ተመለከቱ:: በዚህ ጊዜ ሁሉ ምንም ፍርሃት አይታይባቸውም ነበር:: የሞታቸውን ፍርድ ያነብ የነበረው ኢጣሊያዊ ዳኛ ግን ይንቀጠቀጥ ነበር:: ታላቅ ፍርሃትም በፊቱ ላይ ይታይ ነበር::

«ይሙት በቃ የተፈረደባቸው ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ በችሎት ፊት ለብዙ ሰዓታት ቆመው ስለዋሉና ደክሞአቸው ስለ ነበር ለመቀመጥ ፈልገው ዳኛውን በትሕትናና በፈገግታ ጠየቁት:: እንዲቀመጡም ፈቀደላቸው:: በመጨረሻም የሞታቸው ፍርድ ከተነበበ በኋላ የፈረዱባቸውን ዳኞች ጸልየው በመስቀላቸው ባረኩዋቸው:: ብፁዕነታቸው እስከ መቃብር አፋፍ ድረስ የፍርሃትና የድንጋጤ ምልክት ያይደለ ክልብ የሆነ ፍጹም ቆራጥነት ይታይባቸው ነበር::

«የሀገራቸው በጠላት መወረር፣ የሕዝባቸው መገደልና መታሰር፣ የቤተ ክርስቲያናቸው መደፈር እስከ ሞት ያደረሳቸው እኒህ እውነተኛ ጳጳስ ለመገደል ሲወሰዱ ጥይት አልፎ ሌላ ሰው እንዳይጐዳ ግንብ ይፈለግ ጀመር:: ሩቅ ባለ መሔድ ከመካነ ፍትሑ 10 ሜትር ርቆ ግንብ ያለው መግደያ ቦታ ተገኘና ወደ ዚያ ተወሰዱ:: ከገዳዮቹም አንዱ «ፊትዎን ለመሸፈን ይፈልጋሉን?» ሲል ጠየቃቸው:: «ይህ የአንተ ሥራ ነው» ሲሉ ብፁዕነታቸው መለሱ:: ከመግደያውም ቦታ እንደ ደረሱ ወንበር ቀረበላቸውና ፊታቸውን ወደ ግንቡ ጀርባቸውን ወደ ሕዝቡ አድርገው እንዲቀመጡ ሆኑ::



«ከዚያ በኋላ ስምንት ወታደሮች በስተ ጀርባቸው ሃያ ርምጃ ርቀው ተንበርክከው በተጠንቀቅ ቆሙ:: ወዲያው አዛዡ «ተኩስ» በማለት ትእዛዝ ሲሰጥ ስምንቱም ተኩሰው መቱዋቸው:: ግን በስምንት ጥይት ሳይሞቱ ቀሩ:: መሞታቸውንና አለመሞታቸውን ለማረጋገጥ ዶክተር ተጠራ:: ዶክተሩም እንዳልሞቱ አረጋገጠ:: ከዚያም ሌላ ወታደር በሦስት የሽጉጥ ጥይት ራስ ቅላቸውን መትቶ ገደላቸው:: ብፁዕነታቸው የተገደሉበት ቦታ መኻል አዲስ አበባ ዛሬ መታሰቢያ ሐውልታቸው ቆሞ በሚገኝበት ቦታ አካባቢ ነው::

«የብፁዕነታቸው አስክሬን ማንም እንዳ ይወስደው በአሰቸኳይ ከአዲስ አበባ ውጭ ማንም በማያውቀው ቦታ በምሥጢር እንዲቀበር ተደረገ:: በዚያች ሌሊት በአዲስ አበባ ውስጥ በየቤቱ ልቅሶና ዋይታ ሆነ::» /<u>ትንሣኤ</u> ፣ ቁጥር 58፣ 1978 ዓ.ም./::

ይህ ጋዜጠኛ የሰጠው ምስክርነት የኢትዮጵያን ሕዝብ ጀግንነት ሲያረጋግጥ ይኖራል:: የብፁዕነታቸውን በድን በተመለከተ አንዳንድ የቤተ ክርስቲያናችን አባቶች ቅዱሳን መላእክት የጻድቃንን በድን አያመጡ እንደ ሚያስቀምጡበትና በውስጡ የሚቀመጥ አስክሬን እንደ ማይፈርስ ወደ ሚነገርለት አቡነ መልከ ጸዴቅ ዋሻ /ሰሜን ሸዋ/ መላእክት ወስደው እንዳስቀመጡትና በዚያ እንደ ታዩ ይናገራሉ::

ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ በአደባባይ በተሰበሰበ ሕዝብ ፊት የሰማዕትነት ጽዋቸውን ሲቀበሉ ከሕዝቡ ጋር ሆና ታይ የነበረች አንዲት ከድጃ የምትባል የእስልምና እምነት ተከታይ ሴት በብፁዕነታቸው ፍፁም አባታዊ ቆራጥነት ተማርካ የእኒህን አባት እምነት አከተላለሁ ብላ በመጠመቅ ክርስቲያን ሆናለች ይባላል::

በተጨማሪም ደራሲና ጋዜጠኛ ጳውሎስ ኞኞ «አቡነ ጴጥሮስ እንዴት ሞቱ?» ሲል ሙሴ ፓይላክን ጠይቆአቸው እርሳቸውም የሚከተለውን ተናግረዋል:: «አቡነ ጴጥሮስ የተገደሉ ዕለት እዚያው ነበርኩ:: መጀመሪያ በእጃቸው ይዘውት የነበረውን መጽሐፍ ቅዱሳቸውን ተሳለሙት:: ቀጥለውም በያዙት መስቀል አማትበው ሕዝቡን ባረኩ:: የኪሳቸውንም ሰዓት አውጥተው ካዩ በኋላ መልሰው ከኪሳቸው ከተቱት:: ወዲያው ወታደሮች በሩምታ ተኩሰው ገደሉዋቸው:: ይህ እንደ ሆነ አስገዳዩ ኮሎኔል ተመልካቹን ሕዝብ አጨብጭቡ ብሎ አዘዘና ተጨበጨበ::

ማታ ከአስገዳዩ ኮሎኔል ጋር ተገናኝተን ስንጫወት «በዚህ ቄስ መገደል እኮ ሕዝቡ ተደስቷል» አለኝ:: «እንዴት?» ብለው «አላየህም ሲያጨበጭብ» አለኝ:: እኔም «ባታውቀው ነው እንጂ የሕዝቡ ባሕል ሲናደድም ያጨበጭባል» አልኩት:: «እንዴት?»

ቢለኝ እጄን እያጨበጨብኩ አሳየሁት:: እሱም አሳየኝ:: «ከዚህ በኋላ የሆነው ቢሆን እኔ ትልቅ ማስታወሻ አግኝቼአለሁ» ብሎ አቡነ ጴጥሮስ ሲገደሉ ይዘውት የነበረውን መስቀልና መጽሐፍ ቅዱስ፣ የኪስ ሰዓታቸውን ጭምር አሳየኝ:: መጽሐፍ ቅዱሱ መሐል ለመሐል በጥይት ተበስንጥቋል:: መስቀሉም ልክ በመሐከሉ ላይ ጥይት በስቶት ወጥቷል:: የኪስ ሰዓታቸውንም እንዳየሁት እንደዚሁ ጥይት በስቶታል» ብለው ያዩትን መስክረዋል::» /ዝኒ ከማሁ./::

የብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ጥብአት ማለትም ለሀገራቸውና ለእምነታቸው እስከ መጨረሻዋ ሰዓት ድረስ መስክሮ ማለፍ ምክንያቱ በልጅነታቸው ከቅኔ መምህራቸው የሰሙት የአደራ ቃል እንደሆነ ይነገራል:: አለቃ ተጠምቆ የተባሉ ቅድስናን ከሊቅነት አስተባብረው የያዙ መምህራቸው አንድ ቀን ብፁዕነታቸውን ጠርተው «ኃይለ ማርያም፣ አንተ ወደ ፊት ጳጳስ ትሆናለህ:: በዚያ ጊዜ አረመኔ በዚህች ሀገር ይሠለጥናል:: ታዲያ ያኔ አንተ ለነፍስህ ሳትሰቀቅ በሰማዕትነት እለፍ:: ሰማዕትነት ክፍልህ ነው:: አደራ» ብለዋቸው ነበር ይባላል:: ይህንን የመምህራቸውን የአደራ ቃል የያዙት ብፁዕነታቸው እስከ መጨረሻው ለነፍሳቸው ሳይፈሩ፣ እንዲትም ቀን ሳይሸሹ ከላይ በቀረበው ሁኔታ የሰማዕትነት ጽዋቸውን ሊቀበሉ ችለዋል::

ጠላት ድል ተደርጎ ሀገራችን ነፃነቷን ከተቀዳጀች በኋላ የብፁዕነታቸውን አኩሪ ታሪክ ትውልድ ቢያዘከርላቸው እንዲኖር መታሰቢያ ይሆናቸው ዘንድ በግርማዊ ቀዳማዊ ንጉሠ ነገሥት አሳሳቢነት ሐምሌ 16 ቀን 1938 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ አምብርት ሐውልት ቆሞላቸዋል:: ከድል በኋላ የብፁዕነታቸው ሐውልት ተመርቆ የቤተ መንግሥቱም ሆኑ የቤተ ክህነቱ ባለሥልጣናት የአበባ ጉንጉን ከሐውልቱ ሥር ቢያስቀምጡ ከቤተ ክህነት ካስቀመጡት አባቶች አንዱ በ1921 ዓ.ም አብረዋቸው የተሾሙት ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ ነበሩ:: የሐቀኛው አባታችን በረከት ይደርብን:: አሜን::



# 3.2. ብፁዕ አቡነ አብርሃም ቀዳማዊ

## «ጳጳስ ዘምዕራብ ኢትዮጵያ ተላዌ አሠሩ ለአቡነ ሐራ»


## /1861 – 1931 ዓ.ም/



# 3.2. ብፁዕ አቡነ አብርሃም ቀዳማዊ

## «ጳጳስ ዘምዕራብ ኢትዮጵያ ተሳዌ አሠሩ ለአቡነ ሐራ»

## /1861 – 1931 ዓ.ም/



ብፁዕ አቡነ አብርሃም በጎጃም ሀገረ ስብከት በሞጣ አውራጃ ልዩ ስሙ አሸመን ከተባለው ቦታ ሐምሌ 5 ቀን 1861 ዓ.ም. ተወለዱ። ለድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በምሥጢረ ጥምቀት ልጅነትን ባገኙባትና አጥቢያቸው በሆነችው የቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊደል እና የቃል ትምህርቱን ተምረው ዳዊት ደገሙ።

ከወላጆቻቸው ሳይርቁ በእማረ ሁናቴ የጀመሩትን ትምህርት በመቀጠል በአካባቢያቸው ወደ ሚገኙ የዜማና የቅኔ ትምህርት ቤቶች በመዘዋወር ጸዋትወ ዜማንና ቅኔን በአግባቡ ተማሩ። በመቀጠልም በወቅቱ በጎጃም ክፍለ ሀገር ስመ ጥር የመጻሕፍት ትርጓሜ ቤት ከነበረው ሞጣ ጊዮርጊስ ብሉያቱንና ሐዲሳቱን አጠኑ። መጻሕፍተ ሊቃውንቱንና መነኮሳቱንም በሚገባ አጠናቀቁ።

ብፁዕነታቸው የተማሯቸውት ትምህርት ይበቃኛል ሳይሉ ዕውቀታቸውን ለማስፋፋት ወሎ ቦሩ ሥላሴ ወደ ነበሩት ስመ ጥርው መ/ር አካለ ወልድ ዘንድ ሔዱ። ጎጃም የተማሩትን እንደ ገና እንደ አዲስ በመጀመር አራቱንም ጉባኤያት በሚገባ በመከለስ ዕውቀታቸውን አስፋፉ። የብፁዕ አቡነ አብርሃምን ሊቅነት ያዩ የመ/ር አካለ ወልድ ተማሪዎች ከመማር ጐን ለጐን ጉባኤ ዘርግተው እንዲያስተምሩ ጥያቄ አቀረቡ። መምህር አካለ ወልድም የተማሪዎቻቸውን ጥያቄ ተቀብለው ቁጥሩ ከበዛው ተማሪያቸው በመክፈል የተወሰኑ ተማሪዎች ለብፁዕነታቸው ሰጧቸውና እየተማሩ ማስተማር ጀመሩ። ብፁዕነታቸው ለሚያስተምሯቸው ተማሪዎች ምሥጢር ከምሥጢር አገናኝተው፣ የራቀውን አቅርበው፣ የረቀቀውን አፍታተው ሲያቀርቡ እንኳን ተማሪዎቻቸው ታላቁ ሊቅ መ/ር አካለ ወልድም ይደነቁ ነበር ይባላል።

ቦሩ ሥላሴ ከላይ በተገለጠው ሁኔታ እያስተማሩ ረዘም ላለ ጊዜ ከመምህር አካለ ወልድ ዘንድ ከተማሩና የምስክር ወረቀታቸውን ከያዙ በኋላ ወደ ተወለዱበት አካባቢ ጎጃም በመሔድ ጉባኤያቸውን አስፋፍተው ማስተማር ጀመሩ። የዘረጉት ጉባኤ ዕለት ከዕለት እየሰፋና እየጐለበተ በመምጣት ላይ ሳለ እንደ አባታቸው አብርሃም አበ ብዙኃን ሊያደርጋቸው ያሰበ እምላክ በስውር ጥበቡ ወደ አዲስ አበባ እንዲመጡ አደረገ።

ከጎጃም ተነሥተው ወደ አዲስ አበባ የመጡት ብፁዕ አቡነ አብርሃም ሳይውሉ ሳያድሩ በአዲስ አበባው መንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን በእልቅና ተሾሙ። ብፁዕነታቸው በዚያ ጊዜ የንግሥተ ንግሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ የጸሎት መጻሕፍት አንባቢና አሳላሚ ሆነው ያገለግሉ ነበር። ከተሾሙም በኋላ ሊቅነታቸውን የሰሙ የመጻሕፍት ተማሪዎች ከክፍለ ሀገርም ሆነ ከአዲስ አበባ በመሰብሰብ ስለ ከበቧቸው ጉባኤያቸው ከሙሉውም ጊዜ



በበለጠ ሁኔታ እየሰፋ መጣ። በዚህም ሐዲስ ለሚማረው ሐዲስ፣ ብሉይ ለሚማረው ብሉይ፣ ሊቃውንት ለሚማረው መጻሕፍተ ሊቃውንት፣ መነኮሳት ለሚፈልገው መጻሕፍተ መነኮሳት በየዓይነቱ በሚያጠግብ ሁኔታ ያስተምሩ ጀመር። ለተማሪው ዕውቀት መንፈሳዊን ከመመገብ ጋርም ዐቅማቸው የፈቀደውን ያህል ለተራበው እያጐረሱ፣ ለተጠማው እያጠጡ፣ ለታረዘው እያለበሱ ተማሪዎቻቸውን ይንከባከቡ ነበር ይባላል።

በዚህ ዓይነት ለተወሰኑ ዓመታት የቆዩት ብፁዕ አቡነ አብርሃም በቤተ ክርስቲያኗና በሀገሪቱ መንግሥት በ1921 ዓ.ም. በተደረገው የእጩ ጳጳሳት ምርጫ ከተመረጡት አባቶች አንዱ ሆኑ።

በዚህም ብፁዕነታቸው ግንቦት 18 ቀን 1921 ዓ.ም. በካይሮ ቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ከሌሎች ሦስት ወንድሞቻቸው ጋር መዓርገ ጵጵስናን ተቀበሉ። ወደ ሀገራቸው ከተመለሱም በኋላ «አባ አብርሃም ጳጳስ ዘምዕራብ ኢትዮጵያ ተላዌ አሠሩ ለአቡነ ሐራ » በሚል ተሠይመው በጎጃም፣ በጎንደርና በሜን አህጉረ ስብከት ተሾሙ። /*የሹመት ደብዳቤያቸውን በአባሪ 1 ይመለከቷል*/።

ከሕፃንነታቸው ጀምሮ ለትምህርት ሲሉ ከቦታ ቦታ ሲዘዋወሩ የኖሩት ብፁዕ አቡነ አብርሃም ቅዱሳት መጻሕፍትን አብዝተው ከመመርመራቸው የተነሣ ዓይናቸውን፣ ትጎርምት ከማብዛታቸው የተነሣም አንጀታቸውን በተለያዩ ጊዜያት ያማቸው ነበር። ይሁን እንጂ የሚደርስባቸው ሥጋዊ ፈተና እንቅፋት ሳይሆንባቸው ሕማሙ ጠንቶባቸው አልጋ ላይ እስኪውሉ ድረስ ሕዝበ ክርስቲያኑን ከማስተ ማር፣ ሥራቸውንም ከመሥራት አልታቀቡም ነበር። በዚህ ሁሉ ደገኛ ተግባራቸው የተነሣ ምእመናን «አማናዊው አብርሃም» እያለ ይጠራቸው ነበር ይባላል።

ብፁዕነታቸው ቃለ እግዚአብሔርን ለሕዝበ ምእመናን በማዳረስ በኩል ላቅ ያለ አስተዋጽኦ ያበረከቱ አባት ነበሩ። ከዚህም ውስጥ የሚጠቀሰው በዐውደ ምሕረት ቃለ እግዚአብሔርን ለምእመናን መስበክ በመጀመር የከፈቱት አዲስ የአገልግሎት መሰመር ነው። ብፁዕነታቸው ይህንን አገልግሎት ከመጀመራቸው በፊት ቃለ እግዚአብሔር በቅዳሴ ጊዜ ተነቦ በአጭሩ ከሚተረጎም በስተቀር በባክያን ለስብከተ ወንጌል በፊ መርሐ ግብር ይዘው ምእመናንን አያስተምሩም ነበር። የዐውደ ምሕረት ስብከተ ወንጌል አገልግሎት በብፁዕነታቸው ከተጀመረ በኋላ ግን ይኸውና ዛሬ ድረስ በብዙ አብያተ ክርስቲያናት ምእመናን ዘወትር በሠርክ በዐውደ ምሕረት እየተሰባሰቡ ቃለ እግዚአብሔርን ይማራሉ።

ብፁዕ አቡነ አብርሃም የሀውደ ምሕረትን የስብከተ ወንጌል አገልግሎት እንዲያከናውኑ የነፍስ ልጃቸው የነበሩት ንግሥተ ንገሥታት ዘውዲቱ ትልቅ ድጋፍ እንዳደረጉላቸው ይነገራል። እንደ ሚታወቀው ንግሥተ ንገሥታት ዘውዲቱ ለቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትና ካህናት ይሰጡት ከነበረው አክብሮትና ከብካቤ እንዲሁም ሥልጣን የተነሣ የእሳቸው ዘመን «ዘመነ ካህናት» ተብሎ ይጠራል።

ከላይ እንደ ተገለጠው ብፁዕነታቸው በነበራቸው ዕውቀትና ቅድስና በንግሥቷ ዘመን በቤተ መንግሥቱ ላቅ ያለ ክብርና ሥልጣን ካገኙት አባቶች አንዱ ነበሩ። የንግሥቷ አበ ነፍስ በመሆናቸው በቤተ መንግሥቱ አካባቢ በነበረው መንፈሳዊ እንቅስቃሴና በሚወጣው መመሪያ ትልቅ ተሳትፎ ነበራቸው። ታዲያ በዚህ መዓርግና አገልግሎት ላይ ሳሉ ንግሥቷ ከዚህ ዓለም በሞት ይለያሉ። በዚህ የተነሣ ምንም እንኳን በንግሥቷ ሞት መላው የኢትዮጵየያ ሕዝብ ይልቁንም በንግሥቷ እንክብካቤ ለከፍተኛ ሹመትና መዓርግ የበቁት ሊቃውንት በእጅጉ አዝነው ነበር። ከእነዚህ ሰዎች አንዱ ደግሞ ብፁዕ አቡነ አብርሃም ነበሩ ታዲያ ብፁዕነታቸው ዘወትር ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ይህንን ሐዘናቸውን ይገልጹ ነበር ይባላል። አንድ ቀን እንደ ተለመደው በዐውደ ምሕረት ቃለ እግዚአብሔርን ለምእመናን ሲያሰሙ ያስተማሩበት ርዕስ «አንከሰ ጸርሐት ቤተ ክርስቲያን ፤ እንግዲህስ ቤተ ክርስቲያን ትጮኻለች» የሚል ነበር። በዚህ ርዕስ በነበራቸው የጣዕመ ስብከት ጸጋ በቃለ እግዚአብሔር እያዋዙ ንግሥተ ንግሥታቷ አዝነውና ተጎሳቁለው ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸው ቤተ ክርስቲያን እንደምታዝን፣ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያንና ልጆቿ ያደረጉትን በጎ ሥራ ሁሉ ቆጥሮ ነፍሳቸውን በአብርሃም፣ በይስሐቅና በያዕቆብ አጠገብ እንዲያበቀምጥ ቤተ ክርስቲያን በእጅጉ እንደ ምትጸልይ ያስተምራሉ። ይህንኑ ትምህርታቸውን በሌሎች ጉባኤያትም ይደጋግማሉ። በዚህ ጊዜ ብፁዕነታቸው ስለ ንግሥተ ንገሥታቷ መሞት የተሰማቸውን ሐዘንና ስለ አሟሟታቸው ሁኔታ በዐውደ ምሕረት እየገለጹ እንደሆነ ንጉሡ ይሰማሉ። ንጉሡም ወዲያውኑ ብፁዕነታቸውን አስጠርተው «ምነው በንግሥተ ንግሥታቷ ማረፍ ይኸንን ያህል አዘኑ? እኛስ ክርስቲያኖች አይደለንም እንዴ? እንደዚህ ሊሆኑ አይገባም» አሏቸው። ብፁዕነታቸውም የንጉሡን አባባል ባለመቀበል «ሐዘንተኛ እንደ ቢጤቱ ነው የሚያለቅሰው። በተሰማው መንገድ ሊያለቅስ ይችላል እንጂ በዚህ መንገድ አልቅስ፤ በዚያ መንገድ አታልቅስ አይባልም» አሏቸው ይባላል።

ብፁዕነታቸው በተለይ በሀገረ በብከታቸው ጎጃም ሕዝቡ ቃለ ወንጌል በሰፊው እንዲሰማ፣ የአብነት ትምህርት ቤቶች እንዲስፋፉ፣



ሊቃውንትም ርስት ጉልት እንዲያገኙ ሰፊ ጥረት ያደርጉ ነበር ይባላል። በወቅቱ በአካባቢው የቅብዐት ትምህርት በስፋት ነበረና የቅብዐት ሊቃውንትን ጥልቅ በሆነ ዕውቀታቸው በቃልም በመጣፍም ይረቷቸውና ያስረቷቸው እንደ ነበር ይነገራል። በዚህ ከተደሰቱት የተዋሕዶ ሊቃውንት መካከል አንዱ በቅኔ ሊያወድሳቸው የሚከተለውን ሐረግ ሊቀኝ፤ በጅምሩ የተደሰቱት ብፁዕነታቸው ወደ ሁለተኛው ሐረግ ሳይሔድ «በቃ በቃ፤ ይኸው ይበቃል ታበለሸዋለህ» አሉት ይባላል። በመሆኑም እስከ ዛሬ ድረስ በርካታ ሊቃውንት የሚያውቋት ከዚህ በታች የተጻፈችዋን ስንኝ ብቻ ነው።

*አ አብርሃም ነድዕ የቅብዐት ማቅለሜ*

ታዲያ አንረታም ያሉት የቅብዐት መምህራንም ለተበረከ ተላቸው ቅኔ መልስ ይሆን ዘንድ በሚከተለው ሐረግ የሚጀምር ቅኔ ዘርፈዋል ይባላል።

*ቅብዕ እስመ ያለፍአ ለአብራም አነዳ*

ብፁዕነታቸው በጎጃም ባበረከቱት ሰፊ አገልግሎት ዛሬ ድረስ በአካባቢው አረጋውያን ዘንድ ስማቸው አልተረሳም። ከላይ እንደ ተገለጠው በነበራቸው ሊቅነት የቅብዐትን ሊቃውንት ከመርታታቸው በተጨማሪ በነበራቸው የተቸገረን የመርዳት ጸጋ በገንዘባቸው እየረዱ ብዙዎችን አስተምረው ለወግ ለመዓርግ አብቅተዋልና።

ብፁዕነታቸው የኢጣልያ ወራሪ ጦር ሀገራችንን በግፍ በወረረ ጊዜ በሊቃውንት ተመርጠው ግብፃዊው የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ቄርሎስ ትተውት የሔዱትን መንበረ ጵጵስና ኅዳር 21 ቀን 1930 ዓ.ም በመረከብ በሊቀ ጳጳሳትነት እስከ ዕለተ ዕረፍታቸው በቅንነትና በትጋት አገልግለዋል። በተሾሙበት ዕለትም እንደ ታላቁ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ጉባኤ ውሳኔ ሌሎች አምስት ጳጳሳትንና አንድ ኤጲስ ቆጳስን ሹመዋል። እነሱም እቡነ ዮሐንስ ጳጳስ ዘሸዋ፣ አቡነ ማርቆስ ጳጳስ ዘኤርትራ፣ አቡነ ሰላማ ጳጳስ ዘሐረር፣ አቡነ ገብርኤል ጳጳስ ዘጎንደር፣ አቡነ ማቴዎስ ጳጳስ ዘወሎና አቡነ ሉቃስ ጳጳስ ዘወለጋ ናቸው። በምዕራፍ አንድ እንደ ተገለጠው በዚህ የተነሣ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን አላግባብ አውግዛቸው ነበር።

በመጨረሻ ብፁዕነታቸው በዚህ ዓለም ከአንድ መንፈሳዊ አባት የሚጠበቀውን ካከናወኑ በኋላ ሐምሌ 24 ቀን 1931 ዓ.ም. ስኖ ከጠዋቱ ልክ በአንድ ሰዓት ተኩል ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ።


ሐምሌ 26 ቀን 1931 ዓ.ም. ለሊቀ ጳጳሳት ዕረፍት የሚገባው ጸሎተ ፍትሐት ከተደረገ በኋላ ሥርዓተ ቀብራቸው አዲስ አበባ በሚገኘው የቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን ቤተ መቅደስ መንበር አጠገብ ተፈጸመ:: የብፁዕነታቸው በረከት ይደርብን:: አሜን::



## 3.3. ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ቀዳማዊ

## «ጳጳስ ዘአዜበ ኢትዮጵያ ተላዌ አሠሩ ለአቡነ ዜና ማርቆስ»

## /1870 – 1929 ዓ.ም/



# 3.3. ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ቀዳማይ

## «ጳጳስ ዘአዜበ ኢትዮጵያ ተሳዌ አሠሩ ለአቡነ ዜና ማርቆስ»

## /1870 – 1929 ዓ.ም/



መዓርገ ጵጵስናን ከመቀበላቸው በፊት አባ ኃይለ ሚካኤል
ይባሉ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ሚካኤል በቀድሞው ቤጌምድር ጠቅላይ
ግዛት አፈረ ዋናት ልጫ መስቀለ ክርስቶስ በተባለ ቦታ ተወለዱ።
በዚያው በተወለዱበትም አካባቢ ግንድ አጠመም ቅዱስ ሚካኤል
ቤተ ክርስቲያን በጥምቀት እንደ ገና ሲወለዱ ስመ ጥምቀታቸው
ኃይለ ሚካኤል ተባለ።

ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በዚያው በትውልድ ሀገራ
ቸው ግንድ አጥም ሚካኤል በተባለው ቤተ ክርስቲያን ከነበሩት
መሪ ጌታ ዋሴ ከተባሉ አስተማሪ የመጀመሪያ ደረጃ የቤተ ክህነት
ትምህርታቸውን አጠናቀቁ። ከዚያ በኋላ ከግብፃዊው አቡነ ጴጥሮስ
መዓርገ ዲቁና ተቀብለው በዚያው በትውልድ ሀገራቸው ዘገቦ ጽዮን
በተባለ ቤተ መቅደስ በዲቁና አገለገሉ።

ብፁዕነታቸው ትምህርታቸውን በመቀጠል እዚያው ጎንደር
መካነ ሰማዕት ቅዱስ ገላውዴዎስ ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ዘርግተው
ያስተምሩ ወደ ነበሩት መሪ ጌታ ተድላ ዘንድ ሔደው ጸዋትወ
ዜማን፣ ማኅደረ ማርያም ከነበሩት መ/ር ወልደ ሩፋኤልም ድጓ
በሚገባ ተማሩ።

የዜማ ትምህርታቸውን በተገለጠው ሁኔታ ያጠናቀቁት
ብፁዕ አቡነ ሚካኤል መጻሕፍትን ለመማር በነበራቸው ፍላጐት
የተነሣ ወደ ጎንደር ከተማ በመሔድ ከመ/ር ተስፋዬ ዘንድ የብሉ
ያትንና የሐዲሳትን ትርጓሜ በሚገባ ተማሩ። በጎንደር የጀመሩትን
የመጻሕፍት ትርጓሜ ትምህርት የበለጠ መማር እንዳለባቸው
ሕሊናቸው ስላነሣሣቸው በወቅቱ ስመ ጥር ወደ ነበሩትና ቀደም
ሲል ታሪካቸው የቀረበላቸው አባቶች መምህር ወደ ነበሩት መምህር
አካለ ወልድ ዘንድ ተሻገሩ። በዚያም ሐዲሳቱን በሚገባ በማስፋፋትና
ቅኔን ከነምሥጢሩና አገባቡ ጠንቅቀው ለቅኔ መምህርነት በቅተዋል።

መንፈሳዊውን ትምህርት ከዳር ለማድረስ ቆርጠው የተነሡት
ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ከቦሩ ሥላሴ ወደ አዲስ አበባ መጥተው በገነተ
ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ደብር ሰፊ ጉባኤ ዘርግተው ያስተምሩ ከነበሩት
መ/ር ወልደ ጊዮርጊስ ዘንድ የዓሥራ አራቱን ቅዳሴያት ዜማ
በጥንቃቄ ተማሩ። በዚህ ጊዜ በወቅቱ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ
ከነበሩት ግብፃዊው አቡነ ማቴዎስ መዓርገ ቅስናን ተቀበሉ።

በዚህ ሁሉ ሒደታቸው፣ ትምህርታቸውና ግብረ ገብነታቸው
በሰዎች ዘንድ ስለ ተመሰከረ ይህም በቤተ መንግሥቱ በመለማቱ
ለመኳንንቱ፣ ለመሣፍንቱና ለወይዛዝርቱ አበ ነፍስ ለመሆን በቁ።
ሞያቸውና ግብረ ገብነታቸው የበለጠ ከዕለት ወደ ዕለት እየተጠ
ናከረና እየተመሰከረ በመሔዱም ከአበ ነፍስነት አገልግሎት አልፎ



ወደ ቤተ መንግሥቱ በመግባት የምክር ድጋፍ እንዲያደርጉ
ተሾሙ።

ከንጉሡ ቤተ መንግሥት በሚወጣው ሕግና መመሪያ በቀ
ጥታ ተሳታፊ በመሆን በማገልገል ላይ የነበሩት ብፁዕነታቸው ከዚያ
ከፍ ላለውና ለትምህርታቸውና ለማንነታቸው ተስማሚ የሆነ ቦታ
ተመርጦላቸው የዜና ማርቆስና የዝቋላ ገዳማት አስተዳዳሪ ሆነው
ተሾሙ። የተሰጣቸውን ሐላፊነት በብቃት እየተወጡ ጥቂት ዓመ
ታት ከቆዩ በኋላ እንደ ገና በአዲስ አበባው ደብረ ጽጌ ቅዱስ ዑራ
ኤል፣ ቆይቶም በማኅደረ ማርያም በአልቅና ተሹመው ለምእመናኑ
ትምህርት በመስጠት፣ ካህናትን በማትጋት ሲያገለግሉ ቆዩ።

በኮፕትና በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መካከል ለረጅም
ዘመናት ዘልቆ የነበረው የጵጵስና ሹመት ክርክር ተፈጽሞ
ኢትዮጵያውያን ወደ ጵጵስና ሹመት መድረክ እንዲቀርቡ በተደረገ
ጊዜ ለታላቁ ሹመት ከተመረጡት አባቶች ብፁዕ አቡነ ሚካኤል
አንዱ ሆኑ። ከሌሎች አባቶች ጋር ወደ ካይሮ በመሔድም ግንቦት
18 ቀን 1921 ዓ.ም. መዓርገ ጵጵስናን ተቀበሉ።

አቡነ ሚካኤል ተብለው ወደ ሀገራቸው የተመለሱት ብፁዕነ
ታቸው ከዓመት በኋላ «አባ ሚካኤል ጳጳስ ዘአዜብ ኢትዮጵያ ተላዌ
አሠሩ ለአቡነ ዜና ማርቆስ» ተብለው በኢሊባቡርና በከፋ ጠቅላይ
ግዛቶች ተሾሙ።

ዕድሜያቸውን በሙሉ በትምህርትና በትኅርምት ያሳለፉት
ብፁዕነታቸው የዘወትር ዓላማቸው ምእመናንን ማስተማር ነበረና
በተሰጣቸው ሀገረ ስብከት የሚገኙ የመንፈስ ቅዱስ ልጆቻቸውን
በመንፈሳዊ ትምህርትና ምክር ያጠናክሩ፣ ተወዳጅ የነበረውንም
ሐዋርያዊ ተልዕኮአቸውን ያፋጥኑ ጀመር። በዚህ ተግባራቸው እርሳ
ቸውም እየተደበቁና እግዚአብሔርን እያመሰገኑ፣ ምእመናንም
በብፁዕነታቸው ትምህርተ ወንጌል እየረኩ ቅድስት ቤተ ክርስቲያ
ናቸውን እያወቁ ለሰባት ዓመታት ቆዩ።

ምንም እንኳን በቂ ናቸው ባይባልም ያሉት አራት አባቶች
ኢትዮጵያን ተከፋፍለው ለረጅም ዘመናት በቋንቋው የሚናገር አባት
አጥቶ የቆየውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከካህናቱና ሲቃውንቱ ጋር
በመተባበር እውነተኛውን የወንጌል ትምህርት እያስ ተማሩ ከቤተ
ክርስቲያኑ ጋር በማስተዋወቅ ላይ ሳሉ በ1928 ዓ.ም. ግፈኛው
የኢጣልያ ፋሽስት ጦር ኢትዮጵያን በግፍ ወረረ። ወረራ ውም
ከሰሜኑና መካከለኛው የሀገሪቱ ክፍል አልፎ ከእሳቸው ሀገረ ስብከት
ደርሶ መንበረ ጵጵስናቸው የነበረበት የጎሬ ከተማ ኮሎኔል ማሌታ
በተባለ የጦር አዛዥ በሚመራ የጦር ኃይል እጅ ወደቀ። በዚህ ጊዜ

ብፁዕነታቸው መንበረ ጵጵስናቸውን ለቀው ሰምቢ ወደ ተባለች የገጠር ቀበሌ በመሔድ በፍጹም አባትነት፣ ስሜትና ወኔ «ኢትዮጵያ የኢትዮጵያውያን ብቻ እንጂ የሌላ አይደለችም» በማለት የሀገረ ስብከታቸው ሕዝብ ባሕር አቋርጦ ሊወረው በመጣው ጠላቱ ላይ እንዲነሣ መስበክና መቀስቀስ ጀመሩ::

ብፁዕነታቸው ምንም እንኳን የመንፈስ ወንድማቸው የሆኑትን የብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ቀዳማዊን አኩሪ ሰማዕትነት ሰምተው ቢደሰቱም፣ በአንጻሩ በጊዜው ከጠላት ጦር ጋር የተስማሙ አባቶች በፋሺስቱ ወራሪ ኃይል ተልከው ለምልጃ ስለመጡባቸው አዝነው ነበር ይባላል:: አቶ ታደሰ ሜጫ የተባሉ አርበኛ «ጥቁር አንበሳ በምዕራብ ኢትዮጵያ» በሚል ርዕስ ስለ ገነት ጦር ትምህርት ቤት ምሩቃንና «ጥቁር አንበሳ» ተብሎ ይታወቅ ስለነበረው ሠራዊት ተጋድሎ በጻፉት ታሪክ ውስጥ ብፁዕነታቸው በወቅቱ ስለነበራቸው ቆራጥ አቋም የሚከተለውን ምስክርነት ሰጥተውላቸዋል:: «... ጎሬ በገባን ጊዜ ብፁዕ አቡነ ሚካኤል በከተማው እንደ ሚገኙ ሰማን:: መልእክታችንን ለከቡር ራስ እምሩ አድርሰን ወደ ተሰጠን ሠፈር ከመመለሳችን በፊት የጥቁር አንበሳን ሰላምታ ይዘን ወደ ብፁዕነታቸው መኖሪያ ሔድን:: እርሳቸውም ከተቀበሉንና ቃለ ቡራኬ ከሰጡን በኋላ ከዋነኞቹ መልእክተኞች ጋር ተነጋግረው የማበረታቻ ቃላቸውንም ወደ ጥቁር አንበሳ ጦር እንዲያደርሱላቸው አሳሰበው በቡራኬ አሰናበቱን:: እኛ ወደ ጥቁር አንበሳ ጦር እንድናደርስላቸው አሳስበው በቡራኬ አሰናበቱን:: እኛ ወደ ጥቁር አንበሳ ጦር ከተመለስን በኋላ ራስ እምሩም ጎሬን ለቀው ወደ እኛ በመጡ ጊዜ ብፁዕነታቸው በዚያው ያሉትን ምእመናን ለነጣቂ ተኩላ ጥዬ አልሔድም በማለት መንፈሳዊ ተግባራቸውን በቆራጥነት ያከናውኑ ነበር::»

ስለ እኚሁ ታላቅ የሀገርና የቤተ ክርስቲያን አባት ጣልያን ኢትዮጵያን በወረረችበት ወቅት እስከ ሕይወታቸው ፍጻሜ የኢትዮጵያና ሕዝቦቿ ጽኑ ወዳጅ የነበሩት ስዊድናዊ ኮሎኔል ካውንት ካርል ጉስታፍ በንሮዝን የሚከተለውን የምስክርነት ቃል ሰጥተዋል:: «ፎከር የምትባለውን አውሮፕላን እያበረርኩ በጎሬ አቅራቢያ አረፍኩ:: በምዕራብ ኢትዮጵያ የነበሩትን ስደተኞች አግኝቼ በራስ እምሩ ይመራ ለነበረውም ጦር መገናኛ ከፈትኩ:: ጎሬ እንዳረፍኩ ብፁዕ አቡነ ሚካኤል አስጠሩኝ:: 'በርግጥ አንተ ዘመዶችህን ከድተህ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ለማገልገል ወስነሃልን? ክርስቲያን ነኝ ብለኸኛል:: ለዘመዶችህ ሳታዳላ ለዚች ለተጨነቀች ሀገር ከልብህ ለመሥራት መወሰንህን መስቀሌን በመምታት ማልልኝ' ሲሉኝ የሀገር ፍቅር እንዳቃጠላቸው ተሰማኝ:: 'ጓደኞቼ በዕለት



ጥቅም እየተደለሉ ለጠላት ማደራቸውን ስሰማ በጣም አዘንኩ:: ሌላው የልብ ጓደኛዬ አቡነ ጴጥሮስ ግን ለጠላት አልገዛም ብለው ለመሥዋዕትነት መቃረባቸውን ስሰማ በጣም ደስ አለኝ:: ይህ ነው መሐላን ማክበር:: እኔም የምከተለው የጴጥሮስን ፈለግ ነው::' ብለው አጫወቱኝ:: ቆራጥነታቸውን ሳደንቅ ፋሺስት ንጹሐንን ለምን እንደሚገድል በማሰብ በጣም ተገረምኩ:: ምስቀላቸውን መትቼ ከጎሬ ተመለስኩ:: ወደ ሎንዶን ከሔድኩ በኋላ ጳጳሱ ተገድለው ጎሬም በጠላት መያዟን ስሰማ በጣም አዘንኩ:: አቡነ ሚካኤል ከማልዘንጋቸው ቆራጥ ኢትዮጵያውያን አንዱ ናቸው:: በነጻነት ጉዳይ ኢትዮጵያውያን የተለየ አቋም አላቸው:: ቋንቋ ፈጽሞ አያግዳቸውም:: አይበግራቸውም::ሁሉም በሀገራቸው ጉዳይ ቀልድ እንደማያውቁ የጎሬው ጳጳስ የአቡነ ሚካኤል ጥንካሬ በሚገባ አስረድቶኛል:: የጳጳሱ ድፍረትና የሀገር ፍቅር ምን ጊዜም አይረሳኝም::»

ይህ የብፁለነታቸው ስብከት ለወራሪው ኃይል ትልቅ እሳት ሆነ:: ይህንንም በተረዳ ነገር ያወቀው ፋሺስት ፈቃደኛ ከሆኑ ሕዝቡ «መንግሥቴ የጣልያኑ ፋሺስት መንግሥት ነው» ብሎ ይቀበል ዘንድ እንዲሰብኩ፣ ካልፈቀዱ ግን መስበካቸውን እንዲያቆሙ ለሁለተኛ ጊዜ በደብዳቤ ጠየቃቸው:: ሰውም ልኮ አስጠየቃቸው:: ብፁዕነታቸው ግን በዓላማ መጽናትን ያውቁበታልና ከእውነተኛው የሀገር ፍቅር ዓላማቸው እንደ ማያፈገፍጉ፣ እስከ መጨረሻውም ደማቸውን አፍስሰው ለውድ ሀገራቸው ቤዛ ለመሆን የማይቀዘቅዝ ስሜት እንዳላቸው በሙሉ ልብ አረጋግጠው ላኩበት::

ይህንን የብፁዕ አቡነ ሚካኤልን ጽናት የተረዳው ፋሺስትም የብፁለነታቸውን ዐቋም በማረጋገጥ ያሰበውን ለመተግበር በሌሎች ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ላይ እንደ ፈጸመው ሁሉ በእርሳቸውም ላይ የግድያ ርምጃ ለመፈጸም ወሰነ:: ብፁዕነታቸውም ለጠላት በአንደበታቸው ባረጋገጡለት መሠረት በሀገረ ስብከታቸው ከአውራጃ ወደ ወረዳ እየተዘዋወሩ ሕዝቡ የተባበረ ክንዱን በጠላት ላይ እንዲያነሣ ከውግዘት ጋር መስበካቸውን ቀጠሉ:: በስብከት ጉዞ ላይ እንዳሉ እዚያው ሰምቢ ቀበሌ አጠገብ ከሚገኝ ጫካ ውስጥ በጠላት ጦር ተከብበው በቆራጥነትና በእርበኝነት ሲዋጉ አንድ ሌሊት ካደሩ ሁለት አርበኞች ጋር ተማረኩ::

ከዚያም ከኮሎኔል ማሊታ ፊት ቀርበው ሕዝብን ከማነሣሣት ሥራቸው ተቆጥበው የማረጋጋት ሥራ ለምን እንደማይሠሩ በሕዝብ ፊት ጠየቃቸው:: ቆራጡ ብፁዕ አቡነ ሚካኤልም በጠላት እጅ መውደቃቸው ምንም ሳያስፈራቸው የፋሽስትን በኢትዮጵያ የበላይነት ወይም አስተዳዳሪነት መንበር መቀመጥ በፍጹም ዕውቅና የማይሰጡትና የማይቀበሉት መሆኑን፣ ኢትዮጵያ የኢትዮጵያውያን ብቻ

መሆንዋን፣ ይህንንም ሐቅ አስመመስከር፣ ሕዝቡንም ለትግል አለ ማስተባበር ፍጹም ኃጢአት መሆኑን በድፍረት ዘርዝረው አስረዱ:: «እኔ የማምነው በአንድ እግዚአብሔር ነው:: የምቀበለውም የነጻነታችን ምልክት የሆነውን የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ብቻ ነው:: ኢጣሊያ የሚባል ገዥ አላውቅም:: ለፋሺስት ኢጣልያ የተገዛ እንደ አርዮስ የተረገመ ይሁን:: እንኳንስ ሕዝቡ ምድሪቱም እንዳትገዛላቸው እውግዜአለሁ::» በማለት በዚያ ለተሰበሰበው ሕዝብና ሠራዊት ውግዘታቸውን አሰሙ::

ይህንን ቆራጥነታቸውን ከእንደበታቸው የተረዳው ፋሺስትም በሰጡት ቁርጠኛ መልስ ተናዶ እርሳቸውንና አብረዋቸው የተያዙትን ቀኝ አዝማች ይነሡና ግራ አዝማች ተክለ ሃይማኖት ይባሉ የነበሩ አርበኞችን ለሰምንት ቀናት ያህል ሌሊት በውርጭ ቀን በፀሐይ ሲያሰቃያቸው ሰነበተ:: በመጨረሻም ኅዳር 21 ቀን 1929 ዓ.ም. ከተያዙት ሁለት አርበኞች ጋር በጥይት ተደብድበው እንዲሞቱ ፍርድ አስተላለፈ:: ትእዛዙ ተግባራዊ ሲሆን ከጎሬ ቤተ ክርስቲያን በታች እሮጌው ቄራ አጠገብ ጉድጓድ ተቆፈረ:: በጉድጓዱ ዳር አብረዋቸው በተያዙ ሁለት ሰመ ጥር አርበኞች /ቀኛዝማች ይነሱና ግራዝማች ተክለ ሃይማኖት/ መካከል ብፁዕነታቸው እንዲቆሙ ተደረገ::በዚሀን ጊዜ አቡነ ሚካኤል ሰጥቂት ደቂቃዎች ጸሎት እንዲያደርጉ ጠይቀው ተፈቀደላቸው:: ጸሎታቸውን አድርሰው ቢያበቁ መስቀላቸውን ግንባራቸው ላይ «ብል እንግዲህ የፈለከውን አድርግ» አሉ:: በዚህ ጊዜ የወታደሮቹ አዛዥ የተኩስ ትእዛዝ ሰጠ:: ከእነ አቡነ ሚካኤል ፊት ለፊት በተርታ ተሰልፈው በመንፈሳዊው አባትና በአርበኞቹ ላይ ጠብ መንጃቸውን ያነጣጠሩት የጣላት ወታደሮች አንድ ላይ በእሩምታ ተኮሱ:: ብፁዕነታቸውና ሁለቱ አርበኞች በተተኮሱባቸው ጥይቶች ተመትተው ወደቁ:: በዚህ ዓይነት ብፁዕነታቸው ኅዳር 24 ቀን 1929 ዓ.ም. በሰማዕትነት ዐረፉ:: አቶ ወልደ አብ የተባሉ ሀገር ወዳድ የአካባቢው ነዋሪ ሰው የብፁዕነ ታቸውን አስከሬን ምንም እንኳን ከወደቀበት ጉድጓድ አንስተው ወደ ቤተ ክርስቲያን ወስደው መቅበር ባይችሉም እዚያው በወደቀበት ጉድጓድ በሌሊይ ሔደው በአግባቡ እንደ ቀበሯቸው ይነገራል::

ከዚህ በኋላ የአካባቢው የጣላት ጦር ዋና አዛዥ የነበረው ኮሎኔል ማልታ በጎሬ ከተማና በአካባቢው በሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት የሚያገለግሉትን ካህናት በሙሉ ሰብስቦ ገለፃ አደረገላቸው:: «አቡነ ሚካኤል የተገደሉት ለኃያሉ የኢጣሊያ መንግሥት አልገዛም በማለታቸው ነው:: ሕዝቡም እንዳይገዛ በማውገዝ በእንቢተኛነታቸው ጸንተው በፈጸሙት የአመጽ ሥራ ነው::» አለና ስለዚህ «አቡኑ መገደላቸው ተገቢ ነው? ወይስ ተገቢ አይደለም?» ቢል ካህናቱ በአፋጣኝ አስተያየታቸውን እንዲበጡ



በማዘዝ አፈጠጠባቸው:: ካህናቱም ለዚህ አስቸጋሪ ጥያቄ ወዲያውኑ መልስ ለመስጠት ተቸገሩ:: ይህም የሆነበት ምክንያት «አቡኑ መገደላቸው ተገቢ አይደለም» ካሉ እነርቡም የሚጠብቃቸው ዕድል ሞት ነው:: «የአቡኑ መገደል ተገቢ ነው» እንዳይሉ ደግሞ ለአገርና ለነጻነት መቆርቆርና መታገል ወንጀል አለመሆኑን እንደውም የተቀደሰ ተግባር እንደሆነ ያውቃሉና:: ካህናቱ በቀረበላቸው ጥያቄ ላይ ተወያዩ:: ከመካከላቸውም አነጋገር ይችላሉ ብሰው የሚያም ኑባቸውን አለቃ ቢረሳው የተባሉትን አባት መርጠው እንዲመልሱ አደረጉ:: አለቃ ቢረሳውም ለኮሎኔል ማልታ «እናንተም ደግ ገደላችሁ፤ እርሳቸውም ደግ ሞቱ» በማለት መልስ ሰጡ:: የአለቃ ቢረሳውን መልስ ምስጢር ያልተረዳው ጣሊያናዊው ኮሎኔል የወሰደውን እርምጃ የደገፉለት መሰሎት በመደሰት «አለቃ ቢረሳውን አቡን አድርጌ ሾሜዋለሁ» ብሎ የሟቹን ጳጳስ መስቀልና መቋሚያ በሽልማት እንዲሰጣቸው አዘዘ::

ጠላት ከሀገር ከወጣ በኋላ በ1935 ዓ.ም የብፁዕነታቸው ሀጽም ከነበረበት አልባሌ ሥፍራ ተለቅሞ በክብር በሳጥን ከተደረገ በኋላ በጎሬ ደብረ ገነት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን በክብር ተቀምጧል::

ሀገሪቷ ነፃነቷ ተመልሶ ንጉሡ ኢትዮጵያ ከገቡ በኋላ በ1934 ዓ.ም መታሰቢያ ይሆናቸው ዘንድ በሰማዕትነት ባለፉበት ጎሬ ከተማ አንድ ት/ቤት እንዲቆም አደረጉላቸው:: በዘመነ ደርግም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በጎሬ ከተማ መታሰቢያ የሚሆን ሐውልት ሊያቆሙላቸው ቀን ቆርጠው፣ ዜና ሕይወታቸውን ለማዘከር ጽሑፎች ተዘጋጅተው፤ እንደ ነገ ሊሔዱ እንደ ዛሬ ማታ ምክንያቱ ባልታወቀ ሁኔታ ከደርግ ጽ/ቤት ተደውሎ እንዳይሔዱ ተብለው ሐሳባቸውን ተግባራዊ ሳያደርጉ ቀርተዋል ይባላል:: የብፁዕ አቡነ ሚካኤል ረድኤት አይለየን:: አሜን::

# 3.4. ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ ቀዳማይ

## «ጳጳስ ዘሰሜን ኢትዮጵያ ተላዌ አሠሩ ለአቡነ ሳሙኤል»

## /1871 - 1947 ዓ.ም/





ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ ከአባታቸው ከመሪ ጌታ ክንፉና ከእናታቸው ከወ/ሮ ፈረደ እሸቴ በ1871 ዓ.ም. በወሎ ሀገረ ስብከት ዋግ አውራጃ ተወለዱ:: ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስም አዚያው ከቤተሰቦቻቸው ሳይርቁ ዞብል ሠፈረ ማርያም ከተባለው ቦታ ከነበሩት አለቃ ተድላ ዘንድ ከፊደል ጀምረው ንባብና ዳዊት ተማሩ:: የጀመሩትን ትምህርት በመቀጠልም ጸዋትወ ዜማ፣ ቅኔ፣ ውዳሴና ቅዳሴ ማርያም እንዲሁም የፍትሐ ነገሥትንና የዳዊትን ትርጓሜ ተማሩ:: በዚሁ ጊዜ ቁም ጽሕፈትንም በሚገባ ተማሩ::

ከዚህ በኋላ ራሳቸውን ለመንግሥተ ሰማያት ጃንደረባ በማድ ረግ ወደ ሐይቅ እስጢፋኖስ አባ ኢየሱስ ሞዓ ገዳም በመግባት መጽሐፈ መነኮሳትን ካጠኑ በኋላ ወደ ዠመዶ ማርያም ገዳም በመሔድ ሥርዓተ ምንኩስናን ፈጸሙ:: ከዚያም ዕውቀታቸውን ለማስፋፋት ወደ ቦሩ ሜዳ ሔደው አለቃ መርሻ ከተባሉ የዜማ ሊቅ ድጓን ተምረው አስመሰከሩ:: መሪ ጌታ ላቀው ወደ ተባሉ መምህ ርም በመጠጋት የቅኔ ትምህርታቸውን አጠናከሩ::

ከዚህ በኋላ ወደ ወልዲያ በመሔድ ለአምስት ዓመታት ያህል ዜማ ሲያስተምሩ ቆዩ:: ነገር ግን የብፁዕነታቸውን ትምህርትና ግብረ ገብነት በአንክሮ ሲከታተሉ የነበሩ አለቃ ተድላ የተባሉ አባት እርሳቸውም እንደ ሌሎቹ ወደ አራት ዓይናው ሊቅ መ/ር አካለ ወልድ ዘንድ በመሔድ ዕውቀታቸውን እንዲያደላድሉ መከሯቸው:: ብፁዕነታቸውም የአለቃ ተድላን ምክር በፍጹም እሺታ ተቀብለው ወደ መምህር አካለ ወልድ ወረዱ:: በዚያም የብሉያትንና የሐዲ ሳትን፣ የሊቃውንትንና የመጽሐፈ መነኮሳትን ትርጓሜ አጠናቀው ተማሩ:: በነበራቸውም የተደነቀ የቁም ጽሕፈት ሞያ ሃይማኖተ አበውን፣ መጽሐፈ ኢሳይያስን፣ አረጋዊ መንፈሳዊን፣ ፊልክስዩስን፣ ማር ይስሐቅን ንባቡን ከነትርጓሜው በግእዝ ቋንቋ በእጃቸው ጻፉ::

ከመምህር አካለ ወልድ ዘንድ ለመጻሕፍት ትርጓሜ መምህ ርነት የሚያበቃ የምስክር ወረቀት ከያዙ በኋላ ወደ ላስታ በመሔድ እያስተማሩ የነአኩቶ ለአብንና የገነተ ማርያምን ቤተ ክርስቲያን ማስተዳደር ጀመሩ:: በዚያ ቆይታቸው በርከት ያሉ ሊቃውንትን አስተምረው ለቤተ ክርስቲያን አበርክተዋል:: ከዚያም በ1911 ዓ.ም ወደ ሸዋ መጥተው ደብረ ሊባኖስ አጠገብ ያለውን የጫጋል መድኃኔ ዓለምን ገዳምና ገነተ ኢየሱስን አቅንተዋል::

ብፁዕነታቸው በዚህ ላይ እንዳሉ የስገሌ ጦርነት ተደረገ:: ጦርነቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ብፁዕነታቸው በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ጥሪ ወደ አዲስ አበባ መጡ:: ከዚያም በአንኮበር ቅዱስ ሚካኤል ደብር በአስተዳዳሪነት ተሹመው ለጥቂት ዓመታት

## 3.4. ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ ቀዳማይ

### «ጳጳስ ዘሰሜን ኢትዮጵያ ተላዌ
### አሠሩ ለአቡነ ሳሙኤል»

/1871 - 1947 ዓ.ም/



አገለገሉ:: ስኋላም ወደ አዲስ አበባ በመመለስ በግቢ ገብርኤል ገዳም ተሹመው እያገለገሉ በሚገባ አጠንክረው የተማሩትን መዝሙረ ዳዊት መጽሐፍ 1ኛ. የሃይማኖት፣ 2ኛ. የተስፋ፣ 3ኛ. የትምህርት፣ 4ኛ. የምስጋና፣ 5ኛ. የደስታ፣ 6ኛ. የልመና፣ 7ኛ. የታሪክ ፣ በማለት በሰባት በመክፈል ለተጠቃሚ በሚመች መልኩ በብራና ላይ በቀም ጽሕፈት ጽፈው በገዳሙ እንዲቀመጥ አድርገዋል::

በ1921 ዓ.ም. ለመጀመሪያ ጊዜ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዕውቀት መንፈሳዊ ወልዳ ተክባክባ ካሳደገቻቸው ሊቃውንት ልጆቿ ለጵጵስና መዓርግ ከመረጠቻቸው መካከል ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ አንዱ ሆኑ::

ብፁዕነታቸው በካይሮ መንበረ ማርቆስ ቤተ ክርስተያን የጵጵስናን መዓርግ አግኝተው ወደ ሀገራቸው ከተመለቡ በኋላ «ጳጳስ ዘሰሜኑ ኢትዮጵያ ተላዌ አሠሩ ለአቡነ ሳሙኤል» ተብለው በትግራይ ሀገረ ስብከት ተሾሙ:: ብፁዕነታቸው ወደ ትግራይ ከሔዱ በኋላ የተቀበሉትን የሐዋርያነት ተግባር በማስፋፋት ያላመኑትን ሰብክው ወደ አሚን ሥላሴ ማምጣትና ያመኑትንም ማጠናከር ጀመሩ::

ብፁዕነታቸው የተሰጣቸውን ሐላፊነት ካህናትን በማስተባበር ሰብቃት እየተወጡ ሳለ በ1928 ዓ.ም. ፋሺስት ኢጣልያ ሀገራችንን ለመውረር መጣ:: በዚህ ጊዜ ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ ዓድዋ ዓዲ አቡን ነበሩ:: በወቅቱ የአካባቢው ልዑል የነበሩት ራስ ሥዩም የኢጣልያ ፋሽስት መረብን ሳይሻገር ዳዕር ተኸሊ ከተሰለፉት አሽከሮቼ ጋር ሆኜ ደሜን አፈሳለሁ ብለው ተነሡ:: ይህንንም በአካባቢያቸው የነበሩት ብፁዕነታቸው ሰሙ:: እንደ ሰሙም አርቆ አስተዋይ ናቸውና በፍጥነት ወደ ልዑል ራስ ሥዩም ገሥግሰው በመሔድ እንዳሉት ወደ ጦር ግንባር እንዳይሔዱ፤ ሔደው ቢሞቱ ግን ጉዳት እንጂ ጥቅም እንደ ሌለው በአጽንዖት መከሯቸው::

ራስ ሥዩምም ወደ ዚያው ሳይሔዱ አሽከሮቻቸው ዳዕሮ ተኸሊ በተባለ ቦታ ላይ የተሰለፈውን ጦር ድል አድርገው እንደ አባረሩት ተሰማ:: በዚህ ጊዜ ራስ ሥዩም ጠላት ኃይሉን አጠናክሮ እንደሚመለስ ስለ ገመቱ ሌላ ኃይል ጨማምረው ወደ ተንቤን ተዛወሩ:: ብፁዕ አቡነ ይስሐቅም አብረው ሄዱ:: ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ራስ ሥዩም በተለያዩ ዐውደ ግንባሮች ከጣሊያን ፋሺስት ጦር ጋር ተፋልመዋል:: ብፁዕነታቸውም እስከ ግንባር ድረስ ከልዑሉና ከሠራዊታቸው ጋር በመገኘት የማጽናኛ ቃል ይሰጡ ነበር::

ከዕለታት አንድ ቀን ምሽት ልዑል ራስ ሥዩም ከሠራዊቶቻቸው ጋር ያገኙትን ድል በማስመልከት ድግስ አድርገው እየተደሰቱ ሳለ ጠላት ኃይሉን አስተባብሮ እየመጣ እንደ ሆነ ሰሙ::



ከደረሰው መረጃ እንጻር የጠላት ጦር ጠንከር ያለ ስለ ነበር ይህንኑ ለሠራዊታቸው ገልጠው ዝግጅት እንዲያደርጉ አሳሰቡ:: ሠራዊቱም ማሳሰቢያውን ተቀብሎ ከአሁን አሁን ጠላት ደርሶ ጥቃት ይከፍታል በማለት በፍጥነት መዘጋጀት ጀመረ:: ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ በሠራዊቱ መካከል ቆመው አንድ ጊዜ ሠራዊቱ እንዲረጋጋ ካደረጉ በኋላ የሚከተለውን ንግግር አደረጉ:-

> «ልጆቼ ሆይ አድምጡኝ:: ዝም በሉ:: ነገር ግን ዝም እንድትሉ የምመክራችሁ የጀግንነታችሁን ወኔ ለማብረድና ለማቀዝቀዝ አይደለም:: ከዚህ ቀደም በፈጸማችሁት ተጋድሎ ያስገኛችሁት ድል አድራጊነት ከፎከራችሁለት በላይ ልዩና የሚገመት በመሆኑ ወደ ፊትም የምታጉድሉት ነገር ስለ ማይኖር ለአገራችሁ ታማኞች ናችሁ፤ አሁን ወደ ጠላት ግንባር የመሔጃችን ጊዜ ስለ ደረሰ እኔም አንድ መሣሪያ አለኝና ያንን ሳስታጥቃችሁ እፈልጋለሁ:: መሣሪያ ያልኳችሁም አሁን የምናገረው ቃል ነው::
>
> እነሆ ይህች የምትመጣው ሌሊት የጸሎተ ሐሙስን ሌሊት ትመስላለች:: ይኸውም የመከራ ሌሊት በመሆኑ ነው:: ወርቅ በእሳት ተፈትኖ ጥራቱን እንደ ሚያሳይ እናንተም የዚህችን ሌሊት ፈተና ወጥታችሁ ሃይማኖታችሁንና የሀገር ፍቅራችሁን ሊታስመሰክሩ የተጠየቃችሁበት የጌታችሁንም እምነት አጉልታችሁ የምታሳዩበት በመሆኗ ነው:: ይህች ሌሊት ይሁዳ ጌታውንና ፈጣሪውን አሳልፎ የሰጠባት ሌሊት ናት:: ይህች ሌሊት ግን እናንተ ስለ ጌታችሁ ራሳችሁን አሳልፋችሁ ለሞት ለመስጠት የተዘጋጃችሁባት ናት:: ያቺ ሌሊት ሐዋርያት ጌታቸውን ጥለው የሸሹባት ናት:: ይህች ሌሊት ግን ይህ እንዳይደረግ ቃል የገባችሁባት ናት:: መጥፎ ለድል እንዳይገጥማችሁ እግዚአብሔር ይርዳችሁ:: ሃይማኖታች ሁና አንድነታችሁ የጸና ይሁን::»

ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ ይህንን ከተናገሩ በኋላ ከሠራዊቱ ጋር አብረው ወደ ጦር ግንባር ዘመቱ:: በሀገር ፍቅር ስሜት የነደደው፣ በብፁዕነታቸው ምክርና ቡራኬ የተነሣሣው የልዑል ራስ ሥዩም ሠራዊት ጠላትን ድል አድርጎ ወደ መጣበት መለሰው:: ነገር ግን አንድ በደስታው ላይ ጥላ ያጠላ ጉዳይ ተፈጠረ:: ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ በጠላት ተማረኩ::

ጣልያን ፋሺስት ወደ ኢትዮጵያ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ

ምእመኑንና ሠራዊቱን በማትጋት እሾሀ ሆነውበት የነበሩትን ብፁዕ አቡነ ይስሐቅን እንደ ያዘ ለግዞት ወደ ናኩራ ወስዳቸው:: ከናኩራም ወደ ሮማ ናፖሊ ከተማ ወስዳቸው::

በዚያው ለሁለት ዓመታት በግዞት ከቆዩ በኋላ በወቅቱ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ሆነው በተሾሙት ኢትዮጵያዊው ብፁዕ አቡነ አብርሃም አማላጅነት ወደ አገራቸው ወደ ኢትዮጵያ ተመል ሰው አዲስ አበባ ከተማ ከብፁዕነታቸው ጋር ተቀምጠው ማገ ልገል ጀመሩ::

አቡነ አብርሃም ካረፉ በኋላም ዕጨጌ ተብለው የደብረ ሊባኖስን ገዳም እንዲያስተዳድሩ ተደርገው ለአንድ ዓመት እንዳገለ ገሉ ወራሪው የፋሺስት ጦር ድል ተመትቶ የሀገሪቱ ነጻነት ተመለሰ::

በዚህ ጊዜ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን በኢጣልያ ፋሺስት አስገዳጅነት የተሾሙትን ጳጳሳት እንዳይሠሩ አውግዞ ቀድሞ ከእስክ ንድርያ የተሾሙት ጳጳሳት እንዲሠሩ ፈቅዳ ስለ ነበር ከቀድሞዎቹ ጳጳሳት አቡነ ይስሐቅ ስለ ተገኙ የጵጵስናውን ሥራ እርሳቸው እንዲሠሩ ተደረገ:: በመሆኑም ከ1937 ዓ.ም ጀምሮ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ እስከ ተሾሙበት 1941 ዓ.ም ድረስ መኖሪያቸው አዲስ አበባ ሆኖ በጎንደር፣ በጎጃም፣ በትግራይ፣ በኢሉባቦር እየተ ዘዋወሩ የሐዋርያነት ተግባራቸውን አከናወኑ::

ከዚያም በ1941 ዓ.ም ወደ ወሎ ሀገረ ስብከት ተዛውረው በሊቀ ጳጳስነት አገልግለዋል:: በመጨረሻም ወደ ጥንት ሀገረ ስብከ ታቸው ወደ ትግራይ ተመልሰው ዓድዋ አዲ አቡን ተቀመጡ:: በዚ ያም የተለያዩ መንፈሳውያት ተግባራትን ሲያከናውኑ ከቆዩ በኋላ ባደረባቸው ድንገተኛ ሕመም ምክንያት አሥመራ ሐኪም ቤት ሲታከሙ ቆይተው በ1947 ዓ.ም ነሐሴ 4 ቀን በተወለዱ በ78 ዓመ ታቸው ዐረፉ:: የቀብራቸው ሥነ ሥርዓትም በርእሰ አድባራት ወገዳማት አክሱም ጽዮን ማርያም ተፈጸመ::

በሥርዓተ ቀብራቸው ከተገኙት ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን አንዱ የነበሩት አለቃ ልሣነ ወርቅ ወ/ዳዊት በወቅቱ የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት ት/ቤተቶች ጠቅላይ ጽ/ቤት ዋና ሥራ አስኪያጅ የሚከተለውን መወድስ ሰጥተው ነበር::

ደቂቀ ስቆቃው ኀሥዎ ለዘተሠወረ፡ በሉቅለ ሞተ ዓቤል
ይስሐቅ ለእመ ይትረከብ ዳኅናሁ
ለረኪበ ድኂን አብርሃም እንዘ የሐሥሥ ተሰፋሁ
እም:ነበ አልቦ እስመ ተረክበ፡ በግዕ ዐዓዳ ለይስሐቅ ቤዛሁ፡



ባሕቱ ዘይተግሁ
ለኃሢሦቱ ረከቡ፣ ውስተ ቤተ አብርሃም ምሥዋሪሁ::
የብፁዕነታቸው ረድኤት አይለየን:: አሜን::

## 3.5. ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ቀዳማይ

## «ጳጳስ ዘደቡብ ኢትዮጵያ ወዕጨጌ ዘደብረ ሊባኖስ ተላዌ አሠሩ ለአቡነ ተክለ ሃይማኖት»

## /1868 - 1925 ዓ.ም/





ዕጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ይባሉ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ በቀድሞው የቤጌምድር ጠቅላይ ግዛት ደራ አቡነ ሐራ በሚባለው ቦታ ሚያዝያ 19 ቀን 1868 ዓ.ም ተወለዱ:: በወላጆቻቸው ቤት በክብካቤ አድገው ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በዚያው በአጥቢያቸው የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ መንፈሳዊ ትምህርታቸውን ተማሩ:: ከዚያም በ1880 ዓ.ም ወደ ጎጃም ተሻግረው በወቅቱ የጎጃም ጳጳስ ከነበሩት ከግብፃዊው አቡነ ሉቃስ መዓርገ ዲቁናን ተቀበሉ::

ከዚህ በኋላ ወደ ትውልድ ሀገራቸው ተመልሰው በጥምቀት ክአብራክ መንፈስ ቅዱስ ክማኅፀነ ዮርዳኖስ ሲወለዱ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ተብለው የተሠየሙበትን አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በዲቁና እያገለገሉ ለዓመታት ቆዩ:: ከዚያም በመንፈስ ቅዱስ መሪነት በመጀመሪያ ወደ ሬማ መድኃኔ ዓለም ገዳም፣ ቀጥሎም ወደ አቡ ሥላሴ ገዳም በመሔድ ትምህርታቸውን እየተማሩና ሥርዓተ ገዳም እያጠኑ ረዘም ላሉ ዓመታት ቆዩ::

ብፁዕ እቡነ ሳዊሮስ በሕይወት ዘመናቸው ሳይፈጽሙት በሞት እንዳይጠሩ ወደ እግዚአብሔር ዘንድ አብዝተው የሚጸልዩበት አንድ ሕልምና ፍላጎት ነበራቸው:: ይኸውም በሕፃንነታቸው ፈደለ ሐዋርያ ሲያነቡ ጀምሮ ለሚን እየጠሩ ቅድስትነቷን በእአምሮእቸው ሲሥሏት የኖሯትን ኢየሩሳሌምን መጎብኘት፣ ቅዱሳት መካናቷንም መሳለም ነበር:: ብፁዕነታቸው በተለይ ዕድሜያቸው እየጨመረ ሲሔድ ቅድስት ሀገርን የመጎብኘት ፍላጎታቸው እየጨመረ በመምጣቱ በ1900 ዓ.ም ወደ ደብረ ታቦር ሔደው ራስ ጉግሳ ወሌንና ወ/ሮ ዘውዲቱ ምኒልክን ደጅ መጥናትን ቀጠሉ::

በዚህ ዓይነት ከራስ ጉግሣና ወ/ሮ ዘውዲቱ ጋር የተዋወቁት ብፁዕነታቸው መልካም መልስ በማግኘታቸው ከእነሱ ጋር ለወራት ያህል ቆዩ:: መቼ ጸሎቴ ተበምቶ ወደ ኢየሩሳሌም እሸኝ ይሆን እያሉ በመጣባበቅ ላይ ሳሉ ዓፄ ምኒልክ መታመማቸው ተሰማ:: በዚህም የተነሣ ልጃቸው ወ/ሮ ዘውዲቱ አባታቸውን ለማስታመም ወደ አዲስ አበባ ሲመጡ ኢየሩሳሌም ስደዱኝ እያሉ ደጅ ሲጠኑ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስም ተከትለው መጡ:: በዚህም ንጉሡ ዓፄ ምኒልክን በጸሎታቸው የታወቁ አባቶች ጸሎት እያደረጉ ጠበል እንዲያጠምቋቸው በተደረገ ጊዜ ብፁዕነታቸው እንዱ በመሆን ሲያጠምቁ ቆዩ:: ይሁን እንጂ ንጉሡ በዚህ ዓለም ይኖሩበት ዘንድ የተሰጣቸው ዘመን ዐልቆ ኖሮ ዐረፉ:: የንጉሡን ሞት ተከትለውም ልጅ ኢያሱ መንበሩን ለመያዝ ሲሉ የዓፄ ምኒልክ ልጅ ዘውዲቱ ቤተ መንግሥቱን ለቀው እንዲወጡ አዘዙ:: ዘውዲቱም በታዘዙት መሠረት ግቢውን ለቀው ፋሊ ወደ ተባለ ቦታ ወረዱ:: በዚህ ጊዜ

# 3.5. ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ቀዳማይ

## «ጳጳስ ዘደቡብ ኢትዮጵያ ወዕጨጌ ዘደብረ ሊባኖስ ተላዌ አሠሩ ለአቡነ ተክለ ሃይማኖት»

/1868 - 1925 ዓ.ም/



ያኔ መምህር ተድላ ይባሉ የነበሩት ብፁዕነታቸውም አብረዋቸው ወረዱ::

ይሁን እንጂ በ1909 ዓ.ም ልጅ ኢያሱ የማዘዝ ሥልጣናቸውን ተነጥቀው ወ/ሮ ዘውዲቱ ንግሥተ ንግሥታት ተብለው ተሾሙ:: በዚህ ጊዜ በንግሥቷ የስደት ዘመን ሁሉ አብረው የተቸገሩት ብፁዕነታቸው እንደ ውለታ ተቆጥሮላቸው የአቡነ ሐራንና የወለተ ጴጥሮስን ገዳማት መምህርነት ተሾሙ:: በዚህ ሹመታቸው ለአንድ ዓመት ያህል ካገለገሉ በኋላ ታኅሣሥ 27 ቀን 1910 ዓ.ም መልአከ ገነት ተብለው የገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ደብር አስተዳዳሪ ሆነው ተሾሙ::

ከንግሥተ ንግሥታት ዘውዲቱ ቀረብ ብለው የተሾሙበትን ደብር ለአራት ዓመታት ያህል በብቃት ካስተዳደሩ በኋላ በውስጣቸው ይዘውት የነበረውን የዘመናት ሕልም እውን የሚያደርጉበት ቀን ደረሰ:: በ1914 ዓ.ም ወደ ኢየሩሳሌም ሔደው ቅዱሳት መካናትን ተሳለሙ:: በዚያውም ወደ ግብፅ ወርደው በዚያ ያሉ ገዳማትን ጐብኝተው ወደ ኢትዮጵያ ተመለሱ::

ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ከኢየሩሳሌምና ግብፅ ከተመለሱ በኋላም በዚያው በቀድሞው የገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪነታቸው ሊያገለግሉ ቆዩ:: በኋላም ኅዳር 17 ቀን 1917 ዓ.ም ዕጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ተብለው የታላቁ የደብረ ሊባኖስ ገዳም ዕጨጌ ሆነው ተሾሙ:: በዕጨጌነታቸውም ስፊ አገልግሎትን ሲያበረክቱ ቆይተዋል:: ካበረከቷቸው ዐበይት አገልግሎቶች ውስጥ ዕጨጌ ከሆኑ ከአንድ ዓመት በኋላ መስከረም 8 ቀን 1918 ዓ.ም መንፈሳዊ ጉባኤን አቋቁመው የቤተ ክርስቲያን የወደ ፊት ጉዞ ቀና እንዲሆን የጣሉት መሠረት ተጠቃሽ ነው::

የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከ1600 ዓመታት በኋላ በ1921 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ ከኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ተመርጠው ኤጲስ ቆጶሳት እንዲሾሙ በተፈቀደ ጊዜ ብፁዕነታቸው ከአምስቱ አንዱ ሆነው ተመረጡ:: ይሁን እንጂ በ1921 ዓ.ም ተመራጮቹ አባቶች ወደ ግብፅ ሔደው መዓርጉን በተቀበሉ ጊዜ ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ባጋጠማቸው ሕመም የተነሣ አብረው ሊሔዱና ለሹመቱ ሊደርሱ አልቻሉም ነበር:: አንዳንድ አባቶች እንደሚሉት ግን ብፁዕነታቸው ወደ ግብፅ ያልወረዱት ሹመቱን ስላልፈለጉት ነበር::

ይሁን እንጂ አባቶች ወደ ግብፅ ሔደው መዓርጉን ባገኙ በዓመቱ የወቅቱ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ የነበሩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሐንስ በራስ ተፈሪ ግብዣ ለጉብኝት ወደ ኢትዮጵያ መጡ:: በዚህም ጊዜ የቤተ መንግሥቱም ሆኑ የቤተ ክህነቱ



ባለሥልጣናት ከዓመት በፊት ከሌሎች አባቶች ጋር ወደ ካይሮ ተጉዘው ሥልጣኑን ለመቀበል ባይችሉም ዕጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ሹመቱ ስለ ሚገባቸው ፓትርያርኩ ወደ ኢትዮጵያ እንደ መጡ ሾመዋቸው ቢሔዱ የሚል የይሁንታ ሐሳብ አቀረቡ:: ሐሳቡ ተቀባይነት አግኝቶም ጥር 20 ቀን 1922 ዓ.ም በዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ቤት በአታ ለማርያም ገዳም «አባ ሳዊሮስ ጳጳስ ዘደቡብ ኢትዮጵያ ወዕጨጌ ዘደብረ ሊባኖስ» ተብለው ተሾሙ:: /የሹመታቸውን ደብዳቤ በአባሪ አንድ ይመለከቷል/::

ብፁዕነታቸው ምንም እንኳን በደቡቡ የሀገራችን ክፍል ቢሾሙም መቀመጫቸው አዲስ አበባና ደብረ ሊባኖስ ነበር:: ንግሥተ ንግሥታት ዘውዲቱ ብፁዕነታቸውን ያቀርቧቸው ስለ ነበር የረጅም ጊዜ ሕልማቸው የነበረውን የባዓታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያንን ሕንፃ ግንባታና በአገልጋይ ካህናት መጠናከር አደራውንና ሐላፊነቱን የሰጧቸው ለብፁዕነታቸው ነበር ይባላል:: በተለይ ለቤተ ክርስቲያኗ የሚሆኑ አገልጋይ ካህናትን፣ በየዕውቀት መስኩ የሚያስተምሩ ሊቃውንትን የመምረጡን ተግባር ሙሉ በሙሉ ለብፁዕነታቸው ሰጥተዋቸው ነበር:: ይሁን እንጂ የንግሥተ ንግሥታቷ ሐሳብና ፍላጎት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ የሆነው በኋላ በቦታው በተሾሙ አባቶች ነው::

ቤተ ክርስቲያንን ለረጅም ዓመታት በማገልገል የቆዩት ብፁዕነታቸው ሹመቱን ከላይ በተጠቀሰው ሁኔታ ቢያገኙም ብዙም ሳይቆዩ ከጎንደር ጀምሮ አስከትለዋቸው ለወግ ለመዓርግ ያበቋቸው ንግሥተ ንግሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ ዐረፉ:: በዚህ የተነሣ አሳቸውም እንደ ሌሎች የንግሥቷ ቀራቢ አባቶች ከቤተ መንግሥቱ ያገኙት የነበረው ክብካቤ ተቋረጠ:: በዚህ ሁሉ የተነሣ ብፁዕነታቸው ሁሉንም ትተው ባልቻ አባ ነፍሶ በሰጧቸው ቦታ ላይ /ራሳቸው ንግሥተ ንግሥታት ዘውዲቱ ናቸው የሰጧቸው የሚሉም አሉ/ የማኅደረ ስብሐት ልደታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያንን አሠርተው በዚያው ገቢ መኖሪያቸውን አደረጉ:: የቤተ ክርስቲያኗን ስም ማኅደረ ስብሐት ብለው የሠየሟት እሳቸው እንደ ሆኑ ይነገራል:: ይሁን እንጂ ብዙም ሳይቆዩ ባደረባቸው የአንድ ወር ተኩል ሕመም ጳጉሜን 2 ቀን 1925 ዓ.ም ከዚህ ሥጋዊ ዓለም በሞት ተለዩ:: ሥርዓተ ቀብራቸውም ባሠሯት የልደታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን መቅደስ ውስጥ ተፈጸመ:: ብፁዕነታቸው በየዓመቱ ጳጉሜን 2 ቀን በማኅደረ ስብሐት ቅድስት ልደታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን በታላቅ መንፈሳዊ ሥነ ሥርዓት ይዘከራሉ:: ብፁዕነታቸው በቤተ ክርስቲያንዋም ዘወትር ሲዘከሩ ይኖሩ ዘንድም የቤተ ክርስቲያንዋ ሰንበት ት/ቤት «ተክለ ሳዊሮስ» ተብሎ ይጠራል:: የብፁዕነታቸው ረድኤት አይለየን:: አሜን::